ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሁፍ- አማርኛ ትምርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በደብረ ምጥማቅ የሸንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ስነምግባርን ከማስተማር አንፃር ያላቸው ሚና ፍተሻ

በ

መሰረት ኦሊቃ

ሰኔ 2014 ዓ.ም

ጅማ

# በደብረ ምጥማቅ የሽንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ስነምግባርን ከማስተማር አንፃር ያላቸው ሚና ፍተሻ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሁፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

መሰረት ኦሊቃ

አማካሪዎች

ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ(ዋና አማካሪ)

ዶ/ር ለማ ንጋቱ (ረዳት አማካሪ)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሁፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በደብረ ምጥማቅ የሸንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ስነምግባርን ከማስተማር አንፃር ያላቸው ሚና ፍተሻ

ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

መሰረት አሊቃ

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ______________________________ፊርማ______________________

የውስጥ ፈታኝ ስም_______________________
ፊርማ_______________________

የውጭ ፈታኝ ስም___________________________ፊርማ______________________

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደብረ ምጥማቅ ሽንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ስነምግባር ከማስተማር አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መፈተሽ በሚል ዋና አላማ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ጥንታዊ ገዳም ከተመሰረተ 394 አመታትን ያስቆጠረ ትልቅ ገዳም ነው፡፡ በዚህ ጥናት አስራ አንድ መረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን ስድስቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ የጥናቱ ዓላማም የተሳካ ይሆን ዘንድ ጽሁፋዊ ማስረጃዎችን ከመጠቀም በተጨማሪ በቃለ መጠይቅ፣ በሰነድ ፍተሻ፣ በቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በማስታወሻ፣ በምስል፣ በመቅረጸ ድምጽ እና እንደአስፈላጊነቱ በቪደዮ ካሜራ በማጠናቀር መረጃዎቹን ክግብ ለማድረስ ተሞክሯል፡፡ እነዚህ ተረኮች በገላጭ የምርምር ዘዴ በመጠቀም እና በተረክ ትንተና ንድፍ ሃሳብ መንደርደሪያነት ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም የተጠኝ አካባቢና የማህበረሰቡ ዳራዊ ገለጻ ተቃኝቷል፡፡ በጥናቱ የተለያዩ ተረኮች የተሰበሰቡ ሲሆን ተረኮቹ የገዳሙን ማህበረሰብ ስነምግባር በማስተማር እና በመቆጣጠር ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡

## ምስጋና

ይህንን ጥናት በማዘጋጅበት ወቅት በተለያየ መልኩ እገዛ ያደረጉልኝ አካላት በርካታ ናቸው፡፡ የጥናቱ አማካሪ ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) ረቂቁን ጽሑፌን በማንበብ፣ ለጥናቱ አቅጣጫ በመጠቆም እና በዳበረ ልምዳቸው ጥናቱ መልኩን እንዲይዝ በማድረግ ለጽሁፌ ዳር መድረስ ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጉ ባለውለታዬ ናቸው፡፡ለረዳት አማካሪዬ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር) ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ይህንን የትምህርት ዕድል እንዳገኝ በማድረጉ እና ለጥናቱ መሠረታዊ ወጪዎች ድጋፍ በመስጠቱ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል፡፡ጊዜያቸውን በመሠዋት የሚያውቁትን ሁሉ ለማካፈል ፈቃደኛ የሆኑልኝን መረጃ አቀባዮቼን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡በተጨማሪም ስራዬን በማየት የተለያዩ ሀሳቦችን በመስጠት ያበረታቱኝን መምህራኖቼን በጠቅላላ ማመስገን እወዳለሁ፡፡

በተለይ እስከዛሬ ድረስ ፍቅር እና እንክብካቤያችሁ ምክርና ተግሳፃችሁ ያልተለየኝ ቤተሰቦቼ እኔን ለማስተማር ከሚገባው በላይ ዋጋ ለከፈለው አባቴ ኮማንደር ኦሊቃ ገለታ፣ ከእናትነት በላይ ስም ቢኖር ለሚገባት እናቴ ወ/ሮ ድንቅነሽ አሰፋ ፣ ይህን ጥናት ጀምሬ እስከጨርስ ድረስ ከጎኔ ሆነው ሲያበረታቱኝ ለነበሩት እህቶቼ ሳምራዊት ኦሊቃ እና ህይወት ኦሊቃ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡በምክርና አይዞሽ በማለት ስራዬንም በማየት ከዲግሪ ጀምሮ ላልተለዩኝ መምህሬ ለዶ/ር ዳዊት ፍሬው ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በመጨረሻ በነበሩኝ የትምህርት አመታት አብራችሁኝ ለነበራቹ የክፍል ጓደኞቼ እንዲሁም ለጥናቱ አስተዋፅኦ አድርጋችሁ በዝርዝር ያልተጠቀሣችሁ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

በዚህ ጥናት ላይ የምጠቀምባቸውን ቃላት ለአንባቢ ግልፅ ለማድረግ በማሰብ አጥኚዋ የቃላቱን ፍቺ እንደሚከተለው አስቀምጣለች፡፡ የቃላቶቹ ፍቺ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 ካሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላትን በመጠቀም የተገኙ ናቸው፡፡

ምኔት -ለ ገዳማውያን የተሰጠ ስያሜ (መጠሪያ) ሲሆን ፤

አበምኔት- ለወንዶች የገዳም አለቃ ፣ሹም ወይም አስተዳዳሪ፡፡

እመምኔት - የሴቶች ገዳም አለቃ ፣ ሹም ወይም አስተዳዳሪ፡፡

ምዕመን - አማኞች

አለማዊ - (መንፈሳዊ ያልሆነ) ስጋዊ

አባሆይ - የወንድ መነኩሴ መጠሪያ፡፡

እማሆይ - የመነኩሲት መጠሪያ

ገዳም - መነኮሳት ከአለማዊ ኑሮ ተገለው በሀይማኖታዊ ስርአትና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተክርስትያን ያለበት ቦታ ነው፡፡

ማውጫ


አጠቃሎ ........ I

ምስጋና ........ II

የቁልፍ ቃላት ፍቺ ........ III

ምዕራፍ አንድ ፤መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.3 የጥናቱ ዋና አላማ ........ 3

1.3.2 ዝርዝር አላማዎች ........ 3

1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 3

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 4

1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ቸግሮች የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 4

ምዕራፍ ሁለት ፤ ክለሳ ድርሳናት ........ 5

2. 1 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ........ 5

2.1.1 የገዳም ምንነት ........ 5

2.1.2 ተረክ ........ 9

2.2 የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ ........ 15

2.2.1 ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ........ 15

2.2.2 የስነ ልቦዊ ንድፈ ሀሳብ ........ 18

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 19

2.4 ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዳራዊ ገለፃ ........ 23

2.4.1. ጥናቱ. የተካሄደበት ወረዳ አጠቃላይ መረጃ ........ 23

2.7.2 የወረዳው መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ንብረት ........ 24

2.7.3 በወረዳው የሚገኙ ቅርሶች ........................................................................ 24

ምዕራፍ ሶስት ፤ የጥናቱ ስነ ዘዴ እና አካሄድ ................................................................ 26

3.1 የጥናቱ ዘዴ ........................................................................................ 26

3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ .............................................................................. 26

3.2.1 የቦታ ናሙና አመራረጥ ............................................................................ 26

3.2.2 የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ ................................................................ 26

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ............................................................................ 26

3.3.1. ቃለ መጠይቅ ...................................................................................... 27

3.3.2 ቡድን ተኮር ውይይት ............................................................................... 27

3.3.3 ሰነድ ፍተሻ ........................................................................................ 27

3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ .............................................................................. 28

3.5 ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች ............................................................................... 28

ምዕራፍ አራት ፤የመረጃ ትንተና ........................................................................... 29

4.1 ከሸንኮራ ዩሀንስ ገዳም የተገኙ ተረኮች ትንተና ..................................................... 30

5.1.1 የታላቁ የደብረ ምጥማቅ ሸንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና ስነ ምግባራዊ ፋይዳቸው ........................................ 31

5.1.2 የገዳሙን ቅድስና እና ክብር የሚገልፁ ተረኮች እና ስነምግባራዊ ፋይዳቸው .. 36

5.1.3 በገዳሙ የተፈፀሙ ፈውሶች እና ገቢራተ ተአምራት ተረኮች ............................ 40

4.1 .4. ገዳሙ የማህበረሰቡን ስነ-ምግባር የሚቆጣጠርባቸው ተረኮች ........................ 45

ምዕራፍ አምስት ፤ ማጠቃለያ ................................................................................ 52

ዋቢ መፅሀፍት ................................................................................................ 54

አባሪ 1 ......................................................................................................... 57

የሸንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ምስአል ወምስጋድ የእናቶች አንድነት ገዳም አመሰራረት ................... 57

አባሪ 2 ......................................................................................................... 58

ከስፍራው የተሰበሰቡ ተረኮች.....58
አባሪ 3.....62
ከቦታው የተገኙ ምስሎች.....62
አባሪ 4.....65
መረጃ ለመሰብሰብ የቀረቡ ጥያቄዎች.....65
አባሪ 5.....66
የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ .....66

## ምዕራፍ አንድ ፤መግቢያ

ይሕ ጥናት በሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ከስነምግባር አንፃር ለህብረተሰቡ ወይም ለአካባቢው ነዋሪ ያላቸው ሚና ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜም ተረኮቹን ከመሰብሰብ ባለፈ ተረኮቹን ትውልድ ከመቅረፅ አንፃር ያላቸውን ጠቀሜታ ፈትሿል፡፡

ጥናቱ በአጠቃላይ በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን በምዕራፍ አንድ ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ የጥናቱ ወሰን እና ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሄ ሀሳቦች የሚቀርብ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድርሳናት ፣ የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና ስነምግባራዊ ጉዳዮች ተካተዋል፡፡ በሶስተኛው ምዕራፍም የጥናቱ ዘዴ የቀርበ ሲሆን በዚህም ስር አጥኚዋ ለጥናቱ የተጠቀመችውን መረጃ መሰብሰቢያ እና መረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ለምን እንደተመረጡ ጭምር ተገልፃል፡፡ በአራተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ዋና ክፍል የሆነው ትንታኔው በስፋት ቀርቧል፡፡የመጨረሻው ምዕራፍ አምስት ሲሆን በዚህም የጥናቱ ማጠቃለያ አጭር እና ግልፅ በሆነ መንገድ ተቀምጧል፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶች ከጥንት ጀምሮ ሲተገበሩ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል ክርስትና ፣ እስልምና እና ሀገር በቀል እምነቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በእነዚህ እምነቶች ውስጥ የተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን እናገኛለን፡፡ የተለያዩ ምሁራን የገዳም ስርዓቶች ላይ ምርምር አካሂደዋል፡፡ ስርዓተ ቅዳሴ፣ ስርዓተ ግንዘት ፣ የመዝሙር ግጥሞች፣ የቆሎ ትምህርት ፎክሎራዊ ገጽታዎች ፣ መንዙማዎች ወዘተ… በተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተመራማሪዎች ተጠንተዋል፡፡ ሐይማኖታዊ ፎክሎርን መዝሙር፣ ተረክ፣ እምነት፣ ስርዓት፣ መድሀኒት፣ አለባበስ፣ ጥበብ በመሳሰሉ ዘውጎች መክፈል እና ማጥናት እንደሚቻል ነገር ግን ኃይማኖታዊ ፎክሎር ኃይማኖታዊ እና ከኃይማኖቱ ውጪ ያሉ ልማዳዊ ጉዳዮችን የምንመረምርበት በመሆኑ እንደ እምነት እና ሌሎች ትውፊታዊ ጉዳዮች ያሉት በሁሉም ዘውጎች ሊንፀባረቁ ስለሚችሉ ክፍፍሉን አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ወንደሰን Danielson, (1986: 52-53)ን ጠቅሶ ያስረዳል፡፡ስለዚህም ሀይማኖታዊ ፎክሎርን በምናጠናበት ጊዜ የሀይማኖት ዋና ጉዳይ የሆነውን እምነትን እንዳንነካ መጠንቀቅ አለብን፡፡

ገዳማት ላይ በማተኮር ከተሰሩት አብዛኞቹ ጥናቶች ከገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ከቁሳዊ ባህል እና ከገዳሙ ስርዓት ጋር በአንድነት ያጠኑ ናቸው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከተጠኑ ጥናቶች ውስጥ ምህረት ተስፋዬ (2003 )የጣና ቂርቆስ ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት ፣ተስፋዬ ተገኝ (2003) የደብረ ነጎድጓድ ሀይቅ እስጢፋኖስ አቡነ እየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረት እና ቁሳዊ ባህል ጥናት ፣መሪማ መሀመድ (2009 ) የእንጦጦ ሀመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት፣አንተነህ አየነው (2011) በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና የሚሉት ለአብነት ያህል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህም ሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን የሚያነሱት ጥናቶች አላማቸው በአብዛኛው የገዳማቱን አመሰራረት መፈተሽ እና በገዳማቱ የሚነገሩ ተረኮችን ይዘት መተንተን ነው፡፡ አጥኚዋ በዚህ ጥናት በገዳሙ የሚነገሩ ተረኮች ከመጠናታቸው ባለፈ ያላቸውን ስነምግባራዊ ፋይዳ ለማሳየት ትሞክራለች፡፡ ምክንያቱም በሁሉም እምነቶች ላይ የምናገኛቸው ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከኢትዮጵያዊ ስነምግባር ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ስላላቸው ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ ይህህን ጥናት ለማጥናት ያነሳሷት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡አንደኛው አነሳሽ ምክንያት አጥኚዋ ለእምነታዊ ጉዳይ በአንድ አጋጣሚ ወደ ሽንኩራ ዮሀንስ በሄደችበት ወቅት የሰማቻቸው ተረኮች እጅግ በጣም ስለሳቧት እና አሁን በ ሀገራችን እየሰማናቸውም ሆነ እያየናቸው ያሉት ነገሮች በብዙ መልኩ ኢ-ሞራላዊ እና የሰው ልጅ በዚህ ደረጃ ምግባር እንዴት ይጎድለዋል?ብለን እንድናስብ የሚያስገድዱን መሆናቸው፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስነምግባርን የሚያስተምሩ በመሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያትያት ደግሞ በገዳሙ ዙሪያ የተጠና ጥናት አጠኚዋ ባለማግኘቷ እና በገዳሞች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች በአብዛኛው የሚያተኩሩት ተረኮቹን መሰብሰብ ላይ ብቻ እንጂ ተረኮቹን ከስነምግባር ጋር አያይዞ የተሰራ ጥናት ባለመኖሩ ይህን ክፍተት ለመሙላት አጥኚዋ ይህን ጥናት ለመስራት ተነሳስታለች፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮችን ስነምግባርን ከማስተማር አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መተንተን ነው፡፡ ይህ ጥናት ከዋና ዓማው በተጨማሪ የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎች አካቶ ይዟል፡፡

### 1.3.2 ዝርዝር አላማዎች

- የሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም እንዴት እና በማን አማካኝነት እንደተመሰረተ ማሳየት ፣
- በገዳሙ ውስጥ ያሉት አባቶች እና እናቶች ተረኮቹን በሚተርኩበትን ወቅት የለውን የቃላት አጠቃቀማቸውን መፈተሸ፣
- በተረኮቹ አማካኝነት የመፈጠረውን የገዳማውያኑን እና የአካባቢውን ማኀበረሰብ ትስስር መመርመር ፣
- ተረኮቹ ለገዳሙ ማህበረሰብ የሚሰጡትን ስነምግባራዊ ፋይዳ መተንተን ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

- ❖ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች ስነምግባርን ከማስተማር እና እንዳይጣሱ ከመቆጣጠር አንፃር ያላቸው ሚና ምንድነው ?
- ❖ ገዳሙ እንዴት እና በማን አማካኝነት ተመሰረተ?
- ❖ ተረኮቹን በሚተርኩበትን ወቅት ተራኪዎቹ የቃላት አጠቃቀማቸው እንዴት ነው?
- ❖ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች በገዳሙ በሚኖሩት መናኒያን እና በአካባቢው ማኀበረሰብ መካከል ትስስር ከመፍጠር አንፃር ምን ፊይዳ አላቸው?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ በሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም ላይ መደረጉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከእነዚህም መካከል

- ✓ በአሁኑ ግዜ የምናያቸውን የስነምግባር ግድፈቶችን ለማስተካከል እንደ አንድ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ✓ ስለ ገዳሙ አመሠራረት እንዱሁም ከገዳሙ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች ለመመርመር ለሚነሡ አካላት እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ✓ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩ ተረኮች በመመርመር የገዳማውያኑን እና የአካባቢውን ነዋሪዎች አኗኗራቸውን እና አሳተሳሰባቸውን ለመረዳት ያስችላል፡፡

✓ በገዳሙ ላይ እና ተረኮች ከስነምግባር አንፃር ያላቸውን ሚና መፈተሽ ላይ ጥናት ያልተካሄደ በመሆኑ ይህንን ክፍተት ይሞላል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በሸንኮራ ዩሀንስ ገዳም ውስጥ የሚነገሩ ተረኮችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን ለገዳሙ እና ለገዳማውያኑ ያላቸውን ፋይዳ በመመርመር እና ስነምግባር በማስተማር ረገድ ያላቸውን ሚና ፍተሻ ላይ ብቻ ይወሰናሉ፡፡ ጥናቱ የገዳሙን የአስተዳደር ሥርዓቶችን ፣ መዝሙሮችንም ሆነ ከበራዎችን አይመለከትም፡፡

## 1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች

አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማከናወን በምትነሳበት ወቅት ለጥናቱ የሚሆኑትን መረጃዎች በሰፊው ማግኘት እንደምትችል አስባ ነበር፡፡ምክንያቱም ገዳሙ እጅግ በጣም ጥንታዊ በመሆኑ እጅግ ብዙ ጥንዊ ታሪኮች፣ ቁሶች እና ሰነዶች ማግኘት እንደምትችል አስባ የነበረ ቢሆንም መረጃ ለመሰብሰብ በወጣችበት ሰዓት ግን ያሰበችውን ያህል በጥንት ጊዜ ስለነበበረው ነገር የሚያስረዳ ሰውም ሆነ ሰነድ አላገኘችም፡፡ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በአንድ ወቅት በገዳሙ የተነሳ እሳት ትልቅ ውድመትን አስከትሎ ብዙ ሰነዶች እና የተለያዩ መዛግብት እንዲጠፉ በማድረጉ ነው፡፡ሆኖም የዞኑ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ በፊት በተለያዩ አጋጣሚዎች ተሰንደው የተቀመጡ መረጃዎችን በመስጠት እና የተለያዩ ታሪኩን ያውቃሉ ተብለው የሚታሰቡ ሌላ አካባቢ ላይ የሚኖሩ ሰዎችን አድራሻ በመስጠት ባደረጉላት ትብብር እና በአካባቢው ያሉ አዛውንቶች ባደረጉላት እገዛ ምክንያት አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ችላለች፡፡

# ምዕራፍ ሁለት ፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2. 1 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

### 2.1.1 የገዳም ምንነት

የገዳምን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ፀሀፍት የተለያዩ ፍቺዎችን ሰጥተው እናገኛለን፤ ከእነዚህም መካከል በዚህ ጥናት የተወሰኑትን እናያለን፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948፣302) "ገዳም በቁሙ ምኔት፣ ደብር፣ የመነኮሳት ሰፈር፣ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፣ በደለኛ ሸሽቶ የሚጠጋበት፣ ድውይ የሚማጠንበት ደብር፣ ዱር፣ ጫካ፣ ወማ፣ በረሀ፣ በዳ፣ ከሀገር ከመንደር የራቀ የአራዊት ክፍል…" በማለት ገልፀውታል፡፡በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማእከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣503) ገዳም ማለት መነኮሳት ከዓለማዊ ኑሮ ተገልለው በሃይማኖት ሥርዓት እና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ አንድ ሰው ገዳም ገባ ሲባል ዓለማዊ ኑሮን በመተው መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር መቀመጥ ጀመረ ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ"(1997፣22) ገዲም የሚለውን ቃል እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡ የላመ የጣመ ሳይቀመስ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብስ፣ ጤዛ ለብሶ ድንጋይ ተንተርሶ፣ ድምፀ አራዊትን፣ ግርማ ሌሊትን ታግሦ፣ ከዓለማዊ ኑሮ ርቆ፣ ከሥጋዊ ክብርና ተድላ ደስታ ተጠብቆ፣ ከዕለታዊ ኑሮው ሁሉ ከሰው ሸክምነት ተላቆ፣ እራሱን በእራሱ እየረዳ ዘወትር በፆምና በፀሎት፣ በገድልና ትሩፋት ተጠምዶ የሚኖር የእግዚአብሔር ሰው ማለት ነው፡፡

በገዳም ህይወት የእኔ የግሌ የሚሉት ንብረት የለም፡፡ ሁሉ በማህበር፣ በአንድነት፣ በጸሎት፣ በሥራ እየተጉ ፍጹም የዓለምን ኀላፊነት ተረድተው፣ የማታልፍ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳለች በመገንዘብ ዘወትር በቀኖና ተወስነው የሚኖሩበት ነው፡፡ ይህም ህይወት የቅዱሳን መኖሪያና ጸጋ እግዚአብሔር የማይለይበት ሲሆን በአንጻሩም ከሁሉ የከበደ የአጋንንት ጾር የሚበዛበት ቦታ ነው፡፡ ገዳምና ገዳማዊ ህይወት አስፈላጊ በመሆኑ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አርአያ ሆኖን በገዳመ ቆሮንጦስ በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ተቀመጠ (ማቴ 4÷1-11) ፤ፈታኝ ዲያብሎስንም ድል አደረገው፡፡ ገዳማዊ ህይወትን የመሠረተልን አምላካችን- አርአያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

በአጠቃላይ ገዳማዊ ማለት "ስለ እኔ ብሎ ቤቶቹን ወንድሞቹን፣ እህቶቹን፣ አባቶቹን፣ እናቶቹን፣ እርሻን የተወ ሁለ መቶ ዕጥፍ ይቀበላል፤ የዘላለም ህይወትም ያገኛል" (ማቴ

19፡29) የሚለውን አምላካዊ ቃል ተከትለው ሀብት-ንብረትን፣ ወዳጅ ዘመድን ትተው፣ ከዓለማዊ ህይወት ተገልለው የሚኖሩ መነኮሳትን ያመለክታል፡፡ ይህንን ሁሉ ትተው በመመንኮስ እንደ አብነት የሚጠቀሠው በዘመነ ብሉይ እና በሀዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሶ የምናገኘው የሄኖክ ታሪክ ነው (ያረጋል፣ 1993፡185)፡፡

ከጥቅሶቹ የምንረዳው ምንኩስና ራሳቸውን ለፈጣሪ ለማስገዛት እና ለማቅረብ፣ ዓለማዊውን ህይወት ንቀው ሀብት-ንብረታቸውን ትተው፣ አለን ከሚሏቸው ሁሉ ተለይተው፣ አምላካቸውን ለማገልገል በበርሀ ጎጆ ቀልሰው፣ አራዊትን ሳይፈሩ፣ ለሚመገቡት፣ሳይጨነቁ የሚኖሩት ህይወት መሆኑን ነው፡፡

### 2.1.1.1 የገዳም ህይወት ጅማሮ

የገዳም ህይወት (ምንኩስና) ከተጀመረ ብዙ አመታትን እንዳስቆጠረ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡በብሉይ ኪዳን ዘመን በብህትውና የሚኖሩ እንደ መልከ ፀዴቅ እና ኤልያስ ያሉ አንዳንድ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ሄኖክም ልጆች ከወለደ በኋላ እንዲህ ያለው ኑሮ አጥጋቢ ሆኖ ስላላገኘው የብህትውና ኑሮ ጀምሯል (ያረጋል 1993 ፣185)፡፡ ሄኖክ በዚህ አለም ሚስት አግብቶ ፣ልጅ ወልዶ እና ንብረት አፍርቶ የእግዚያብሄርን መንገድ በመከተል ይኖር እንደነበር በዘፍጥረት፣ 5 ፣ 21-25 ላይ ተጠቅሷል፡፡ (ያረጋል 1993 ፣185) ደግሞ በዘመነ ብሉይ ሄናክ የዚህን አለም ህይወት ከጀመሩ በኋላ (ሚስት አግብቶ እና ልጆች ወልዶ መኖር ከጀመሩ በኋላ) ለሚመንኑ እና ለሚመነኩሱ ሰዎችአብነት ሆኗል፡፡ምንም እንኳ ብህትውና ከቀድሞ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም ምንኩስና በሀዲስ ኪዳን የተጀመረ የህይወት መንገድ ነው ይላሉ፡፡

ባህታዊ ማለት "ባተሌ ፣ብቸኛ ከሰው ተለይቶ በበአት (ዋሻ) ተከቶ ዘግቶ ለብቻው በዱር በገደል በተራራ የሚኖር መናኝ እንደሆነ  ደስታ ተክለወልድ (1962 ፣262) ይገልፃሉ፡፡ምንኩስና ደግሞ በድንግልና እና በንፅህና ሆኖ በፀሎት ፣ በስግደት ፣ በትምህርት ፣ በአገልግሎት ተወስኖ መኖር ማለት ነው፡፡ የሁለቱ ልዩነትም ብህትውና ከሰው ተለይቶ በብቸኝነት መኖር ሲሆን ምንኩስና ግን ከሌሎች መነኮሳት ጋር በገዳማዊ አገልግሎት የሚኖርበት ህይወት ነው፡፡

ከሶስተኛው እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ምናኔ ምንኩስና እና  ገዳማዊ ህይወት በግብፅ ፣ በሶሪያ፣  በፍሊስጤም እና በሊባኖስ በረሀዎች የተስፋፋበት ወቅት እንደነበር መረጃዎች የመለክታሉ፡፡ (ያረጋል ፣ 1993 ፣188 -189 ) የምንኩስና ማዕከልም ግብፅ እንደነበረች ጨምሮ ይገልፃል፡፡

ገዳማዊ ህይወት ስርአት ባለው መንገድ በአባ እንጦንስ አማካኝነት የተጀመረ ሲሆን ፤ የእርሱ ደቀ መዝሙር የነበረው ጳኩሚስ ደግሞ ይህን ህይወት ወደ ተሻለ ደረጃ አሸጋግሮታል። (ሉሌ 1997፣ 60-61) ጳኩሚስ ገዳማውያኑ የሚተዳደሩበትን ህግና ስርአት ከማውጣቱም በላይ ገዳማውያኑ በእለት ተእለት ህይወታቸው የሚከተሏቸውን ሀይማኖታዊ ደንቦችን እና ጋርዮሻዊ ኑሮን አስተዋውቀዋል (Knowles, 1966, 3, Chadwick, 1968 , 6):: ስለሆነም የምኩስና ህይወት መስራቹ ቅዱስ እንጦንስ ሲሆን ፤ የመነኮሳት የአንድነት ህይወት (የጋራ ስራ፣ የጋራ ማዕድ ፣ የጋራ ፀሎት አ፡በአጠቃላይ ጋርዮሻዊ ህይወት መስራቹ ደግሞ ጳኩሚስ ነው።

ገዳማዊ ህይወት በዚህ ሁኔታ ተጀምሮ የተስፋፋ ሲሆን በገዳም ህግና ስርአት መሰረት ወንድ እና ሴት መነኮሳት በጋራ መኖር ፣ በጋራ መፀለይ በጋራ መስራት እና መመገብ ፤ በአጠቃላይ በአንድ ገዳም ውስጥ የጋርዮሽ ኑሮ እንዲመሩ አይፈቀድላቸውም። (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን ትናንት እና ዛሬ ፣ 1977 ፣22) ይሁን እንጂ ወንድ እና ሴት መነኮሳት በአንድ ፃድቅ መጠርያ ገዳም ለየብቻ መኖር እና ህይወታቸውን መምራት እንደሚችሉ ጨምሮ ያስረዳል።

#### 2.1.1.2 የገዳም ህይወት ጅማሮ በኢትዮጵያ

የገዳማዊ ህይወት በመጀመሪያ ሰሜናዊ ክፍል በትግራይ ዋና ከተማ በነበረችው በአክሡም አካባቢ የተወሰነ ነበር። የመጀመሪያው የገዳማውያን ማኅበረሰብ በ5ኛው ምእት ዓመት ዘግየት ብሎ ከኢያሪኮ ባህር አካባቢ (ምናልባትም ከሶሪያና ከግብጽ በመጡ ዘጠኝ መነኮሳት እንደተመሠረተ ይነገራል (ያረጋል 1993፣185) ፡፡ከዚሁ የተቀደሰ መንፈሳዊ ህይወታቸው የተነሣ ተስዐቱ ቅዱሳን ተብለዋል። በነዚሁ ቅዱሳን ከተመሠረቱት ገዳማት በጣም ታዋቂ የሆነው ደብረ ዳሞ የተቋቋመው ከተስዐቱ ቅዱሳን መካከል ስማቸው ጎልቶ በሚታወቀው ቀድሞ ዘ-ሚካኤል ኋላ ላይ አቡነ አረጋዊ በሚባሉት ቅዱስ አባት ነው።(ሉሌ 1997፣30)።

የተወሰኑ ገዳማት በሁለቱ ነገሥታት በአብርሀና አጽብሀ /4ኛው ምእት ዓመት/ እንደተመሠረቱ ይገለጻል። ከዚያ ዘግየት ብሎ በገዳማት ምሥረታ የታወቁ ሌሎች ነገሥታት መኖራቸው ይነገራል (ያረጋል፣1993፣189)። በከፍተኛ ደረጃ የታወቁት አበው እስከተነሡበት እስከ 13ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ስለ ገዳማዊ ህይወት የሚያስረዱ ሰነዶች ብዙ አልነበሩም።የደብረ ዳሞው የአቡነ ዮሀኒ መንፈሳዊ ልጅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ በ1287 ነው ያረፉት። የመነኮሱት እስከ ዛሬም የገዳማዊነት ማእከል በሆነው በደብረ ዳሞ ነው። አቡነ ኢየሱስ ሞአ በ1248 ወደ ቤተ ዐምሀራ፣ ማለትም የእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ወደ ሚገኝበት

ወደ ሀይቅ ተጉዘው የደብረ ሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳምን መንፈሳዊ ት/ቤት አቋቋሙ። ገዳሙ ከአፄ ይኩኖ አምላክ (13ኛው ምእት ዓመት) ጋራ የቀረበ ግንኙነት ነበረው። የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ደቀመዝሙርና በጣና ሀይቅ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መሥራች እንደ ነበሩት እንደ አቡነ ህሩይ አምላክ ያሉት ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶች ከገዳሙ የተገኙ ወይም በገዳሙ መንፈሳዊ ህይወት እየተሳቡ ከሌላ ቦታ የመጡ ናቸው (ዳኛቸው ፣1999፣133፣ ሉሌ፣1997፣60-61፣ አሳምነው፣2000፣56)

በጣና ሀይቅ ደሴቶች ዙሪያ የገዳማዊ ህይወት ምሥረታ የተጀመረው በ14ኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመን ነው። በጣም ታዋቂ ከሆኑት የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ተክለሃይማኖት ናቸው። (ዳኛቸው ካሳሁን 1999፣ ተክለሃይማኖት ወደ ምዕራቡ የሀገሪቱ ክፍል በመሄድ በ13ኛው ምእተ ዓመት መጨረሻ በሸዋ ውስጥ የደብረ ዐስቦን (ኋላ በ1445 ደብረ ሊባኖስ የተባለውን) ገዳም አደራጅተው አቋቁመዋል። ብዙ ገዳማትን በመመሥረት እጅግ ታዋቂና ተደማጭነት የነበራቸው ሌላው መነኩሴ በትግራይ ገር አልታ ውስጥ የነበሩት የታላቁ መናኝ የአቡነ ዳንኤል የእህት ልጅ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ /1273-1352/ ናቸው (ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም፣1999፣133-134)።

ከዚህ በኋላ በገዳማዊ ህይወት የሀረግ አወራረድ ሁለት ታላላቅ ሀዋርያዊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት በዋነኛነት ወደሸዋ እና ከዙያም ራቅ ወዳለ ደቡብ እንደዚሁም በምዕራብና በሰሜን ሲሰማሩ፣ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ደቀ መዛሙርት ደግሞ በዋነኛነት ወደ ሰሜን / ወደ ትግራይና ኤርትራ / እንደዚሁም ወደ ምዕራቡ ክፍል ተጉዘዋል።ከአቡነ ተክለሃይማኖት ታዋቂ ደቀ መዛሙርት መካከል የደብረ ዐስቦው ሦስተኛው ጸባቴ / አስተዳዳሪ/ አቡነ ፊሉጶስ፣ የደብረ ብሥራቱ አቡነ ዛና ማርቆስ / በሰሜን ሸዋ ሞረት/ እና አቡነ አኖሬዎስ ይገኙበታል (ያረጋል፣ 1993፣188-189፤መልአከ ሰላም፣1999፣173)።

በ16ኛው ምእት ዓመት ደግሞ በጣም ታዋቂ የነበሩት የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪዎች አቡነ ንባቆምና አቡነ ዮሀንስ ናቸው። የሀይቅ እስጢፋኖስን ገዳም ስናነሣ በሀይቅ የሚገኙትን የቅዱስ ጊዮርጊስና የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያንን የመሰረቱት አቡነ ሰላማ ዘ አዛብ ሁለተኛ እና አፄ ዴልናኦዴ ናቸው። ይሁን እንጂ የነበረውን ቤተክርስቲያን ወደ ገዳምነት እንዲቀየር ያደረጉት በ13ኛ ክፍለ ዘመን የመጡት አቡነ እየሱስ ሞአ ናቸው። (ዳንኤል 1999፡9-11) በዚህችም ገዳም በርካታ ቅዱሳን መንፈሳዊ ትምህርት ተምረዋል። ከተማሩት

ቅዱሳን መካከል ተክለ ሃይማኖት፣ አባ በጸሎተ ሚካኤል፣ አቡነ ጊዮርጊስ ዘ ጋሥጫ፣ አቡነ ገብረ ናዝራዊ፣ አቡነ ሔዝቅያስ፣ አቡነ እስጢፋኖስ ይጠቀሣሉ፡፡ (ሥርግው 1977፡112-13)፡፡

የሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አስተዳዳሪ የማዕረግ ስም "ዓቃቤ ሰዓት" ይሰኛል፡፡ ይህ ስም ተገቢነቱን እንደያዘ እስከ 16ኛው ምእት ዓመት ቆይቷል፡፡ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ እንደ ኢትዮጵያ ትውፊት ከጻድቁ ከተክለ ሃይማኖት ዕረፍት በኋላ ወይም ከ16ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ "ዕጨጌ" ይባላል (ዳኛቸው ካሳሁን፣1999፣173-174)፡፡

በራሳቸው ተነሣሽነት በገዳማት ምሥረታ የታወቁ ሴቶች መነኮሳትም አሉ፡፡ ለምሳሌ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ /15ኛው ምእት ዓመት/፣ ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ፣ ቅድስት ቆራጣ ወለተ ጴጥሮስ /17ኛው ምእት ዓመት/ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 2.1.2 ተረክ

ተረክ የሰው ልጅ የፅሁፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ የነበረ፣ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ስለ አለም አፈጣጠር፣ ስለነገሮች አመጣጥ፣ ስለእምነቱ፣ ስለባህሉ እና ስለማንነቱ ለመግለፅ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ተረክ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው፣ በማንኛውም ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኝ፣ ዘመንና ባህል የሚሻገር፣ በሁሉም የኪነጥበብ ቅርጾች የተለያዩ ጉዳዮችን ማስተላለፍ የሚችል፣ በቃል ወይም በፅሁፍ፣ በቅርጽ ወይም በስዕል፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ በዝርው ወይም በግጥም ቅርፅ ሊቀርብ የሚችሉ በርካታ የማህበረሰቡን ሁነቶች የሚያሳይ መግባቢያ መንገድ ነው (Barthes 1975: 237, Degh, 1972: 54) ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ (ቴዎድሮስ 2001፣ 259-260)፡፡ የተረክን ምንነት እንደሚከተለው ያስረዳሉ ፡፡ "ተረክ ታሪኩን፣ ትረካውን፣ ታሪኩ የሚቀርብበትን ሁኔታና መንገድ ሁሉ ጠቅልሎ የሚይዝ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በሰፊ አገባቡ ተረክ በቃል አልያም በፅሁፍ ሊቀርብ፣ በግጥም ወይም በዝርው ሊተረክ ይችላል፡፡ ከዚህም አልፎ ሊዘፈን፣ ሊተወን፣ ሊደነስ፣ ሊሳል፣ ሊቀረጽ፣ በተለያዩ መንገዶች ሊከወን የሚችል ቅርጽ ነው ፡፡

ተረኮች በተለያየ ቅርጽ ይቀርባሉ ካልን የዚህ ጥናት ትኩረት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን (oral prose narratives) ማጥናት ነው፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረክ የስነቃል አንዱ ክፍል ሲሆን ግጥማዊ ባልሆነ መልኩ በቃል የሚተረክ፣ ተለጣጣቂነት ያላቸው ድርጊቶችና ሁነቶች የሚፈፀሙበት፣ የድርጊቱ ተሳታፊ የሆኑ ገጸ ባሕርያት የሚገኙበት፣ እንዲሁም ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ቦታና

ጊዜ የሚያመለክት ታሪክ ነው (Oring, 1986: 122)፡፡በተጨማሪም ተረክ የግለሰብን ወይም የአንድን ማህበረሰብ ልምድና ገጠመኝ በወጉ የተደራጁ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም እንዴ የተከሰተ ሁነትን ማሳያ ወይም ማቅረቢያ መንገድ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ተረኮች የተራኪውን ማህበረሰብ አመለካከት የያዙና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ተረኮች በማጤን የማኅበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና፣ ወዘተ. ማወቅ ይቻላል በዘመናችን በተለያዩ ቤተ እምነቶች የተለያየ ይዘት ያላቸው ተረኮች ይተረካሉ፡፡ እነዚህ ተረኮች ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ምዕመኑን ለማስተማር እና የእምነቱን ስርዓት ጠብቆ እንዲጓዙ ለማድረግ የሚፈጠሩ እና የሚከወኑ ናቸው፡፡ (Sims, 1963: 168) ፡፡

በተመሳሳይ መልክ (Deign1972፣54) ተረክ (Oral narratives) በማንኛውም ማህበረሰብ እንደሚቀርቡ ሁሉ በየትኛውም አካባቢና ማህበራዊ ሁኔታ (Social condition or climate) ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይናገራሉ፡፡በተጨማሪም የአንድን ማኅበረሰብ ተረክ ለማጥናት ሲፈለግ ትኩረት መደረግ ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ (Deign 1972፣54) ይገልጻሉ፡፡ እነርሱም በተረኮቹ አማካይነት የሚተላለፉት መልእክቶች ምንድን ናቸው? ለተረኮቹ መፈጠርና መነገር ምክንያት የሆኑት ምን እንደሆኑና ተረኮቹን ተራኪዎቻቸውና ታዳሚዎቻቸው እንዴት አድርገው ይመለከቷቸዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች ተረድተው መልስ መስጠት እንደሚገባ ነው የገለጹት፡፡

ከእነዚህ ሀሳቦች በመነሣት ተረክ የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ የሆነ፣ በዝርው የሚቀርብ፣ የድርጊት ተሳታፊዎች ገጸ ባህርያት ያሉት፣ ድርጊቱ የሚፈጸምበትን ቦታና ጊዜ የሚያመለክት፣ ረጅም ዘመን ያለው፣ ለሰው ስሜት ቅርብ የሆነ፣ ከነባራዊ ዓለም ጋራ በሚስማማ መልኩ የሚቀርብ የሥነ-ቃል አካል ነው ማለት ያስችላል፡፡ Oring በበኩላቸው ተረኮች በድርጊቶችና በሁነቶች የተዋቀሩ የአንድ ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ልማድ ለማስተላለፍ የሚጠቅሙ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ይህም ተረክ የአንድን ማኅበረሰብ ተከታታይ ድርጊት ቃላዊነቱ እንዳለ ሆኖ በተለያየ ቅርጽ የሚቀርብበት ነው ማለት ያስችላል፡፡

ተረክ ቋንቋን መሠረት ያደረገና ቃላዊ ባህርይ ያለው ነው፡፡ ነገር ግን ቃላዊ መሆኑ የተለየ ቅርፅና ባህሪ እንዳይኖረው አያደርግም፡፡ ይልቁንም ከሌሎች የሥነ- ቃል ዘርፎች የሚለይበት የራሱ ቅርፅና ማዕቀፍ አለው፡፡ ይህ ማእቀፍ (Framework) ቃለ ተረክን ሙሉ ትርጉም የሚሰጥና ሥርዓታዊ ያደርገዋል፡፡ Barthes ይህንኑ ጉዳይ በማንሳት ዋናዎቹ የቃል ተረክ

ማእቀፎች ከቋንቋ አንጻር አገነባቡ (Organization) እና ከመቼት አንጻር ያለው ወቅታዊነት መሆናቸውን (Bruner 1990 , 43) ይገልፃል፡፡

ተረኮች ለተለያዩ ሀይማኖቶች እምነትን ለማስረፅ፣ የኃይማኖቶቹን ሥርዓት ተጠብቀው እንዲቆዩና ለትውልድ እንዲተላለፉ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ የተለያዩ ኃይማኖቶች (ለምሳሌ ክርስትና፣ እስልምና፣ ሂንዱ…ወዘተ) የሀይማኖቱን ማዕከላዊ ጉዳይ የሆነውን እምነትን የሚያሰርጹት እና ሀይማኖታዊ እሴቶቻቸውን የሚያፀኑት በተረክ ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ተረኮች በኃይማኖት ቅዱሳን እና ነቢያት የሚባሉትን ሰዎች የህይወት ታሪክ እና ኃይማኖታዊ ተጋድሎ በውስጣቸው የሚይዙ ናቸው፡፡ ይሄንንም ለማረጋገጥ የክርስትና ኃይማኖት መሰረት የሆነውን የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን መፅሀፍት፣ እንዲሁም የእስልምና ሀይማኖት መሰረት የሆነውን ቁርዓንን ማየት ይቻላል፡፡

ተረክ በተለያየ መንገድ ይተላለፋል እነዚህም ቃለ ተረክ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ‹‹የሥነ ቃል ህይወት ›› ብሎ የሚጠራቸው 'Barthed' ቃለ ተረክ በተረት፣ በአፈ ታሪክ፣ በታሪክ፣ በአሳዛኝ ሁኔታ፣ በድራማ፣ በቀልድ፣ በማይም (በድምፅ አልባ ተውኔት )፣ በቀለም የመስታወት መስኮቶች፣ በሲኒማ፣ በቀልዶች ፣ በ ውይይት ይገለፃል፡፡ ከዚህም በላይ በዚህ ማለቂያ የሌለው ልዩነት ስር ትረካ በየእድሜ፣ በየስፍራው፣ በየህብረተሰቡ ውስጥ ይገኛል፤ ተረክ ከሰው ልጅ ታሪክ ጀምሮ የሚጀምር ሲሆን የትም ሆነ ማንም ተረክ የሌለው ህዝብ የለም፡፡ ሁሉም መደብ፣ ሁሉም ሰብዓዊ ቡድኖች፣ የራሳቸው የሆኑ ተረኮች አሏቸው ይላል፡፡

#### 2.1.2.1 የተረክ አይነቶች

ተረኮችን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይመድቧቸዋል፡፡ ምሁራዊ ክርክሩም ቢሆን ከትርጓሜው ይልቅ በምደባዎቹ ላይ ከፍ ብሎ ይታያል፡፡ ምሁራኑ ለምደባቸው መሰረት የሚያደርጉት በዋናነት ከቃለ ተረኩ ቅርፅ፣ ጭብጥ እና ባህርይ በመነሣት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተለያዩ ምሁራን የሚሰጡት ምደባዎች ወጥ ስምምነት የሚያመጡ አይደለም፡፡ ቃለ ተረኮችን (ሰለሞን፣ 2010 ፣86) ተረት አፈታሪክ፣ ሚትና ግለሰባዊ ትረካዎችን ዋና በማለት ይከፍላቸዋል (Oring. 1986) የቃለ ትረካ ዘርፎች የሚላቸውን 15 ዘርፎች ከጠቀሱ በኃላ ሚት አፈታሪክና ተረትን በዋናነት ወስደዋቸዋል ፡፡

#### *2.1.2.1.1 ሚት*

ሚት ማለት የሰው ልጅ አካባቢውን እና ተፈጥሮውን ለመረዳት፣ በአዕምሮው የሚመላለሱ የማንነት እና የምንነት ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚረዳ መንገድ ነው፡፡ ይህንን በማስመልከት (ቴዎድሮስ 2001፣ 67-68) ሚት የሰው ልጅ የስሜት ህዋሱን ከሚያግደው አድማስ አምልጦ በመውጣት በሜታፊዚክሳዊ ሀይል ዓይን ዓለመ ዓለማቱን ለማየት፣ ለማወቅ፣ ያወቀውን ለመበየንና ለመቆጣጠር የሞከረበት ፍልስፍናው ነው፡፡… ሚት በምርምር የማይደረስበትን፣ በተግባር ሙከራ የማይረጋገጥን ልዕለ አካላዊ ጉዳይ በመንፈስ፣ በምናብ ኃይል የምናቀርብበት ስርዓት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

ሚት ማህበረሰቡ በአካባቢው የሚያስተውላቸው ተፈጥሯዊ ሁነቶች ያላቸውን ባህሪይ፣ አፈጣጠራዊ ሂደት፣ ከየት-መጣነት መልስ ለማግኘት የሚጥርበት ነው፤ የአካባቢውን የባህል እሴት መሠረት በማድረግ ለራሱ የአስተሳሰብ አድማስ ለዓለም ያለውን ግንዛቤ የሚገልጽበት የተረክ አይነት ነው፡፡ሚት የሰው ልጅ በአእምሮው አሰላስሎ ምላሽ ሊሰጣቸው ያልቻለው ጉዳዮችን ምላሽ የሰጠበትና በነዚህ ምላሽ አልባ ጉዳዮች ምክንያት ውል አልባ የነበረውን ዓለም ውል የቋጠረበት አቢይ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ይህ የሰዎች የወል ሀብት የሆነ ሚት በተረክ የተገነባ ሲሆን የሰዎች ማን ነኝ? ወደየት እሄዳለሁና የተፈጥሮ ሥርዓት እንዴት ይመራል? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን የመለሱበት ሚት ባለበት ማኅበረሰብ ቅቡል በመሆኑ የሰዎችን የአእምሮ ክፍተትም ይሞላል፡፡ የሰው ልጅ የሚኖርበትን ማህበረሰብ ሚታዊ ተረክ አክብሮና በማመን ተቀብሎ ለምኞቱና ለፍላጎቱ መነሻና መድረሻ እየተገለገለበት ዘመን ይሻገራል፡፡

የሚት አይነቶች ተብለው በተለያዩ ምሁራን ተመድበው ከምናገኛቸው መካከል ሀተታ ተፈጥሯዊ ሚት (creation myth) ፣መንፈሳዊ ሚት (Deity myth) ፣የባህል ታጋይ ሚት (myth of culture heroes and esoteriological)፣ ጊዜያዊና የዘላለማዊ ሚት (Myth of time and eternity) ፣የዘመናዊ ማህበረሰብ ሚት (Myth of modern society)፣ ጂኦሚቲዮልጂ geomethology ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡ ሰለሞን (2007፣101)፡፡

ሚቶሎጂ የሚታዊ ተረኮች ስብሰብና ሚቱ የተመሠረተበትን ልማድ እንዲሁም ሚቶቹ የሚጠኑበትና የሚመረመሩበት መስክ መጠሪያ ነው፡፡ ሚቶሎጂ በየወቅቱ አድማሱን እያሰፋ ሌሎች ሙያዎችን በአንድ ቀንበር ለማስተሳሰር ችሏል፡፡ ቴዎዴሮስ ገብሬ (2001) ይህን

አስመልክተው በመፅሀፋቸው ሚቶሎጂ በየትኛውም ዘመን የሚኖር በሁሉም ስፍራ የሚፈስ ታልቦ የማይነጥፍ ተጠልቆ የማያልቅ ተቀድቶ የማይደርቅ ታላቅ ወንዝ ነው ለማለት እንችላለን። ሚት የነገረ መለኮት የፍልስፍና ፣ የሥነ ልቦና፣ የአንትሮፖሎጂ ፣ የታሪክ፣ የሥነ ፅሁፍ ወዘተ የወል ምንጭ፣ የጋራ ግዛት ነው ይላሉ።ሚቶሉጂ ከላይ የተጠቀሱትንና የሌሎችም ሙያዎች ጉዳይ ነው ።ስለዚህም ሃይማኖታዊ ሚታዊ ክዋኔዎችና ሚታዊ ተረኮችን መተርጎምና መፈከር ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

### *2.1.2.1.2 አፈ_ታሪክ*

አፈታሪክ በማህበረሰብ ውስጥ የተከሠተ እውነተኛ ታሪክ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው። በመሆኑም ተስተላልፎው በአንድ ትውልድ ያልተገታ ነው። አፈ ታሪክ ቃላዊ በሆነው ተስተላልፎው አድማጩን በማስተማር፣ በማንቃት፣ወይም ለአዴማጩ መረጃ በመስጠት፣ ታሪክ በማሳወቅ ወዘተ… ረገድ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ድርሻ አለው።

እንደ Bascom (1965፣6) ገለጻ አፈ ታሪክ በእውነት ላይ የሚመሠረት፣ ልማዳዊ የሆኑ ነገሮች የሚመረመሩበት፣ ገጸ ባህርያቱ ሰዎች የሆኑ፣ በእራሳቸው የሚቆሙ ሳይሆኑ እራሳቸውን አሳልፈው ሰዎችን ነጻ የማውጣት ባህሪን የተላበሱ፣ ገጸ ባህርያቱ የሚተውኑበትን መንፈሳዊ ፣ስጋዊ ጉዳይም የሚያነሣ፣ በዚህኛው ዓለም የተፈጸመ የቅርብ ሀላፊ ጊዜ ያለው፣ መቼቱ አንዳንዴ የሚታወቅ፣ እውነትነት ያለው፣ ስለ ሰዎች ፣ ስለ ቦታዎች ስለ ታሪኮች እና የተለያዩ ክስተቶችን የሚተርክ ማለት ነው።አፈ ታሪክ በጊዜና በዘመን በሚታወቁ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው በቃል የሚነገሩ ታሪኮች መጠሪያ ነው። ይኸው አፈ ታሪክ ጽሕፈት ባልነበረበት ዘመን የነበረውን ታሪካዊ ሁነት ዘመን እንዲሻገር ያስቻለ በቀላሉ በንግግርና በሌሎች የመከወኛ ስልቶች የተስፋፋና ታሪክን እና ቅርስን ጠብቆ ለማኖር እንዲሁም ህብረተሰብ የእኔ የሚለውን የጋራ ማንነት እንዲገነባ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለ ነው። በታሪክ የሚታወቅ ጊዜ ስፍራና ሁነትን መነሻው በማድረግ የሚነገርና የሚፈጠር መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ገልፀዋል።

ሰለሞን (2007 ፣94) አፈ ታሪክ (Legend) በአንድ አካባቢ ተከስቷል ተብሎ በሚታመን ያለፈ ታሪክ ሊይ ተመስርቶ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚነገር ወይም በፅሁፍ የሚተላለፍ የቃል ትረካ ዓይነት ነው። ይህ ቃለ ትረካም ታሪኩ በተፈፀመበት ቦታ ታሪኩ ተፈፀመ ተብሎ በሚነገርበት ወቅት የተፈፀመው ድርጊት፣ የፈፃሚው ሰው ስም ወዘተ በአካባቢው ተጨባጭና እውነተኛ ታሪክ ማኅበረሰቡ እውነት ነው በሚል የሚቀበለው እንደሆነ ያስረዳሉ።

### 2.1.2.1.3 ተረት

ተረቶች በሳይንሳዊ መንገድ ሊረጋገጡ የማይችሉና በሰዎች አእምሮ ውስጥ ተአማኒነት የሌላቸው ፈጠራዊ ድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ ፍሰታቸውን ጠብቀው የሚቀርቡበት የተረክ አይነት ነው። ተረት በሴራ ያልተወሳሰቡ ልማድና ቀጥተኛ የሆኑ ታሪኮችን፣ ዓለም ዓቀፋዊ ባህርይ ያላቸውን ታሪኮች የሚገለፅና በውስጡም የሚገኙትን ገጸ ባህርያት፣ አጋጣሚዎች፣ ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦችና የድርጊቱ ገጽታዎች እንደ ዋና መሠረታዊ ጭብጥ የሚወስድ ነው።ከዚሁ ጋራ በተያያዘ Bascom (1965፣6) ተረቶች ብዙውን ጊዜ የራሳቸው የአቀራረብ ሥርዓቶች እንዳሏቸውና በሚተገበሩበት ጊዜም በተረቱ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ መመሪያዎችን በማምጣት አድማጩም ተረቶቹ ተጀምረው እስኪጨረሱ ድረስ ሥርዓት ባለው መልኩ እንደሚከታተሉ ያስረዳሉ እንደ Bascom አገላለፅ የተረቶች በአንድ መደብ መመደብ ይዘትን መሠረት ያደረገ ነው።ሁሉም ተረቶች ተቀራራቢ ባህርይ አላቸው። ይህም የሆነበትን ምክንያት (Finnegan 1970፣363) ስትገልፅ በአንድ ማህበረሰብ አፈ ታሪክ ወይም ተረት ናቸው ተብለው የሚነገሩት በሌላ ማህበረሰብ ሚት ወይም ተረት ተብለው መነገራቸው ነው። የዚህ ምሳሌ ዮሴፍ ቦኪ የተባለ አጥኚ በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ከፎክሎር ትምህርት ክፍል ጥናቱን ባደረገበት ጊዜ በጥናቱ ወቅት ካጋጠሙት ችግሮች መካከል የጠቀሠውን ስናንሣ። አጥኚው በሄደበት ማህበረሰብ ተረክን በተረክነቱ ከመግለጽ ይልቅ እንደ ተረት የመተረት እና ተረክ የሚለውን ቃልም ከነጭራሹኑ ያለመረዳት ነገር እንደ ነበር ይገልጻል።

ከእነዚህ ከሶስቱ አከፋፈሎች በተጨማሪ የአንድን ግለሰብ ገጠመኝ መሰረት አድርገው የሚተረኩ ተረኮች አሉ Bascom, (1965: 4)። እነዚህ ግለሰባዊ ገጠመኞች ላይ ተመስርተው የሚተረኩ ተረኮች በተራኪው ዘንድ እውነተኛ ተደርገው ይቆጠራሉ። የተለያዩ ምሁራን እነዚህን ግለሰባዊ ተረኮች "True experience stories" Degh, (1972: 77)፣ "Personal experience stories" ወይም "Memorate" በማለት በተለያየ ስያሜ ይጠሯቸዋል። ግለሰባዊ ተረኮች የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት ህይወቱ የሚገጥሙትን ገጠመኞች መሰረት አድርገው የሚተረኩ ናቸው። እነዚህም ገጠመኞች የስራ እና የጉዞ ማስታወሻዎች እንዲሁም የህይወት ታሪኮች ሊሆኑ ይችላሉ (Degh, 1972: 78)። እነዚህ ግላዊ ተረኮች በአተራረክ ስልታቸውና በሚያነሱት ሀሳብ ግለሰቡ የበቀለበትን ማህበረሰብ እምነት እና ማንነት ያንፀባርቃሉ።

በአፈታሪክና ሚት መካከል ያለውን ድንበር ለመለየት ጥናት ያደረጉት Bascom በአሜሪካ ፎክሎር ማህበር ጆርናል ባሳተሙት The Form of Folklore: Prose Naratives በሚል

ባጠኑት ጥናታቸው በአፈ ታሪክና በሚት መካከል አሉ ያሏቸውን ድንበሮች አሳይተዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ በሚት፣ በአፈታሪክና በተረት መካከል ያለው ልዩነት በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡-

| ቅርፅ | ተአማኒነት | ጊዜ | ቦታ | ጠባይ | ገፀባህርያት |
|---|---|---|---|---|---|
| ሚት | እውነት | በጣምእሩቅ | የተለያዩአለማት | የተቀደሰ | ሰዎችያልሆኑ |
| አፈ ታሪክ | እውነት | የቅርብ እሩቅ | የምንኖርበትአለም | የተቀደሰ ወይም አለማዊ | ሰዎች |
| ተረት | ልቦለድ | ማናቸውም ጊዜ | የትም ቦታ | አለማዊ | ሰዎችም ሰው ያልሆኑም |

በባስኮም አገላለፅ መሠረት ሚት  እውነት የሆነ በጣም የሩቅ ዘመን መቼቱ በምድር እና ከምድር ውጪ በሆኑ ዓለማት የተቀደሰ ሰውና ሰው ያልሆኑ አላባዎች ያሉት ነው፡፡ በአንፃሩ አፈታሪክ እውነትነት ያለው፣ በዘመን የሚታወቅ፣ በምንኖርበት ምድር ላይ መቼቱን ያደረገ፣ ቅዱስና ዓለማዊ ታሪኮች ያሉት፣ ገጸባህርያቱ ሰው የሆኑ ናቸው፡፡ በእንፃሩ ተረት ልቦለዳዊ መቼቱ የትም ቦታ የሆነ፣ ዓለማዊ ሰዎችና ሰው ያልሆኑ ፍጥረታትን ገጸ ባህርይው ያደረገ ነው፡፡

## 2.2 የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ

### 2.2.1 ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ

ለዚህ ትኛት አጥኚዋ  ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን የምትጠቀም ይሆናል፡፡ ይህንን ንድፈ ሀሳብ ከፎክሎር ውጪ የሶሲዮልጂ እና አንትሮፖሎጂ ምሁራን ይጠቀሙበታል ፡፡የንድፈ ሀሳቡ ማእከላዊ ሀሳብ ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ የሚገነባቸውን ልዩ ልዩ ተቋማት እንደ ሥርዓትና ግብዓት በመውሰድ ማህበረሰባቸውን በአዎንታዊነት ለመገንባት ያላቸውን ሙያ ወይም ተግባር ማጥናት ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ቃላዊም ሆነ ቁሳዊ ባህል መጠናትና መመርመር ያለበት በማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ መሰረት በማድረግ ነው (Sims, 2005:174)፡፡ በመሆኑም በዋናነት ገዳማውያኑ ተረኮቹን ለምን አገልግሎት ያውላቸዋል? በገዳማውያኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እና ለገዳሙ ስርዓት ተረኮቹ ምን አገልግሎት አላቸው?  በተጨማሪም

ተረኮቹ የሰዎችን ስነምግባር ከማስተካከል አንፃር ምን ይመሳላል? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ስለሆነ ነው፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ሀይማኖታዊ ፎክሎሮችን ለማጥናት ከሚያገለግሉት መስኮች አንዱ መሆኑን Dorson (1972: 25) ያስረዳሉ፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ ፎክሎሮችን ለማህበሩ ምን እና እንዴት ይጠቅማሉ የሚለውን ማጥናት ያስችላል፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን ከሰው ልጅ አካል ጋር አቆራኝቶ ያየዋል፡፡ በሰው ልጅ አካል ውስጥ አጥንቶች፣ ጡንቻዎች እና ሌሎች ክፍሎች በተናጥል ሳይሆን በጋራ የሰውን ልጅ እንደሚያኖሩት ሁሉ፤ የተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች በጋራ በመሆን ትክክለኛውን ማህበረሰብ ይፈጥራሉ፡፡የተግባራዊ ትወራ Functional Approach ምልከታው በተናጠል ያለ ማህበራዊ መዋቅሮች ለትክክለኛ ማህበረሰብ መገንባት ያላቸውን ጥቅም ማጥናት ነው፡፡

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ እንደ ቤተሰብ፣ የእምነት ተቋማት፣ የፍትህ ተቋማት፣ ማህበራዊ ተቋማት በመቀናጀት አዎንታዊ ጥቅም ያለውን ማህበረሰብ ይፈጥራሉ፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ይህንን አዎንታዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ተቋማቱ ያላቸውን ጥቅም ይመረምራሉ፡፡ ይህ አይነቱ ንድፈ ሀሳብ የጋራ ድክመቶች አሉት፡፡ ሰለሞን (2007 ፣76)፡፡ የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ከማህበራዊ መዋቅር ጋር ያለውን ዝምድና በፎክሎር ባለሙያዎች ትንተና መሠረት ሲያስረዱ ማህበራዊ መዋቅሮች ባላቸው ጠቀሜታና ሚና ላይ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ፈቃደ (1992 ፣ 17) እንደገለፁት እ.ኤ.አ በ1930ዎቹ ዓመታት፣ የብሪታንያ የሥነ ሰብእ ምሁራን የአፍሪካ ሥነ ቃል፣ ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ እንሰበስባለን ብለው ጀመሩ ፡፡የእነሱ የአስተሳሰብ ፈለግ "መዋቅራዊ ተግባራዊ" (Structural Functionalism) ይባላል፡፡ የዚህ ፈለግ ዋና ዓላማ በየጊዜው ያሉትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ፣እና ባህላዊ ሁኔታዎች ማጥናት ነው፡፡

ፎክሎር ይህንን ንድፈ ሀሳብ ወደ ራሱ ሲያመጣው በተወሰነ ደረጃ ለራሱ እንዲስማማ አድርጎታል ፡፡ በፎክሎር ጥናት ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በፎክሎሩ ይዘት በፎክሎሩ ባለቤት አጠቃቀም እና በሚሰጠው ትርጉም ላይ ተመሥርቶ ፎክሎሩን ለመተንተን የሚያስችል ግኝት የሚያመጣ ንድፈ ሀሳብ አድርጎ ነው፡፡ ሰለሞን (2007 ፣75) ይህ ንድፈ ሀሳብ ለፎክሎር ጥናት ባለሙያው የሚሰጠውን ግልጋሎት አስመልክቶ የጠቀሜታዊነት ንድፈ ሀሳብ አንድ ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ ወይም ለፎክ ቡድኑ

የሚሰጡት ጠቀሜታና በቡድኑ ውስጥ ያላቸው አውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ የዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች ተረቶች ፣ሚቶች ምሣሌያዊ አነጋገሮች እምነቶችና ሌሎችም ሎሮች ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ስነ ልቦናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ማሟላት ይኖርባቸዋል የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሲሆን ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ ምን አይነት ትርጓሜና ጠቀሜታ አለው? የሚለው አብይ ጥያቄያቸው ነው፡፡በማለት ይገልፃሉ፡፡

የአንድ ማህበረሰብ ፎክሎሮች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ስርዓቶች፣ ህይወት የሚመራበትን መንገድ፣ መልካም ምግባራትን ያስተምራሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፍቃደ (1991፣ 20) “ስነቃሎች የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሄድ ሥርዓትን ያሳውቃሉ፡፡ በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የህብረትን ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ” በማለት  የፎክሎር ተግባራት ውስጥ አንዱ ማስተማር እንደሆነ አስፍረዋል፡፡

ሁለተኛው የፎክሎር ተግባር የማምለጫ ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር ከተወሰኑብን እና በባህል ምክንያት ከታገድንባቸው ሥርዓቶች ማምለጫ ነው፡፡ ፎክሎር ከአሰልቺና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች እንድናመልጥ ያደርገናል ፡፡  ፈቃደ  (1991፣ 20) በመሆኑም የሰው ልጅ በፎክሎር በዙሪያው ከሚገኙ የማያስደስቱ እና ነፃነት ከሚነፍጉ ጉዳዮች በማምለጥ በውስጡ የራሱን የደስታና የነፃነት ዓለም ይመሰርታል፡፡

ሶስተኛው የፍክሎር ተግባር የመትከል ወይም የመቆጣጠር ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ቅቡል የሆኑ ባህሪያትን የመትከል ወይም የመቆጣጠር ተግባር አለው፡፡ ባህል በተደጋጋሚ ጊዜ አንድን ሰው ወደ ተረጋገጠ የባህርይ መስመር ይወስዳል(Sims, 2005: 176)፡፡ ይህም ማለት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መልካም ከሚባሉ መርሆች የሚያፈነግጥን ግለሰብ በአርፈህ ተቀመጥ ግሳፄ መመለስ ነው፡፡ ፈቃደ ( 1991፡ 20)፡፡ ስለዚህም ማህበረሰቡ ስህተት ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መርሆች ለማጥፋትና መልካም ናቸው ብሎ ወደሚያምንባቸው መስመሮች ለመመለስ፣ እንዲሁም ሰናዮቹን ለማፅናት በፎክሎር ይገለገላል፡፡

የመጨረሻው የፎክሎር ተግባር የማረጋገጥ ወይም የማፅደቅ ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር ስርዓትን በማክበር፣ እነዚህ ድርጊቶች በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው በማድረግ ባህልን የማረጋገጥ ተግባር ይፈፅማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈቃደ (1991፣18) አድንዳሰፈሩት የቡድኑ አባላት በስነቃል አማካኝነት ከልደት እስከሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች

አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወኑ ክዋኔዎችና ተቀባይነት ያላቸው መርሆች ትክክለኛ እና መቀጠል ያለባቸው እንደሆኑ ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ በማቅረብ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማድረግ አቅም አለው፡፡ ነገር ግን የባስኮም ሃሳብ በቀደምት የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አራማጆች ተቀባይነት የነበረው ቢሆንም ትችት እና ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ (Sims, 2005: 176)::

(Bascom 1965 ) የፎክሎር ተግባራትን በአራት መድበው ማስቀመጣቸው ተመራማሪዎች የሚያጠኑት የፎክሎር ዘርፍ በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ ያለውን ተግባር ከመመርመር ይልቅ እርሳቸው ያስቀመጧቸው ተግባራት ላይ መመደብ እንዲተገብሩ ሆነዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ፍክሎር ቢጠናም ባይጠናም ተግባራቱን ባህልን ማፅናት ሊይ የተወሰነ ያስመስለዋል፡፡ ፎክሎር ዘርፈ ብዙ እንደመሆኑ በርካታ ተግባራት አሉት፡፡ ቀደምት ተግባራውያን ሀገር በቀል እምነቶች ሁሌጊዜ የሚያመለክቱት የማህበረሰቡን እምነት ነው፡ ተረቶች ደግሞ በአድማጭና በነጋሪው ምክንያት ማምለጥን ያመለክቱናል በማለት ጠቅላይ ድምዳሜ ያስቀምጡ ነበር፡፡ ሀገር በቀል እምነቶች ሁሌጊዜ የሚያመለክቱት እምነትን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን የወደፊት ህይወት ለመተንበይ እና የሚመጣውን በማሰብ ጥንቃቄ ለማድረግም ጭምር እንደሆነ እነ Sims (2005: 177) ያስረዳሉ ::

### 2.2.2 የስነ ልቦዊ ንድፈ ሀሳብ

ስነልቦና ቀደም ሲል የፍልስፍና ክፍል እንደነበር ይነገራል፡፡ ሆኖም ቀስ በቀስ ከፍልስፍና ነፃ እየሆነ በመምጣት አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡የሰነ-ልቦና ቲዎሪ አነሳስ ከ(1856-1939) ድረስ የነበረውን ሲግመንድ ፍሮይድ የተባለ የስነልቦና ሙሁርን ተከትሎ ነው፡፡ ፍሩይድ የሰው ልጆችን ባህሪ ለመረዳት የሚጠቅም ስነልቦናዊ ትንታኔ ያደርግ ነበር፡፡ በመሆኑም የስነ-ልቦና ዋና ስራ የሰዎችን ባህሪ መረዳት ነው ብሎ ያምናል፡፡ በስነልቦናውያን አይን አለም የግለሰቦች ስብስብ ናት፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብ ደግሞ የራሱ የሆነ ስነልቦናዊ ታሪክ አለው፡፡ ያ ስነልቦናዊ ታሪኩ የሚጀምረው በልጅነቱ ከቤተሰቦቹ ጋር ሲኖር ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ቲዎሪ አራማጆች አንድ ግለሰብ የሚናገራቸው፣የሚፈጽማቸው ነገሮች ሁሉ የልጅነቱ ውጤቶች ናቸው ብለው ያስባሉ፡፡ በተጨማሪም በዖታዊ ግንኙነት ወቅት የግለሰቡ ባህሪ ሙሉ በሙሉ ይገለጣል ይላሉ፡፡

Ritamani Das (2014 ,18) እነደሚገልፁት ስለ አንድ ማህበረሰብ ትክክለኛ ግንዛቤ ለማግኘት አፈታሪኮቻቸው የሚነገሩባቸውን ስነ-ልቦና ማጥናት አስፈላጊ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በተለያዩ የአፌ ታሪክ ገፀ-ባህሪያት አማካኝነት ህብረተሰቡ ባልተጠበቁ ፍላጎቶች እና ተስፋዎች የተነሳ ጭንቀቱን እና ውጥረቱን ይቀንሳል፡፡እያንዳንዱ ማህበረሰብ አባላት እንዲከተሏቸው አስፈላጊ የሆኑ የራሳቸው ደንቦች እና እሴቶች አሏቸው፡፡Ritamani አክለው ሲገልፁ ሰዎች ተረክን እንዲተርኩ የሚያነሳሳቸው ምኞት ነው፡፡ በተረኮቻቸው ውስጥ ምኞታቸው ይሳካል በዚህም ደስተኛ ይሆናሉ፡፡ስለዚህም ከሥነልቦና ቲዎሪ አንፃር ተረት ማጥናት የሰውን ልጅ ባህሪ እና ማህበራዊ ችግር ለመረዳት ጠቃሚ መሆኑን Ritamani Das (2014 ,18) ያረጋግጣል፡፡

ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት ተረኮቹ በሰዎች ስነምግባር ላይ ያለው ፋይዳ ምን እንደሆነ ይመረምራል፡፡ የስነልቦና ንድፌ ሀሳብ ደግሞ የሰው ልጆች ባህሪ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ አንድ ሰው ስነምግባርን የሚማረው ከማህበረሰቡ ነው፡፡ አንድ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ህግ እና ደንብ አለው፡፡ አንድን ተግባር ከስነምግባር አንፃር ጥሩ ወይም መልካም ሲል ሌላውን ደግሞ መጥፎ ስነምግባር በማለት ይመድባል በዚህም ይመራል፡፡ስለዚህም በዚህ ጥናት የማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና ማህበረሰቡ የቱን ስነምግባር ጥሩ የቱን መጥፎ ብሎ እንደሚያስቀምጣቸው ለመረዳት ይህን ንድፌ ሀሳብ አጥኚዋ የምትጠቀም ይሆናል፡፡

### 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ በሸንኮራ ዩሀንስ ገዳም አመሰራረት እና በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩ ተረኮች በሚል ርዕስ ከምትሰራው ጥናት ጋር በቀጥታ የተገናኘ ጥናታዊ ፅሁፍና የታተሙ መፅሀፍት የሉም፡፡ ይሁንና ርዕሰ ጉዳያቸው በአብያተ ክርስቲያናት እና በገዳማት አመሠራረት ታሪክ ጋር ያደረጉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ተረክን እና የአብያተ ክርስቲያናት ምስረታን ጉዳያቸው ያደረጉ ጥናቶችን እና በዩንቨርስቲያችን የተሰራ አንድ ጥናት እናያለን፡፡

መሪማ መሀመድ፡፡(2009)“ የእንጦጦ ሀመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት “ በሚል በአዲስ አበባ ዩንቨርቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ ጽሁፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የድህረ ምረቃ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጋለች፡፡ጥናቱ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሣው ከእንጦጦ ሀመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም አመሠራረት ጋራ

ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች የገዳማውያንና ለገዳማዊ ህይወት የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመርን ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም የፅሁፍ መረጃዎችን በመመልከት ቃለ መጠይቅን እና ምልከታን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም የተለያየ ማጣቀሻ መፀሀፍትን መሠረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በጥናቱ ትንታኔ ገዳሟ ጥንት የነበሯት ታሪኮች፣ ምእመናኑ በገዳሟ ያላቸው አመለካከት፣ የተደረገላቸው ተአምራት፣ የሚነገሯቸው ትንቢቶች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ እንደተቻለ አጥኚዋ ታስረዳለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አጥኚዋ በጥናቷ ተረኮቹ የሚነግሩን ነገሮች ምንድን ናቸው? ቁሶቹስ ያላቸው አገልግሎት ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክራለች፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱን ጠንካራ እና ደካማ ጎን እና ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ተመሳስሎ ስናነሳ ጥናቱ አላማውን ያሣካ ነው፡፡መሪማ  በጥናቷ ቃላዊ ተረኮቹን ተንትናለች ፡፡ቁሳዊ ባህሎቹን መርምራለች፡፡ ያላቸውንም ግንኙነት ለማሳየት ችላለች፡፡ በሌላ በኩል ከስፍራው (ጥናቱ ከተካሔደበት አካባቢ) የተሰበሰቡ ተረኮች፣ ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች፣ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ፣ ከስፍራው የተወሰዱ ፍቶግራፎች፣ ካርታዎች እና የተለያዩ ደብዳቤዎች በአባሪነት ተሰንደዋል፡፡ይህ የጥናቱ ጠነካራ ጎን ሲሆን ተረኮቹ  ከዕምነታዊ ይዘት ውጪ ያላቸው ፋይዳ ላይ  ትኩረት አለመስጠቷን እንደ ድክመት ወስጀዋለሁ ፡፡ የመሪማ ጥናት በገዳም ላይ መመስረቱ፣ ተረኮችን ማጥናቱም ሆነ የመተንተኛ ስልቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ይሆናል፡፡ ነገር ግን የይህ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለየ መሆኑ እና ተረክ ላይ ብቻ በማተኮር በመሰራቱ በተጨማሪም ይህ ጥናት የተረኮቹን ስነምግባራዊ ፋይዳ ማንሳቱ ከእርሷ ጥናት ይለየዋል፡፡

አቤል አሰፋ፡፡ (2008 ዓ.ም)  “የጣራ ገዳም፣ ዋሻ እንድርያስ እና ወይን ዋሻ ተክለሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናትና በዙርያቸው የሚነገሩ ተረኮች“ በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ  የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል  የድህረ ምረቃ  መርሀ ግብር  ያቀረበውን ጥናት ስንመለከ የዙህ ጥናት ዋና ዓላማ በጣራ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ገዳም፣ በዋሻ  እንድርያስ ወይን ዋሻ ተክለሃይማኖት አብያተክርስቲያናት እና በዙርያቸው የሚነገሩ ተረኮችን በማጥናትና በመተንተን በተረኮቹ አማካኝነት ስለ አብያተ ክርስቲያናቱ ምስረታ፣ አብያተ ክርስቲያናቱን ስለመሰረቱ ዋኖች ቅድስናና በአብያተክርስቲያናቱ ስለተፈጸሙ ተአምራት እንዲሁም ስለ ቀዳሚት ሰንበት አስተምህሮ  ተረኮቻቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማተስተላለፍ እንዴት

እንደተገለገሉበት ማሳየት ነበር፡፡ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡የተሰበሰቡት መረጃዎችም በተለያዩ የማጣቀሻ መጻሕፍት አማካኝነት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ከመረጃዎቹ በመነሳት በተሰጠው ትንታኔ መሠረት በጣራ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ገዳም፣ በዋሻ እንድርያስ እና ወይን ዋሻ ተክለሃይማኖት አብያተክርስቲያናት የሚነገሩ ተረኮች የጣራ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ገዳም ሲመሠረት በእግዚአብሔር ፍቃድና በመላእክት አመላካችነት እንደሆነ፣ መስራቹ አቡነ ገላውዳዎስ ለአርባ ዓመታት በስፍራው እንፀለዩ ጸሎታቸው ለመሠማቱ የድንኳናቸው ካስማ በተአምራት እንደለመለመ፣ ገዳሙ አራዊት እንደማይደፍሩት፣ በገዳሙ ውስጥ ሕግጋትን የሚያስፈጽም ነብር እንዳለ በተረኮቻቸው ተገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱን ጠንካራ እና ደካማ ጎን እና ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ተመሳስሎ ስናነሳ አጥኚው ቃላዊ ተረኮቹን ከገዳሞቹ አመሰራረት ጋር አያይዞ ሰፊ ትንታኔን ሰጥቷል ፡፡እነደ መሪማ ጥናት ሁሉ በአቤል ጥናትም ከስፍራው (ጥናቱ ከተካሔደበት አካባቢ) የተሰበሰቡ ተረኮች፣ ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች፣ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ፣ ከስፍራው የተወሰዱ ፍቶግራፎች፣ ካርታዎች እና የተለያዩ ደብዳቤዎች በአባሪነት ተሰንደዋል፡፡ይህ የጥናቱ ጠነካራ ጎን ሲሆን በገዳሞቹ የሚነገሩት ተረኮች ፋይዳ ላይ ትኩረት አለመስጠቱን እንደ ድክመት ወስጄዋለሁ ፡፡ የአቤል ጥናት በገዳም ላይ መመስረቱ፣ ተረኮችን ማጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያም ሆነ የመተንተኛ ስልቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለየ መሆኑ እና የተረኮቹን ስነምግባራዊ ፋይዳ ማንሳቱ ከእርሱ ጥናት ይለየዋል፡፡

ወንደሰን ሞላ፡፡ ( 2007) "በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት " በሚል በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ የቀረበውን ጥናት ስንመለከት የጥናቱ ዋና አላማ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ለገዳሙ እና ለገዳማውያኑ ህይወት ያላቸውን ፊይዳ መፈተሽ፣ መመርመር እና መተንተን ሲሆን ይህን አላማ ለማሳካትም አጥኚው ሰነድ ፍተሻ ፣ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታን መረጃ በመሰብሰቢያ መሳሪያነት ተጠቅሟል፡፡በመጨረሻም በጥናቱ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩት

ተረኮች የገዳሙን ቅድስና በማሳየት፤ የገዳሙ ህግና ስርዓት እንዲከበርና እንዲጠበቅ የማድረግ፣ የገዲማውያኑን እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ግንኙነት ጤናማ እንዲሆን የማድረግ፣ ገዳማውያኑ እና ምዕመናኑ በእምነታቸው እንዲፀኑ እና እንዲጠነክሩ የማድረግ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የኦርቶድክስ ተዋሕዶ ክርስትና እና የሌሎች እምነት ተከታዮች የገዳሙ ጠባቂ፣ ተቆርቋሪና ደጋፊ እንዲሆኑ የማድረግ  ፊይዳ እንዳላቸው፡፡ በገዳሙ ለሚከወነው የልማትና የመስፋፋት ስራም የተቃና ይሆን ዘንድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ  አጥኚው ለማሳየት ሞክሯል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱን ጠንካራ እና ደካማ ጎን እና ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ተመሳስሎ ስናነሳ አጥኚው ቃላዊ ተረኮቹን በአምስት ይዘት መድቦ ትንታኔን ሰጥቷል ፡፡ለጥናቱ አላማ መሳካት የተጠቀማቸው መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ትንታኔው በአግባቡ እና በይዘት ተከፋፍሎ መቅረቡ በአጠቃይ እንደ ጠንካራ ጎን የሚወሰዱ ሲሆኑ እንደ መሪማ ሁሉ የወንደሰን ስራም ተረኮቹ ለገዳማውያኑ እና ለምዕመናኑ የሚሰጡት ፋይዳ ብሎ ያነሳው ዕምነታዊ ፋይዳውን ብቻ መሆኑን እንደ ድክመት ወስጄዋለሁ፡፡ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለውምጥናት በገዳም ላይ መመስረቱ፣ ተረኮችን ማጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያም ሆነ  የመተንተኛ ስልቱ ሲሆን ይህ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለየ መሆኑ እና የተረኮቹን ስነምግባራዊ ፋይዳ ማንሳቱ ከእርሱ ጥናት ይለየዋል፡፡

አንተነህ አየነው:: 2011 ፡፡"በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና ጥናት" ጅማ ዩኒቨርሲቲ ፡፡ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ ፤ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና  ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለድህረ ምረቃ መረሐ ግብር ኮርስ ማሟያ ጥናት አድርጓል፡፡የጥናቱ ዋና ዓላማ ከርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ይዘት እና ማህበራዊ ፋይዳ ተንትኖ ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የጽሁፍ መረጃዎችን በመመልከት ቃለ መጠየቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ተኮር ውይይት በመጠቀም አጥኚው መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡትም መረጃዎች እንደአስፈላጊነቱ ማጣቀሻ መጽሃፍትን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡በትንታኔውም በአጠቃላይ በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮች የገዳሟን ጥንታዊነት የሚዘክሩ፣ ገዳሟ እንድትከበርና እንድትጠበቅ የማድረግ፣ አማኙ ማህበረሰብ በእምነታቸው እንዲፀኑና እንዲጠነክሩ የማድረግ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ገዳሟን በማክበር እንዲንከባከብ፣ አካባቢውን እንዲወድ፣ በመንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ

ኑሮው ተስፈኛ እንዲሆን የማድረግ፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች የገዳሚ ጠባቂ፣ ደጋፊና ተቆርቋሪ እንዲሆኑ የማድረግ አገልግሎት እንዳላቸው አሳይተዋል።

በአጠቃላይ የጥናቱን ጠንካራ እና ደካማ ጎን እና ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ተመሳስሎ ስናነሳ አጥኚው ቃላዊ ተረኮቹን በሰባት ይዘት መድቦ ትንታኔን ሰጥቷል ።ለጥናቱ አላማ መሳካት የተጠቀማቸው መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ትንታኔው በአግባቡ እና በይዘት ተከፋፍሎ መቅረቡ እና በገዳሙ የሚነገሩት ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳቸው ምንድነው የሚለውን ለማሳየት መሞከሩ በአጠቃይ እንደ ጠንካራ ጎን የሚወሰዱ ሲሆኑ ።ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለውም ጥናቱ በገዳም ላይ መመስረቱ፣ ተረኮችን ማጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያም ሆነ የመተንተኛ ስልቱ ሲሆን ይህ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለየ መሆኑ እና የተረኮቹን ስነምግባራዊ ፋይዳ ማንሳቱ ከእርሱ ጥናት ይለየዋል።

## 2.4 ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዳራዊ ገለፃ

### 2.4.1. ጥናቱ. የተካሄደበት ወረዳ አጠቃላይ መረጃ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ 14 ዞኖች መካከል አንዱ የሆነው የምንጃር ሸንኮራ ወረዳ በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ ከሚገኙት 5 ከተማ እስተዳደር እና 22 ወረዳዎች መካከል አንዱ ነው። የወረዳው የቆዳ ስፋት 2294.63 ካ.ሜ ወይንም 229463 ሄ.ር ይኟል።( ከግብርና ፅ/ቤት እቅድ ላይ የተወሰደ መረጃ) ወረዳው ከዞን ጠቅላላ የቆዳ ስፋት የ 9.205% አለው። የወረዳው አቀማመጥም በቀጥታ አቅጣጫ በሰሜን ላቲቲዩድ (north latitude ) $8^0$44``0''--- $9^0$6``0'' N እና ምስራቅ ሎንግቲዩድ (east longitude ) $39^0$ 14 ``0''E ---$39^0$ 45 ``0'' E ላይ የሚገኝ ሲሆን በተለያዩ አቅጣጫዎችም የተለያዩ ከተሞች ወረዳዋን ያዋስኗታል። እነሱም

- ❖ በሰሜን ሀገረ ማርያም ከሰም ወረዳ
- ❖ በሰሜን ምስራቅ በረኸት ወረዳ
- ❖ በደቡብ ኦሮሚያ ክልል ቦሰት ወረዳ
- ❖ በምስራቅ ኦሮሚያ ክልል ፈንታሌ ወረዳ
- ❖ በምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ጊንቢቹ ወረዳ
- ❖ በደቡብ ምስራቅ ኦሮሚያ ክልል ሎሜ ወረዳ ጋር ይዋሰናል።

በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ አስተዳደራዊ ክፍፍልን በተመለከተ በወረዳዋ ውስጥ 1 ከተማ አስተዳደር 26 የገጠር ቀበሌና 1 የከተማ ቀበሌ ይገኛሉ፡፡የወረዳዋ ዋና ከተማ የዞን ርዕሰ መስተዳደር ከሆነችው ከደብረ ብርሀን የለው ርቀት 257.3 ኪ.ሜ ሲሆን ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ዋና ከተማ ባህር ዳር ያላት ርቀት 643.1 ኪ.ሜ ነው፡፡ወረዳው ከቅርብ አጎራባች ወረዳዎች ጋር በማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ትስስር በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡(ወ/ሮ በየነች ጥሩነህ የሸንኮራ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊ ሚያዚያ ፣ 29፡፡)

ሰንጠረዥ 2 የወረዳው የቆዳ ስፋት ፣ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ፣ ወረዳው ያለው ርቀት

| የወረዳው ስም | የወረዳው ዋና ከተማ | የወረዳው የቆዳ ስፋት | | በወረዳው የሚገኙ ቀበሌዎች ብዛት | | የወረዳው ዋና ከተማ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በካ.ሜ | በሄክታር | ገጠር | ከተማ | ከዞን ያለው ርቀት በኪ.ሜ | ከባ/ዳር ያለው ርቀትበኪ.ሜ |
| ምን/ ሸንኮራ | አረርቲ | 2294.63 | 229463 | 27 | 3 | 257.3 | 643.1 |

ምንጭ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም መጽሄት 2009 ዓ.ም እትም የተወሰደ

### 2.7.2 የወረዳው መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ንብረት

የወረዳው የመሬት ገፅታ የተለያየ እና ወጣ ገባ ነው፡፡ ሸለቆና በአብዛኛው ሜዳማነት የሚታይበት ነው፡፡መልክአ ምድሩን ስንመለከት ተራራማ 2 % ፣ወጣ ገባ 24.1 % ፣ ሜዳማ 73.9 % ነው፡፡ በአብዛኛው መሀል ምንጃር እና ከሞላ ጎደል ሸንኮራ ሜዳማ አሰፋፈሩም የተራራቀ ለኑሮም አስቸጋሪ መሆኑን ያሳያል፡፡ በወረዳው በሶስት የመሬት አወቃቀር የሚከፈል ሲሆን እነሱም ቆላ ፣ደጋ እና ወይናደጋ ናቸው፡፡

### 2.7.3 በወረዳው የሚገኙ ቅርሶች

በወረዳው የተለያዩ ዘመናትን ያስቆጠሩ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ቅርሶች ውስጥም አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ንብረት የሆኑ ገዳማት እና አብያተ ክርስትያናት ናቸው፡፡በወረዳዋ ከሚኖሩት ሰዎች መካከል 87% የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ 3 % የፕሮቴስታንት 10 % ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታዮች ይገኙበታል፡፡በ

ወረዳዋ በአመት እስከ 500ሺ የሚሆኑ ቱሪስቶች (የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ጨምሮ) ወደ ወረዳዋ ይገባሉ፡፡( የምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ መፅሄት 2009 ዓ .ም)

ሰንጠረዥ 3. በወረዳው የሚገኙ ቅርሶች

| ወረዳ | የሚገኝበት ቀበሌ | አካባቢያዊ ስያሜ | የቅርሱ አይነት | የተመሰረተበት ዓ.ም | የመስህቡ የተፈጥሮ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| ምን/ሸንኮራ | ሳማ | የሳማ ሰንበት ገዳም(እግዚኦ ለሰንበት)አመታዊ ክብረ በአል እና ዋሻዎቹ | ገዳም | 1750 | ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ |
| | ጨረቻ | የሸንኮራ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዩሀንስ ፈዋሽ ፀበል እና መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ | ገዳም | 1620 | ተፈጥሮ |
| | ራራቲ | የገራምባ ደብረ መድሀኒት ቅድስት ማርያም ሙቅ እና ቀዝቃዛ ፈዋሽ ፀበል እናመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ | ገዳም | 1840 | ተፈጥሮ |
| | ራራቲ | የዲፋ ደብረ መዊ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስትያን ተአምራት እና መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ | ቤተ ክርስትያን | 1906 | ተፈጥሮ እናሰው ሰራሽ |
| | ባልጪ | የባልጪ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስትያን ጥንታዊ ቁሶች | ቤተ ክርስትያን | 1540 | ሰው ሰራሽ |
| | አረርቲ | አረርቲ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም | ገዳም | 1812 | ሰው ሰራሽ |
| | ኢራንቡቲ | ኢራንቡቲ 44ቱ ታቦታት ማደርያ ስፍራ (የጥምቀት በአል ማክበሪያ) | ሀይማኖታዊ ስፍራ | በ14ኛው ክ/ዘመን | ተፈጥሮ |

# ምዕራፍ ሶስት ፤ የጥናቱ ስነ ዘዴ እና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የሚከተለው ገላጭ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ ይህም የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ ከስታስቲካዊ መረጃዎች ይልቅ በገለፃ መልክ የሚቀርቡ መረጃዎችን ስለሚይዝ ነው፡፡ይህም በሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮችን ለመመርመር እና ስነምግባራዊ ፋይዳቸውን ለማሳየት ጥያቄዎች በሰፊው በማብራራት ለመተንተንና ጥናቱን ለማስኬድ አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ለመምረጥ ችያለሁ፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.2.1 የቦታ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የሚካሄድበት ቦታ በአማራ ክልል ዉስጥ በሰሜን ሸዋ ዞን ስር የምትገኝ ምንጃር ሸንኮራ የምትባል ወረዳ ስትሆን ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ላይ ትገኛለች፡፡በወረዳው ስር ብዙ አድባራት እንዲሁም ገዳማት ይገኛሉ፡፡ስለዚህም ይህ ጥናት የሚከተለው የናሙና አወሳሰድ ዘዴ አላማ ተኮር (Purposive Sampling). የናሙና አመራረጥን ይሆናል፡፡አጥኚዋ በሸንኮራ ወረዳ ከሚገኙ አድባራት እና ገዳማት ጥናቱ የሚካሄድበትን የሸንኮራ ዮሀንስ ገዳምን የመረጠችበት ምክንያት ዋነኛው ገዳሙ 394 አመትን ያስቆጠረ እጅግ ጥንታዊ እና እጅግ በጣም ብዙ ታሪኮች ያሉት በመሆኑና በገዳሙ የተጠና ጥናት አጥኚዋ ባለማግኘቷ ይህንን ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ነው፡፡

### 3.2.2 የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ

በመረጃ ሰጪዎች ምርጫ በኩል ደግሞ ጥናቱ በገዳሙ ተረኮች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከጥናቱ አላማ አንፃር መረጃ ሊሰጡ የሚችሉትን ገዳማውያን የአካባቢው ነዋሪዎች እና ሌሎች ከጥናቱ ጋ ተያያዥነት ይኖራቸዋል ብዬ የማስባቸውን ማህበረሰብ አካላት ወይም ተጠኝዎች ተመርጠዋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

መረጃ የምሰበስበው ከቀዳማይ እና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ይሆናል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሳት፣ ስለገዳሙ የሚያውቁ የአካባቢው ነዋሪዎችና ከገዳሙ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ፡፡ ካልዓይ የመረጃ ምንጮች የሚሆኑት ደግሞ ለጥናቴ የሚበጁ ንድፈ ሃሳቦች እና ጽንሰ ሃሳቦች፣ የተለያዩ መጻሕፍት፣ ስለገዳሙ የሚያትቱ ድርሳናት እና ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ይሆናሉ፡፡በአጠቃላይ ይህን ጥናት ለማካሄድ ሦስት የመረጃ

ዘዴዎችን የምጠቀም ይሆናል፡፡ እነሱም ቃለ መጠይቅ ፣ ቡድን ውይይት እና ሰነድ ፍተሻ ይሆናሉ፡፡

### 3.3.1. ቃለ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጠበት ምክንያት ተረኮቹን ለመሰብሰብ ዋነኛ መሳርያ በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ከገዳማውያኑ እና ከአካባቢው ነዋሪዎች ትረካ በመነሳት ተረኮቹ ስነ ምግባር ከመቅረፅ እና ከማስተካከል አንፃር ያላቸውን ሚና ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለጥናቱ በቂና ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስለሚያስችል ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ተመርጧል፡፡በቃለ መጠይቅ ለመረጃ አቀባይነት የሚመረጡት ግለሰቦች በፆታ ወንድና ሴት ፣ በእድሜ ደግሞ ከ40 አመት በላይ የሆኑ ገዳሙን በቅርበት የሚያውቁ የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ አምስት ሰዎች (5) እና በገዳሙ የሚኖሩ አስር ገዳማውያን አባቶች እና እናቶች( 10 )የገዳሙን አስተዳደር ጨምሮ የሚሳተፉ ይሆናል፡፡ ጥያቄዎች ከሚፈለገው መረጃ አንፃር የተዋቀረና ያልተዋቀረ የሚሉትን የቃለ መጠይቅ አይነቶችን አጥኚዋ ተጠቅማለች ፡፡

### 3.3.2 ቡድን ተኮር ውይይት

የቡድን ውይይት በሁለተኛ ደረጃ ለዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠ ዘዴ ነው፡፡ የተመረጠበትም ምክንያት በቃለ መጠይቅ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን ለመመለስና የጎደለ መረጃ ካለ የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት በማሰብ ነው፡፡ ስለሆነም በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች አጠራጣሪና እርግጠኛነት የጎደላቸው መረጃዎች ካሉ ለመረጃው ቅርበት ያላቸውን በእድሜ ከ45 በላይ ይሆናቸዋል ተብሎ የሚታሰቡትን 6-10 ያህል የአካባቢውን ሰዎች በመምረጥና በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ ወጥነት ያለው መረጃ ሊያስገኝ ስለሚያስችል መረጃዎች በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ተሰብስበዋል፡፡በቡድን ተኮር ውይይት ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች መሀከል በቃለ መጠይቅ መረጃ የሰጡ ሰዎች ተካተዋል፡፡

### 3.3.3 ሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት ከሚዳሰሱ ነገሮች አንዱ የሸንኮራ ዩሀንስ ገዳም አመሰራረት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የገዳሙን አመሰራረትም ሆነ ከገዳሙ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለማግኘት የተለያዩ መፅሀፍን ፣ ጥናታዊ ፅሁፎችን እና የመሳሰሉ የህትመት ውጤቶችን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ስለታያት ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ መርጣለች፡፡

### 3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ ፣በቡድን ተኮር ውይይት እና በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የምርምር ጥያቄዎቹን ለመመለስ እና የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች ለገዳሙ ሥርዓት እና ለገዳማውያኑ ህይወት እንዲሁም የገዳማውያኑን እና የአለማውያንን ስነ ምግባር ከመቅረፅ አንፃር ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት አጥኚዋ አይነታዊ የመተንተኛ ስልትን ተጠቅማለች፡፡ይህን ስልት በመጠቀምም መረጃዎቹን እያንዳዱን መረጃ በጭብጥ ተመሳስሏቸው በመከፋፈል እና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን እና ስነልቦናዊ ንድፈ ሀሳብን መነሻ በማድረግ በአይነታዊ የመተንተኛ ስልት መረጃዎቹ ተተንትነዋል፡፡

### 3.5 ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች

አጥኚዋ በመጀመሪያ ትልመ ጥናቱን ጨርሳ መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ ለመውጣት ስትዘጋጅ የመጀመርያ ያደረገችው ተግባር ከትምህርት ክፍሉ የትብብር ወረቀት በማውጣት ወደ ገዳሙ ማቅናት ነበር፡፡በገዳሙ ደርሳ በአካባቢው ላይ የማረፍያ ቦታዋን ካመቻቸች በኋላ በነጋታው ቀን ጠዋት ከፀበል መልስ የገዳሙን አበምኔት ፍለጋን የመጀመሪያ ስራዋ ነበር ያደረገችው፡፡የገዳሙ አበምኔት የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን በማስፈፀም እጅግ በጣም ውጥረት ላይ በመሆናቸው እሳቸውን ማግኘት የቻለችው በአምስተኛው ቀን ነበር ፡፡እሳቸውን እንዳገኘቻቸው የትብብር ደብዳቤውን አስቀድማ ትብብር እንዲያደርጉላት ጠይቃቸዋለች፡፡እሳቸውም ጊዜው ከባድ ስለሆነ ከ ፓትሪያሪክ ፅ/ቤት ወረቀት እንድታመጣ አዘዟት አጥኚዋ ፀበል እየተጠመቀች እንደሆነ በማስረዳት አቋርጣ መሄድ እንደማትፈልግ ገልፃ እንዲተባበሯት ለመነቻቸው፡፡ የመጣችበትንም ቀን ጠቅሳ እስከዛ እለት ድረስ እሳቸውን ለማስፈቀድ ስትጠብቅ እንደነበር እና የጥናቱ ጊዜ እያለፈባት እንደሆነ አስረዳቻቸው፡፡ እሳቸውም ከሶስት ቀን በኋላ ቐጠሯት አጥኚዋም አመስግና ተመለሰች፡፡ በሶስተኛው ቀን ሲያገኙዋት ቅዳሴ ስታስቀድስ እና ፀበል ቦታም ስትሄድ በማየታቸው እንዳመኗት ገልፀው፡፡ የተለያዩ ሰዎችን ከመጠቆም እንስቶ እስከ የተለያዩ መረጃዎችን እንድታገኝ በመርዳት ተባብረዋት ጥናቷን አጠናቃ ፡፡ልትሄድ እንደሆነ ስትነግራቸውም መርቀው እና የተለያዩ ምክሮችን ለግሰው ተሰናብተዋታል፡፡

## ምዕራፍ አራት ፤የመረጃ ትንተና

መረጃዎቹን ከመተንተናችን በፊት ተረኮቹን የምናይበትን አበይት ጉዳይ የሆነውን የስነምግባርን ምንነት በአጭሩ እንመልከት፡፡"ሥነ ምግባር" የሚለው ቃል ብዙ ፍቺዎች አሉት፣ እሱም ከግሪክ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ባሕርይ" ማለት ነው፡፡ በአንዳንድ መዝገበ ቃላቶች ሥነ ምግባር "ጥሩ እና መጥፎ የሆነውን ለመወሰን እንዲሁም የሞራል ግዴታዎችን እና ኃላፊነቶችን የመወሰን ተግሣጽ" ተብሎ ይገለጻል፡፡ የሩሲያ መዝገበ-ቃላትም የስነ-ምግባር መግለጫዎችን እንደሚሰጡ (.https://wapstroy.ru ፣ 2020 ) ባወጣው ፅሁፍ ላይ ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ:

1. ስነምግባር- የፍልስፍና ሳይንስ ሲሆን ዓላማው ሥነ ምግባር አንድ ዓይነት ማህበራዊ ንቃተ-ህሊና መፍጠር ነው፡፡ስነምግባር የሰው ልጅ ህይወት ተፈጥሮውን እና ውስጣዊ መዋቅሩን ይመረምራል ፣ የሥነ ምግባርን ተፈጥሮ እና ታሪካዊ እድገት ያጠናል ፡፡ (ፍልስፍናዊ ኢንሳይክሎፒዲያ መዝገበ ቃላት፡፡ገጽ 776)፡፡

ወደ ሀገራችን ስንመጣ "ስነ ምግባር" የሚለው ቃል ከግዕዝ የመጣ እንደሆነ ሊቃውንት ያሥረዳሉ፡፡( www.eotcmk.org ፣2020)ስለ ክርስትያናዊ ስነ ምግባር የፃፈበት ገፅ ላይ ይሕን አስፍሯል፡፡

- ሥነ ማለት ሠናየ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጕሙም ማማር' መዋብ ማለት ነው፡፡
- ምግባር ማለት ገብረ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጕሙም ተግባር ክንውን ማለት ነው፡፡
- ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ማለት የክርስቲያን መልካም ሥራ ያማረ ተግባር የተዋበ ክንውን ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት ያመነ ሰው የሚሠራው መልካም/ያማረ ተግባር ማለት ነው፡

በዚች አለም የሚኖር ሰው ሁለት ምድራዊ ህጎችን ሊያከብር ይገባል፡፡የመጀመሪያው የአንድ ሀገር መንግሥት ወይም የሚያስተዳድር አካል ሕዝቡን ለማስተዳደር የሚያወጣው ሕግ ከሆነ ሁለተኛው ደግሞ ኅብረተሰቡ በባሕሉ ትክክል ነው ብሎ የተቀበለውና በወረቀት ያልተጻፈው ሕግ ነው፡፡ "በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ" 2 ተሰ.2፣15 እንዲል፡፡

ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ሕግ እንደሚገዛ ሁሉ የሰውንም ሕግ ከእግዚአብሔር ጋር እስከ አላጣላው ድረስ ሊያከብር ይገባል፡፡ አንድ ሰው ምንም ቢጾም ቢጸልይ፣ ለእግዚአብሔር እገዛለሁ ቢል የሚያስተዳድረውን አካልና የኅብረተሰቡን መልካም ባሕል ካፈረሰ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባሩን ኀደሎ ያደርገዋል፡፡ በሥራ ቦታ የታዘዘውን ካልፈጸመ፣ የሥራ ሰዓት ካላከበረ፣ በቤተ ክርስቲያን ያለውን ምግባሩን በሌላ ሥፍራ ካልገለጸው ዋጋ አይኖረውም፡፡ ለእግዚአብሔር እንደሚገዛ ሁሉ በሰውም ፊት ያለነቀፋ ሊኖር ያስፈልጋል፡፡ "በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጐራጕሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ በእነርሱም መካከል የሕይወት ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ" ፊል.2፥15

ሐዋርያው ከዚህም በተጨማሪ "ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ መልካም የሆነውን እናስባለን" ብሏል፡፡ 2ቆሮ.8፥20 ይህ ሲባል ኀጢአትም ሲሆን የሰው ሕግ ወይም ባሕል ነውና ሁሉን መፈጸም አለበት ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ አንድ ሰው በማኅበራዊ ኑሮው ከሌሎች ጋር በሠላምና በፍቅር ሊኖር እንዲሁም አልጫውን ዓለም በምግባሩ ሊያጣፍጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም ሰው በማኅበራዊ ኑሮ ተሳትፎ ውስጥ ሊይዝ የሚገባቸው ነገሮች አሉ፡፡እነርሱም የተለያዩ የስነምግባር ክፍሎች ናቸው፡፡

## 4.1 ከሸንኮራ ዩሀንስ ገዳም የተገኙ ተረኮች ትንተና

በዚህ ጥናት በትንታኔ የሚቃኙት ቃላዊ ተረኮች ሚታዊ ገጽታን የተላበሱ፣ አንዳንዶቹም አፈ ታሪካዊ አተራረክን የያዙ ናቸው፡፡ በእርግጥ እነዚህ የተረክ አይነቶች አንዱ በአንዱ ውስጥ መገኘታቸው እና ለአንዳንድ ወጥ ክፍፍል የተመቹ አለመሆናቸው እውን ነው፡፡ በጥናቱ አሰባሰብ ወቅት የተወሰኑ መረጃ አቀባዮች ተረኩን "ከአባቶቻችን ሲባል የሰማነው አፈ ታሪክ ነው" በሚል ሲገልጹት፣ ከፊሎቹ ደግሞ በዓይናችን ያየነው ተአምር ነው ይላሉ፡፡ ይህም ተረኮቹ ግለሰባዊ ዕውቀት ላይ የተመሠረቱ እና የግለሰባዊ ገጠመኝ ተረኮች ሊባሉ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎችም ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚጠቁም ነው፡፡ ስለዚህ ለተሰበሰቡት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ቁርጥ ያለ ዘውጋዊ ትንተና መስጠት ባይቻልም ዋና የሆኑትን ፅንሰ ሀሳቦች በመምዘዝ እና የጭብጥ ትንተና በማድረግ አጥኚዋ ተረኮቹን በይዘት ከፋፍላ አቅርባቸዋለች፡፡ ከገዳሙ የተሰበሰቡትን ተረኮች በይዘት ሲከፈሉ የገዳሙን አመሰራረት እና

ጥንታዊነት የሚዘክሩ፣ የቦገዳሙን ቅድስና እና ክብር የሚገልፁ፣ በገዳሙ የተፈፀሙ ፈውሶችን እና ገቢረ ተአምራቱን የሚያሳዩ እና ገዳሙ የማህበረሰቡን ስነምግባር የሚቆጣጠርባቸው ተረኮች እና ስነምግባራዊ ፋይዳቸው የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡

### 5.1.1 የታላቁ የደብረ ምጥማቅ ሽንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና ስነ ምግባራዊ ፋይዳቸው

የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሀንስ ፅላት አሁን ወዳለበት ስፍራ ከመምጣቱ በፊት በ 16ኛው ክፍለ ዘመን በደብረ ኢጎራ መንዝ እንደ ነበር ይነገራል፡፡

> ያኔ በስደት ዘመን በሽሽት ከደብረ ኢጎራ ታቦተ ህጉን ይዘው ከእጬ ዮሀንስ ወደ ጠራ ሳፋጅ ዮሀንስ ይሰደዳሉ፡፡ ታቦቱን የተሸከሙትም መነኩሴ ከእጨ ዮሀንስ እስከ ጠራ ሳፋጅ ድረስ አባ ገድሉ ብርሀኑ ሚባሉ ናቸው፡፡ከዛ ቡልጋ እንደደረሱ ታቦተ ህጉን ከአባ ገድሉ በፈቃደ እግዚአብሄር አባ ሰርፀወልድ ተቀብለው አሁን ታቦቱ ካለበት በስተቀኝ ዋሻ አለ አደለም? በዛ ያሥቀምጡታል፡፡ በዚያም ወደ 30 አመት አካባቢ ኖሯል፡፡እንግዲህ በዋሻው እንደነበረ ግራኝ እያሳደደ ታቦትን ያቃጥል አልነበር፡፡እነሱ ክር የላቸውማ ታዲያ በቦታው የነበሩ መነኮሳት ከዛ ከትልቁ ዛፍ ላይ እየወጡ ሌትም ቀንም ሳይሰለቹ ነው እንግዲህ ጠብቀው ያቆዩት፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ ፤ አባ ወልደ አማንኤል ፣ሚያዝያ2 27፣ 2014)

ከዚህ በመነሳት አሁን በሽንኮራ የሚገኘው የቅዱስ ዮሀንስ ታቦት መነሻው ከመንዝ ደብረ ኢጎራ እጬ ዮሀንስ አንደሆነ እንረዳለን ፡፡ እኚህ አባት ተረኩን በሚተርኩበት ወቅት "ማእተብ የለውም አደለም?" የሚል በውስጡ "አዎ " የምትለዋን መልስ ያዘለ ጥያቄ አንስተዋል ፡፡ማእተብ ምድነው ስንል አንድም የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይነትን የሚያመለክት በአንገት ዙሪያ የሚደረግ ጥቁር ክር ሲሆን አንድም የታማኝነትን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ እኚህ አባት ግን በዚህ ሀረግ ለማስተላለፍ የፈለጉት ግራኝ ጨካኝ ፣ ምግባር የለሽ አውሬ መሆኑን ነው፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያት ግራኝ በሰአቱ የኦርቶክስ እምነት ታቦታትንም ሆነ የተለያዩ ቅርሳዊ ቁሶች ያቃጥል እንደነበር በተለያዩ ተረኮች ላይ ይጠቀሳል፡፡ ይህን ምግባርም ከሰብአዊነት የወጣ ምግባር ያለው ፍጡር ሊያደርገው የማይችለው ነገር እንደሆነ ያሥረዳሉ፡፡

ታቦቱ በዋሻው ውስጥ ለ30 አመት ከቆየ በኋላ በ1620 ዓ.ም ከዋሻው ወጥቶ አሁን ወዳለበት ቤተ መቅደስ ገብቷል፡፡ስለዚህ የሽንኮራ ዮሀንስ ታቦት ወደ ምንጃር ሽንኮራ የመጣው በ1590 አካባቢ እንደሆነ ይነገራል፡፡

መምህር ሰርፀወልድ ለ30 አመት ከታቦቱ ሳይለዩ እየተቀመጡ እንዳለ በአንድ ሌሊት እግዚያብሄር በራዕይ ይታያቸውና "አንተ ወደ እኔ መምጫህ ደርሷል ስለዚህ ታቦቱን ከዋሻው አውጣና ቤተክርስትያን መስርት በዛም ብዙ ተአምራት ይደረግበታል ፣ድውያን ይፈወስበታል ፣ ለምፅ ይነፃበታል።" ብሎ ይነግራቸዋል። እሳቸውም በቃ ተጠርተዋልና ትውልድ አፅሜን እንዳይወቅስ ብለው ታቦተ ህጉን ለ ሰላሳ አመት ካስቀመጡበት ዋሻ አውጥተው በትዕዛዙ መሰረት ቤተክርስትያኑን መሰረቱ።

(ቃለ መጠይቅ ፤ አባ ወልደ አማንኤል ፣ሚያዝያ2 27፣ 2014)

ከላይ እንደምንመለከተው መምህር ሰርፀ ወልድ የተባሉት አባት በህይወት ዘመናቸው ብቻ ሳይሆን ከዚህ አለም ካለፉ በኃላ እንኳ ቀጣዩ ትውልድ እንዲድን ፣ከበሽታው እንዲፈወስ እና እንዳያዝንባቸው የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ተቀብለው ታቦተ ህጉን አውጥተው ቤተክርስትያኑን መመስረታቸው ራስ ወዳድ አለመሆንን እና ለሌላው ጥሩ ነገር ማሰብን ያመላክተናል።ይህን ሀሳብ የምትገልፀው ቃልም "ትውልድ አፅሜን እንዳይወቅስ ብለው" የምትለው ቃል ነች። ከዚህም በህይወት ስንኖር የምናደርጋቸው ተግባራትም ሆኑ በህሊናችን የምናስባቸው ሀሳቦች ሌሎችን እንዴት ይጠቅማሉ? ፣ የሚያመጣው መጥፎ ነገርስ ይኖራል ወይ? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ እንደሆነ እንገነዘብበታለን።አንድ መጥፎ ተግባር ስናከናውን በህይወት ባለን ጊዜ ብቻ ሳይሆን በህወት ካፍን በኋላም እንኳን ቢሆን ሰዎች እንዲያዝኑብን እና ስለኛ ጥሩ ነገር እንዳያስቡ ያደርጋቸውል።ከሞትን በኋላ እንኳን አፅማችን እንዳያርፍ ይሆናል።



የሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም የድሮው ቤተ መቅደስ

በዚህ አይነት መንገድ ገዳሙ ለብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ እንደተባለው ብዙ በሽዎችን የሚፈውሰው ፣ለምፅን የሚያነፃው ፀበል በ1954 ኢ.ም እነደተገኘ የገዳሙ ሊቃውንት ይገልጻሉ፡፡ነገር ግን ፀበሉ ከመፍለቁ በፊት ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት በነበሩ ሁለት ተክሎች የበለስ እና የቅንጭብ ዛፍ ቅጠሎች ምክንያት ብዙ ሰዎች ከበሽታቸው ይፈወሱ እንደነበር በአካባቢው የሚኖሩ አዛውንት ያስረዳሉ፡፡

> ነቀርሳ ፣ ሻሽኝ ፣ኪንታሮት ያድናል፡፡ሻሽኝ አፍንጫ ላይ ትወጣና ጉርስርስ አድርጋ ነው ምትጥለው፤ ኪንታሮት ፊንጢጣ ላይ ይወጣና መከራ ነው እህል እንኳ አያስበላም፡፡ታድያ ዱብ ነው ሚያደርገው ዮሀንስ እንስከነምናምኑ፡፡ምንድነው ሚቀባው ታድያ ቅንጭብ ነው፡፡ያን ቅንጭብ

ይወስዳሉ ይጨቀጨቅና እበረንዳ ላይ ያድራል ወደ ቤት አይገባም በነጋታው ቁስሉ ላይ ይደመደማል በቃ መዳን ነው፡፡ዘባት ሚባል እንደ በለስ ያለ ቅጠል አለ እሱ ደግሞ ፍልቅቅ ሲያደርጉ ይደማል እሱን ቁስሉን ተቀብተው መዳን ነው፡፡

(ቃለ መጠይቅ ፣ አብዬ ተረፈ ፀጋ ፣ግንቦት 1፣2014)



ብዙሀንን የፈወሰው የቅንጭብ ዛፍ

ከላይ የተጠቀሱት እፅዋት ሁሉንም በሽታ የሚያድኑት ቅዱስ ዮሀንስ በእነርሱ ስለሚጠቀም እንደሆነ ተራኪው አስረድተዋል፡፡ይህ የቅንጭብ ብዙ ሰዎችን ከችግሮቻቸው ሲፈውስ እና ሲፈታ አንድ ትዕዛዝ አለው ፡፡ቅጠሉ ተጨቅጭቆ ወደ ቤት አይገባም፡፡ በረንዳ ላይ ወይም ከቤት ውጪ ነው የሚያድረው፡፡ ታድያ አብዬ ተረፈን ይሕ ትዕዛዝ ባይከበርስ ቅንጭቡን ወደ ቤት ቢያስገቡትስ ምን ይሆናል? ብዬ የጠየኳቸውን ጥያቄ ሲመልሱ "አታድርግ ከተባለ ለምን ይደረጋል ሰው እንዴት ለድህነቱ ያምፃል!?" ነበር ያሉት ይህ አባባል ስናጤነው በህይወት

መንገዳችን ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን ለማከናወንም ሆነ ለማግኘት የተለዘያዩ ትዕዛዛት ያጋጥሙናል፡፡ታዲያ መጠየቅ ባይከፋም አንዳንዴ ትዕዛዛትን ላለማክበር ስንል ብቻ ለምን ፣ይህ ባይሆን ምን ይሆናል እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እናነሳለን፡፡ነገር ግን አንድ ነገር አድርጉ ስንባል እኛንም ሆነ ሌሎች ሰዎችን የማይጎዳ መሆኑን እያወቅን ይልቁን ለእኛ መድሀኒት የሆነን ነገር ላለማድረግ መትጋት እንደሌለብን የሚያመላክት ነው፡፡አሁን ላይ እያስተዋልን ያለነውን አንድ ነገር እንኳን እንደ ምሳሌ ብናነሳ ስለ አንድነት በሚወራበት ጊዜ "ብንለያይስ ምን ይመጣብናል?" የሚል በእብሪት የተሞሉ ጥያቄዎችን ያነሳሉ፡፡ይህን ስንመለከት እውነትም "ሰው እንዴት በድህነቱ ላይ ያምፃል" የሚለው የአብዬ ተረፈ ጥያቄ የእኛም ጥያቄ ትሆናለች፡፡ ስለዚህም ከላይ ካስቀመጥኩት አንቀፅ የቀደሙትን ትዕዛዛት ማክበር ከብዙ መጥፎ ነገሮች እነደሚጠብቀን እና እንደሚያድነን ያስተምራል፡፡

በ1954 ተአምረኛው የሸንኮራ ዮሀንስ ፀበል እንደተገኘ የሚገልፁት አባቶች መምህሬ ካሳ የተባሉ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳገኙት ይጠቁማሉ፡፡

> በዚህ የሚኖሩ መምሬ ካሳ የተባሉ አስታራቂ ሽማግሌ ነበሩ፡፡እኚህ ሰው በተደጋጋሚ በህልማቸው የፀበሉን ስፍራ ያሳያቸዋል፡፡ታዲያ አንድ ሌሊት በዛ ፀበል ብዙ ሰዎች እንደሚድኑ ይነግራቸውና ተነስተው ፍለጋ እንዲጀምሩ ያዛቸዋል፡፡ እሳቸውም በነጋተው ተነስተው ፍለጋውን ይጀምራሉ፡፡ሆኖም አላገኙትም ተመልሰው ወደ ቤታቸው ይገባሉ፡፡በተከታታይ ለስምንት ቀን እየሄዱ ቢፈልጉትም ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ከዛ በስምንተኛው ቀን ለሊት ነገ በጠዋት ተነሳና ፍለጋህን ጀምር አንዲት ወፍ ትመራሀለች እሷን እየተከተልክ ከሄድክ ታገኘዋለክ፡፡ካገኘህው በኋላ ለካህናቱ እና ለህዝቡ ንገር ይላቸዋል፡፡እንደተባሉት ጠዋት ተነስተው መንገድ ሲጀምሩ ወፊቱ ፊታቸው ቀድማ ትመራቸው ጀምር፡፡ደክሟቸው ከድንጋይ ላይ ሲያርፉ እሷም ከዛፍ ቅጠሎች ላይ እያረፈች ወደ ፀበሉ አደረሰቻቸው፡፡ፀበሉ ጋር እንደደረሰች አጠገቡ ካለ ዛፍ ላይ አርፋ ክንፏን በማርገብገብ ምልክት ሰጠቻቸው፡፡እሳቸውም እግዚአብሄርን አመስግነው ከፀበሉ ቀምሰው ተመለሱና ለካህናቱ እና ለህዝቡ ነግረው ሚያዝያ 30 ቀን ታቦተ ህጉን ይዘው ወርደው ፀበሉ ተባረከ፡፡እንደቃሉም እስካሁን ብዙ ሰዎችን እያዳነ ነው፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ ፣ አባ ወልደአማኑኤል ሚያዝያ 27፣ 2014)

በአሁኑ ሰአት ወደ ገዳሙ ከሚመጡት ሰዎች ብዙሀኑ ለፈውስ ወደ ፀበሉ የሚመጡ ናቸው፡፡ብዙ በህክምና መፍትሄ ያልተገኘላቸው በሽታዎች በዚህ ፀበል እንደተፈወሱም ይነገራል፡፡ከላይ ካለው አንቀፅ ሁለት ነገሮችን ወስደን ስነምግባራዊ ፋይዳቸውን ስንመለከት የመጀመሪያው "ሰው አስታራቂ" የሚለው ቃል ሲሆን ይሕ ቃል የሚያመላክተው የመምሬ ካሳን

ማህበራዊ ደረጃ ነው፡፡ሰው አስታራቂ መሆናቸው የተከበሩ በአካባቢው ማህበረሰብ የሚወደዱና መልካም ሰው መሆናቸውን ያመላክተናል፡፡በዚህም ምክንያት ለዚህ ትልቅ ክብር ቅዱስ ዮሀንስ እንደመረጣቸውም ያሳየናል፡፡ሁለተኛው ደግሞ ፀበሉ ለብዙሀን ድህነት እንደሚሆን ስለተነገራቸው ያደረጉትን ተስፋ ያለመቁረጥ ትግል የሚያመላክተን ሲሆን ለህብረተሰባችን መልካም ነገሮችን ለማድረግ መትጋት እንዳለብን የሚያሳየን ነው፡፡ ይህም በተያየ መስክ ህብረተሰብን የሚያገለግሉ ሙያተኞች ለማህበረሰቡ ጥቅም መስራት ግዴታቸው እንደሆነ አምነው ያለመታከት መስራት እነዳለባቸው ያስተምራል፡፡

### 5.1.2 የገዳሙን ቅድስና እና ክብር የሚገልፁ ተረኮች እና ስነምግባራዊ ፋይዳቸው

በሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም ከተሰበሰቡት ተረኮች የስፍራውን ቅዱስነት የማስጠበቅ ተግባር ያላቸው ይገኛሉ፡፡ በገዳሙ ከሚተረኩት ተረኮች መካከል በዚህ ሥር ይካተታሉ ያልኳቸውን የተወሰኑ ተረኮች አነሳለሁ፡፡ የተለያዩ ቁሶችን ከገዳሙ ሰርቀው ለመውጣት የሞከሩትን ሰዎች ፣ እና ትዕዛዝን ያላከበሩ ሰዎች የገጠሟቸውን ነገሮች የሚያሳይ ነው፡፡

> አንድ ዕለት ከፀበልተኛ መሀል ተቀላቅላ የገባች አንዲት ሴት የፀበልተኛውን ልብሶች ፣ለሊት ለባትሪ እንዲያገለግሏቸው የያዙትን ስልኮች እና ሌሎች የፀበልተኞችን ንብረቶች ዘርፋ ፀበል የሚቀዳበትን ጀረኪና ከላይ ያለውን ለማስገቢያ እንዲረዳት ቀዳ ማስገቢያ ካበጀችለት በኂላ በነጠላዋ ተሸክማ ከፀበሉ ወጥታ እየተመለሰች ሳለ ሰባ ደረጃውን እንዳለፈች እግሯ አልንቀሳቀስ ይላታል፡፡እስከ ማታ ድረስ ባለችበት ተቀምጣ ብትቆይም መንቀሳቀስ አልቻለችም፡፡በመጨረሻም በዛ ሰአት የጊቢው ጠባቂ የነበረው ሰው "አንቺ ሴት አረ ቀኑ እየመሸ ነው እዚህ ቦታ ጅብ እንዳይበላሽ" ሲላት "እግሬ አልንቀሳቀስ ብሎኝ ነው፡፡" ትለዋለች እሱም በእጁ ደግፎ ሊያነሳት ቢል እጁን እሳት አነደደበት፡፡ኂላ የሆነ ችግር አለ ብሎ አባ ሀይለጊዮርጊስ የሚባሉ መነኩሴ ጠርቶ የሆነውን ይነግራቸዋል፡፡ እሳቸውም በቦታው ደርሰው ካዩ በኂላ ዮሀንስ አስመልክቷቸው ኖሮ "ከጀርባሽ ያለውን አውርደሽ ንስሀ ስጪ ልጄ ቢሏት ያደረገችውን ተናዛ ሸክሟን አወረደች፡፡እግሯን ቅዱስ ዮሀንስ በቸርነቱ ፈታላት እቃውም ለጠፋባቸው ሰዎች ተመለሰ፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ፣ አባ መላኩ በላይ ፣ሚያዝያ 28 ፣2014)

በዋናነት የዚህን ተረክ ተግባር ስንመለከት በግቢው ውስጥ ምንም አይነት መጥፎ ተግባር ለመፈፀም የሚሞክር ሰው ቢኖር እንደማይሳካለት ይልቁንም ራሱን ከባድ አደጋ ውስጥ እንደሚጥል ማሳየት ነው፡፡ተራኪው በትረካቸው ወቅት የተጠቀመዋቸውን ቃላት ወስደን ስንመለከት ስርቆቱን " ዘርፋ" የሚለውን ቃል ተጠቅመው የገለፁበት ምክንያት የስርቆትን መጥፎነት ለማሳወቅ እና ትኩረት እንዲሰጠው ይመስላል፡፡ ስርቆት በቤተክርስትያን በአስርቱ

ትዕዛዛት  እንዳይደረጉ ከተከለከሉት ነገሮች መሀከል ሰባተኛው ትዕዛዝ ነው፡፡ የሠው ንብረት መውሰድ ሆነ መመኘት ከባድ ሀጥያት እንደሆነም ያስገነዝባል፡፡ ሌላው ተራኪው "ሽክሚን አወረደች " የሚለውን ቃል የተጠቀሙት አንድም በጀርባዋ የያዘችውን ዕቃ እንዳወረደች ለመግለፅ ሲሆን ሌላው እና ዋናው ደግሞ በንሰሀ ከሀጥያቷ ነፃ ወጣች የሚል ነው፡፡ በክርስትና ጥፋትን መስራት ባይደገፍም ሰው ነንና የተለያዩ ጥፋቶችን ስናጠፋ በንስሀ መመለስ ሀጥያታችን እንዲሰረይልን ማድረጊያ እና ጥፋት ሰርተን ያስቀየምነውን ፈጣሪያችንን ይቅርታ የምንጠይቅበት መንገድ ነው፡፡(ሊቀ ልሣናት ቀሲስ ከፍያለው ጥላሁን ፣ 2005 ) ንስሓ ማለት መጸጸት ማለት ነው፡፡ የክርስትና ሕይወት የንስሓ ሕይወት ነው፡፡ በንስሓ የበደለ ከበደሉ ይነጻል፡፡ ኀጢአተኛውም ጻድቅ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለግል መንፈሳዊ ሕይወት ሥራችሁን አቅኑ፡፡" ኤር.18፥11 ከንስሐ በኋላ ቅዱስ ቁርባን መቀበል ያስፈልጋል፡፡ "የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡" ዮሐ.6፥53

እንግዲህ ቃሉን ሰምተን ንስሓ ገብተን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ስንቀበል የግል መንፈሳዊ ሕይወታችን የተስተካከለ ይሆናል፡፡ የግል መንፈሳዊ ሕይወት ጽናት ደግሞ ለማኅበራዊ ኑሮአችን ወሳኝ ነውና፡፡ "ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አሳብ ይህንም አዘውትር፡፡ ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፡፡ በእነዚህ ጽና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህ፡፡" 1ጢሞ.4፥15 በማለት ስለ ንስሀ ምንነት እና ጠቀሜታ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት ሰዎችን ማስቀየም እንደሌለብን በአጋጣሚዎች ግን በዳይ ሆነን ስንገኝ ይቅርታ መጠየቅን ከተረኩ እንማራለን፡፡

> በ2012 ነው ኮሮና ወደ ሀገሪቱ ገብቷል ተብሎ የክልሉ ብትይ የወረዳው አስተዳዳሪዎች አይናቸው ወደ እዚህ ሆነ፡፡በቃ እየመጡ ገዳሙን ዝጉ ይሉናል እኛም "ተው ቡዙ በሽተኞች መጥተው የሚፈወሱበት ነው እንዴት ይዘጋል ይሄኮ የቃልኪዳን ስፍራ ነው፡፡"ብንላቸው አሻፈረን ብለው መንገድ ዘግተው ወደ ፀበል የሚመጣውን ሰው ከመንገድ ይመልሱት ጀመር፡፡ፀበልተኛው ችግሩን እየነገረ ቢለምናቸው ያን ሁሉ በሽተኛ እና  ደካማ ሲያንገላቱት በዋሻው ከሚኖሩ ባህታውያን መልዕክት  መጣ፡፡"ታገሱ የአመቱን ክብረ በአል እናንተ እንጂ እነሱ አያዩትም"የሚል እውነትም ሰኔ 30 አመታዊ በአሉ ሲከበር እነዛ ህዝቡንም ከህናቱም አልሰማ ብለው ሲያስቃዩ የነበሩ ሰዎች ኮሮና ተይዘው ወደ ማገገሚያ ገቡ፡፡
> (ቃለ መጠይቅ ፣መጋቢ ሀዲስ መላከ መንክራት ቆሞስ አባ አብርሀም ዳኛቸው ፣ ግንቦት  2 ፣1014)

ወደ ገዳሙ ለፀበል በአማካይ ወደ 300 ሺ ህ ያህል ሰው ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ብሎም ከተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚመጡ ሲሆን ለፀበል መጥተው በፀበሉ ተፈውሰው ከቀዬው አልርቅም በማለት በአጥቢያው በአሁን ሰአት እየኖሩ ያሉ ወደ 10 ሺ የሚጠጉ ምዕምናን እንደሚገኙ የነገሩኝ የደብሩ አስተዳዳሪ መጋቢ ሀዲስ መላከመንክራት ቆሞስ አባ አብርሀም ዳኛቸው እነዚህ ፀበልተኞች በተለያዩ ችግሮች አልፈው ወደዚህ ስፍራ ድህነትን ፍለጋ እነደሚመጡ ጠቁመዋል፡፡ከእዚህም መካከል የትራንስፖት ተቸግሮ አግኝቶ የሚመጣ ፤ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ከአልጋ መነሳት የማይችል ሰው ሌሎች ሰዎችን አስቸግሮ የሚመጣ እና አዛውንቶችን ጨምሮ ብዙ ነገሮችን ሰውቶ ደጁን ረግጦ ለመፈወስ የሚመጣን ሰው ችግር ያለመረዳት ብሎም የታላላቅ ካህናትን ምክር አለመስማት እና እነሱን አለማክበር ያመጣባቸውን ችግር ተረኩ ይነግረናል፡፡ መከባበር ማለት ለሌላው ሰው ያለን ልባዊ የሆነ መታዘዝ፣የፍቅር ፍርሃት፣ እና የምናሳየው ከፍ ያለ ዋጋ ነው፡፡

መከባበር የፍቅር ሌላኛው ገጽታው ነው፡፡ መፅሀፍ ቅዱስ እናትና አባትን ፣በእድሜ ታላላቆችን ፣ባለስልጣናትን የእግዚአብሔር አገልጋዮችን (የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን) እንድናከብር እና እርስ በርስ እንድንከባበር ያስተምረናል፡፡( ሊቀ ልሣናት ቀሲስ ከፍያለው ጥላሁን ፤ 2005)

ይህ ስነምግባራዊ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ በዋናነት ተረኩ ለማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት የገዳሙን ክብር የሚነካ እና የገዳሙን አባቶችም ሆነ ዮሀንስን አምነው ሊድኑ የሚመጡ ምዕመናን የሚያስከፋ እና የሚያጎሳቁልን የትኛውንም አካል ( ሰው) ቅዱስ ዮሀንስ እንደሚቀጣው ነው፡፡

> አባ ፈላውቶስ የተባሉ በገዳሙ ይኖሩ የነበሩ መነኩሴ ከደግነታቸውና ከመንፈሳዊ ብቃታቸው የተነሳ በሚቀድሱበት ጊዜ መላ ሰውነታቸው እንደፀሀይ ያበራ ነበር፡፡ ቢሆንም እሳቸው ከትህትናቸው የተነሳ በሚቀድሱበት ጊዜ ታናናሾቻቸውን እናንተ ቀድሱ እኔ ምዕዋት አዘጋጃለሁ፣ በትምህርት ጊዜ አስተምሩ ሲባሉ ከኔ በላይ እናንተ ስለምታውቁ እናንተ አስተምረኝ ባይሆን እኔ ሌላውን እሰራለሁ የሚሉ ትሁት ነበሩ፡፡አባ ፈላውቶስ ላዘዛቸው ሁሉ የሚላኩ እና የሚታዘዙ ነበሩ ታዲያ ቅዱስ ዮሀንስ በተደጋጋሚ በህልማቸው እጃቸውን ይዞ ሲወስዳቸው ይታያቸው ነበር፡፡ አንድ ሌሊት ዛሬ ወዳጆችህ ተሰናበት ላሳርፍህ ነው አላቸው፡፡እሳቸውም በጥዋት ተነስተው ሁሉንም ከተሰናበቱ በኋል ተሰውረዋል፡፡
>
> ( ቃለ መጠይቅ ፤ አባ በለጠ ሞላ ፣ሚያዝያ 27 ፣2014)

ከላይ ያለውን ተረክ ስንመለከት ዋና አላማው በገዳሙ ቅዱስ ዮሀንስ በቤቱ በንፅህና ለሚያገለግሉት ክብሩን እነደሚገልፅ ማሳየት ሲሆን ለተራኪዎቹም ሰው የኔ ነው የሚለውን ነገር ያውም እምነቱን ከፍ ከፍ ማድረግ ሰዋዊ ባህሪ በመሆኑ የቦታውን ክብር አንድም በስሙ

በታነጸው ቤተ ክርስቲያን ስም አልያም በገዳሙ በሚያገለግሉ አባቶች ስም ተረኮችን በማያያዝ እንደሚተርኩ እንገነዘባለን፡፡ ስለሆነም የእኛ ታቦት እኮ ታምረኛ ነው! የእኛ የእምነት አባቶች እኮ ከሁሉም በላይ የበቁ ናቸው! በአጠቃላይ ተረኩ የእምነቱን ትክክለኛነትና አዳኝነት ለማሳየት የተሞከረበት በሚመስል መንፈስ የተባለ ይመስላል፡፡የተረኩን ስነምግባራዊ ፋይዳ ከተራኪው የቃላት አጠቃቀም በመነሳት ስንመለከት ደግሞ በመጀመሪያ ተራኪው አባ ፈላውቶስን ደግነታቸውን እና መንፈሳዊ ብቃታቸውን ይጠቅሳሉ፡፡

እነዚህ ሁለት ነገሮችን ተንትነን ስንመለከት የደግነት ተግባር መንፈስን የማረጋጋትና የማጽናናት ኃይል አለው፡፡ደግነት ለሌሎች ደህንነት ልባዊ አሳቢነት ማሳየትን ይጨምራል፤ ይህ አሳቢነት ደግሞ ሌሎችን ለመርዳት ብለን በምንናገራቸው ቃላትና በምናደርገው ድርጊት ይገለጻል:: ደግነት በተግባር የሚገለጽ ባሕርይ ስለሆነ ለታይታ ብሎ መልካም ምግባርና ትሕትና ከማሳየት የበለጠ ነገር ማድረግን ይጠይቃል:: እውነተኛ ደግነት ለሌሎች ካለን ጥልቅ ፍቅርና ችግራቸውን እንደ ራሳችን ችግር አድርጎ ከመመልከት የሚመነጭ ባሕርይ ነው:: ከዚህም በላይ እንዲህ ዓይነቱ ደግነት ክርስቲያኖች እንዲያዳብሩት የተነገራቸው የአምላክ ቅዱስ መንፈስ ፍሬ አንዱ ገጽታ ነው:: (ገላ. 5:22, 23 ) ኢየሱስ ምድር ላይ በነበረበት ወቅት ደግና ርኅሩኅ በመሆኑ ይታወቅ ነበር:: ኃይለኛ ወይም ሌሎችን የሚጫን ሰው አልነበረም:: የሰዎችን ችግር እንደራሱ ችግር አድርጎ በመመልከት "እናንተ የደከማችሁና ሸክም የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም እረፍት እሰጣችኋለሁ" በማለት ተናግሯል:: (ማቴ. 11:28-30) ኢየሱስ ደግ ስለነበር ሕዝቡ በሄደበት ሁሉ ይከተለው ነበር:: ኢየሱስም 'በጣም ስለሚያዝንላቸው' ይመግባቸው፣ ሕመምተኞቻቸውን ይፈውስ እንዲሁም  ያስተምራቸው ነበር:: (ማር. 6:34 ፤ ማቴ. 14:14፤ 15:32-38) ኢየሱስ ከሰዎች ጋር በነበረው ግንኙነት አስተዋይና የሌሎችን ስሜት የሚረዳ ሰው መሆኑ ደግነቱን የሚያሳይ ማስረጃ ነው:: እንዲያውም የተጠየቀው ነገር የቱንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን እሱን ፈልገው የመጡትን ሁሉ "በደግነት" ይቀበላቸው ነበር:: (ሉቃስ 9:10, 11) ለምሳሌ ያህል፣ ይፈስሳት በነበረው ደም ምክንያት በሕጉ መሠረት ርኩስ የነበረች አንዲት ሴት ፈውስ ለማግኘት ተስፋ በማድረግ ፈራ ተባ እያለች የልብሱን ጫፍ በነካች ጊዜ አልገሠጻትም:: (ዘሌ. 15:25-28) ለ12 ዓመታት ስትሠቃይ ለነበረችው ለዚህች ሴት ርኅራኄ በማሳየት "ልጄ ሆይ፣ እምነትሽ አድኖሻል:: በሰላም ሂጂ፤ ከሚያሠቃይ ሕመምሽም ተፈወሽ" ብሏታል:: (ማር. 5:25-34)

ሁለተኛው በእምነት መብቃት ሲሆን ተራኪው ይሕን ቃል የተጠቀሙት ሁሉንም ክርስትያናዊ ስነምግባሮች እንደሚከተሉ ለመግለፅ ነው፡፡እንዲህ በምግባር ስለታነፁ ቅዱሳን በመፅሀፍ ቅዱስ

እንዲህ የመሰለ ገጠመኝ ተፅፎ ይገኛል፡፡"ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ፥ እግዚአብሔርም
ስለወሰደው አልተገኘም። ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና፤ ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።" ዕብ 11፥17-1
ስለዚህም ከተረኩ የምንማረው ጥሩ ስነምግባር የተላበስን እና ደግ (ለሰው አሳቢ) ስንሆን አምላካችን ከክፉ ነ ነገሮች ሁሉ እንደሚጠብቀን ነው፡፡

### 5.1.3 በገዳሙ የተፈፀሙ ፈውሶች እና ገቢራተ ተአምራት ተረኮች

ሃይማኖታዊ ፈውስ አንድ አካላዊ ወይም ስነልቦናዊ ችግር ያለበት ሰው ለአካላዊውም ሆነ ለስነልቦናዊ ችግሩ በእምነቱ የሚያገኘው ደህንነት ነው ሊባል ይችላል፡፡ የፈውስ አይነቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህንም ከፋፍለን ስንመለከት የመጀመሪያው የፈውስ አይነት ከአካላዊ ህመም መዳን ሲሆን ለምሳሌ፡- የአይንን መብራት፣ የጆሮን መስማት፣ የስብራትን መጠገን፣የቁስልን መሻር፣ ከአለመራመድ ቆሞ መሄድን፣ ከውስጥ ህመም መዳን ወዘተ ይመለከታል፡፡ ሁለተኛው ከአጋንንት እስር ነጻ መውጣት ነው፤ሦስተኛው ፈውስ ከሞት መነሣት ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች በመስቀል በመታሸት፣ በአባቶች ፀሎት፣ በፀበል በመጠመቅ ወይም በመጠጣት ወዘተ ፈውስ ያገኛሉ ተብሎ የሚታመንባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተረኮችም ከዚ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡

> አንድ ሰው ለፀበል ወደ እዚህ ስፍራ ይመጣል፡፡ሰውየው የተፈጥሮ ድውይ ያለበት ነው፡፡የተፈጥሮ ድውይ የምንለው በተለያየ አካል ላይ ትርፍ የማያስፈልግ ነገር ያለባቸው ሲ ፈጠሩ ጀምሮ ማለት ናቸው፡፡ ታዲያ ይህ ሰው ሲመጣ "እኔ ስፈጠር ጀምሬ እንዲሁ ነኝ አሁን ከዚ በኋላ ምን አዲስ ነገር ይኖራል" ብሎ በልቡ ተጠራጥሯል፡፡ታዲያ እዚህ መጥቶ ሲጠመቅ የተለያዩ በሽታዎችን ዮሀንስ ሲፈታ ያያል፡፡ በህክምና የማይቻሉትንም ከዛ ሰውየው በልቡ ስላሰበው ነገር ይፀፀትና ምህረት ይለምናል፡፡ለምን ብዙ ከሱ የባሱ ችግሮች ሲፈቱ አይቷላ መቼስ ሰው ካላየ የራሱ ችግር አይደለም ከሁሉም በላይ መጥፎ የሚመስለው፤ እና ይህ ሰው እኔም እድናለሁ ይህ ሁሉ ለሚያድን ቅዱስ ዮሀንስ ይሄ አይቸግረውም ብሎ ይላል፡፡ታዲያ ይህን አስቦ በነጋታው ፀበሉን ተጠምቆ ሲወጣ ከጀርባው የነበረው ድውይ ተቆርጦ ወድቆ ተመልሶ ጀርባው ተሰፍቶ ወጣ ፡፡ ስላመነ ከሁሉ በላይ ተደረገለት ማለት ነው፡፡ከዛ ድኖ በአውደምህረት መስክሮ ወደ ቤቱ ገብቷል፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ ፣ አባ ወልደ አማኑኤል ፣ ሚያዝያ 27 ፣2014 )

“ችግሩ ከእምነት እንጅ ከመድኃኒት አልነበረም፡፡ “እንዲሉ አበው ከላይ ከተረኩ የምንረዳው አብይ ነገር እምነት የድህነት ቁልፍ መሆኑን ነው፡፡ተራኪው እንደነገሩን ሁላችንም እኛ ጋር ካለው የበለጠ ችግር ፣ህመም ፣ስቃይ እንዳለ ወጥተን ካላየን በቀር እኛ ጋር ያለው ችግር በአለም ካው ሁሉ የከፋ እና መፍትሄ እንደሌለው ቆጥረን ከመንገዳችን እየቆምን ነው፡፡ ሁሉን የሚችል ፣ ሁሉን የፈጠረ ብለን የምናመልከው ፈጣሪን እንኳን መጠራጠር ጀምረናል፡፡ “እምነት ተስፋ የተደረጉትን ነገሮች በእርግጠኝነት መጠበቅ ማለት ነው፤ በተጨማሪም የምናምንበት ነገር በዓይን የሚታይ ባይሆንም እውን መሆኑን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ነው፡፡” (ዕብራውያን 11:1)

በተረኩ ላይ የተገለፀው ሰው ያለ እምነት ሲመላለስ ያልተደረገለት ነገር አምኖ ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ በ አንድ ቀን መዳኑ ሁለት ነገሮችን ያስተምረናል፡፡የመጀመሪያው ነገር እምነትን ማዳበር ነው፡፡” እውነተኛ እምነት ታምራቶችን፣ ራዕዮችን፣ ህልሞችን፣ መፈወስን፣ እና እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ የሚሰጣቸውን ሁሉ ስጦታዎችን ያመጣል፡፡ በእምነት አንድ ሰው የኃጢያት ስርየትን እናም በመጨረሻም በእግዚአብሔር ፊት የመኖር ችሎታን ያገኛል፡፡ እምነት ማጣት ሰውን በኃጢያት ምክንያት ወደሚመጣው ተስፋ መቁረጥ ይመራል፡፡” (ሞሮኒ 10፣22)፡፡ይህም በህይወታችን ሁሉንም ሰዎች ተጠራጣሪ ከሆንን ወደ ሌላ ህጥያት እንደሚከተን የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ከምናያቸው እና በሌሎች ከሆኑት ትምህርትን ወስዶ በጊዜ ህይወትን ማስተካከል እንደሚቻል ነው፡፡

> አንዲት ለአስራ ሁለት አመታት የአልጋ ቁራኛ የነበረች ሴት አስራ ሁት አመት ሙሉ ደም እየፈሰሳት ህክምና በቃ ትሞቻለሽ ብሏት የነበረች ሴት ወደ ሸንኮራ ዮሀንስ ውሰዱኝ ብላ ሰዎች ይዘዋት እንዲመጡ ታደርግና ወደ ፀበሉ መውረድ ባትችልም ጊዜው ክረምት ነበር ከጣራው የሚወርደውን አስቀድታ “ዮሀንስ አቅሜን አንተ ታውቀዋለህና ጠበልህ አድርግልኝ” ብላ ትጠጣለች፡፡ ከዛ ደሙም ቆመላት በሽታውም ጠፍቶ ድና ሄዳለች
>
> (ቃለ መጠይቅ፣ አባ መላኩ በላይ ፣ ሚያዝያ 28 ፣2014 )

ይህ ተረክ አንዲት መዳን የምትፈልግ ሴት ለመዳን ስትል የምትችለውን ሁሉ የምታደርግበትን መንገድ ፣ ተስፋ ያለመቁረጧን እና የእምነቷን ከፍታ ያሳየናል፡፡በተረኩ የተገለፀችው ሴት ማድረግ የማትቸለው ነገር ስላለ ለድህነት የምታደርገውን ጉዞ አላቆመችም፡፡ይልቁንም በእርሷ አቅም የምትችለውን ነገር በእምነት አድርጋ የምትፈልገውን ነገር አግኝታለች፡፡

ተስፋ መቁረጥ አንደ ኤልያስ ያሉትን ታላላቅ ነቢያት ተፈታትኗል።"ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ፥ ነፍሱንም ሊያድን ሄደ፥ በይሁዳም ወዳለው ወደ ቤርሳቤህ መጥቶ ብላቴናውን በዚያ ተወ። እርሱም አንድ ቀን የሚያህል መንገድ በምድረ በዳ ሄደ፤ መጥቶም ከክትክታ ዛፍ በታች ተቀመጠና፦ ይበቃኛል አሁንም፥ አቤቱ፥ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ።"(መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 19:3-4)ነገር ግን በሆነው ባልሆነው እጅ የማንሰጠው እኛ ባይመቸንም እግዚአብሄር አላማውን እየፈፀመ ስለሆነ ነው። እኛን ደስ ባይለንም የእግዚአብሄር አሰራር ስራውን እየፈፀመ ነው።

ተስፋ የሕይወት ጣዕም ነው! ይህ ጣዕም ሲጠፋ ሕይወት ውሃ ውሃ ማለት ይጀምራል! ሕይወት ውሃ ውሃ ሲል ደግሞ መኖር ትርጉም ያጣል። መኖር ትርጉም ሲያጣ አለመኖር ይከተላል።አንድ ሰው በህይወት የመኖርን ተስፋ ካጣ ደግሞ ከፍተኛ ማህበራዊ ጉዳቶችን ያስከትላል። ምክንያቱም ራሱን የማይወድ ሰው ሌላውን ሊወድ አይችልም።ራሱንም ሆነ ማህበረሰቡን የማይወድ ሰው ደግሞ ለማህበረሰቡ ስነምግባራዊ መርህ ተገዢ አይሆንም።

> አንድ በውጪ የሚኖር ወጣት ነው። በልጅነቱ ነው ከኢትዮጵያ የወጣው ቋንቋ እንኳን አይችልም እና ይታመም እና ወደ ህክምና ሲሄድ ነቀርሳ ነው ትሞታለህ።ይሉታል ልጁም ለአያቱ ሲነግራት አያቱም ስዕለት ተስሎ ጥዋት ጥዋት ለ 1 ወር ንፁህ ውሀ በቅዱስ ዮሀንስ ስም እንዲጠጣ ትነግረዋለች።ያንን አድርጎ ተመልሶ ሀኪም ቤት ቢሄድ ትሞታለህ ያሉት ሀኪሞች ነቀርሳውን አጡታ! ከዛ ልጆም ከአያቱ ጋር እዚህ መጥቶ ስእቱን አስገብቶ ተመልሶ ሄደ።
>
> (ቃለ መጠይቅ ፣መጋቢ ሀዲስ መላከ መንክራት ቆሞስ አባ አብርሀም ዳኛቸው፣ ሚያዚያ 27፣ 2014 )

ይህ ተረክ ቅዱስ ዮሀንስ ላመኑት እና ስሙን ለጠሩት በየትኛውም ሰአት ፣በየትኛውም ቦታ ፣ በየትኛውም ሁኔታ የሚደርስ መሆኑን ያመለክታል። በዚህ ተረክ ውስጥ ሁለት ስነምግባራዊ ትምህርቶችን እናገኛለን ። የመጀመሪያው ወጣቱ የአያቱን ምክር ሰምቶ እሳቸው ያሉትን ማድረጉ የታላላቆቻችንን ምክር መስማት እና ታዛዥነትን የሚያሳይ ነው።መፅሀፍ ቅዱስ "በልማድ ብቻ መሥዋዕትን ከማቅረብ መታዘዝ ይበልጣል፤"( 1ሳሙ. 15:22።)በማለት መታዘዝ ከሁሉ በላይ እግዚአብሄርን የሚያሥደስት ተግባር መሆኑን ይገልፃል።

በተደጋጋሚ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ታዛዥነትን እንደሚባርክ እና እንደሚባርከን በተደጋጋሚ እናነባለን።ደካማም ይሁኑ ብርቱ፡ ከድካማቸው እንድንማር፡ ብርታታቸውን እንድንከተል በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ታሪካቸው የተጻፈላቸው ሰዎች ሁሉ ምንጊዜም ለኛ

የሚያስተምሩት ነገር አለ። ለምሳሌ አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ለመባል የበቃው በእምነት ባሳየው መታዘዝ በመሆኑ እኛም እንደ አብርሃም በእምነት እግዚአብሔርን ብንታዘዝ የበረከቱ ተካፋዮች እንደምንሆን እግዚአብሔር

ተናግሯል።"መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ። በአንተ አ ሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ።" (ወደ ገላ 3፣6) ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዝ አለባቸው።( ኤፌሶን 6:1-3) "ከአምላክ ፈቃድ ጋር በሚስማማ መንገድ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ" ይላል።

በተረኩ የተገለጸው ወጣት የአያቱንምክር በመስማቱና በመታዘዙ ፈውስን አግኝቷል፡፡ ከዚህም የታላላቆቻችንን ምክር መስማት እና መታዘዝ በህይወታችን የወደፊት እጣችንን ለመወሰን እና መንገዳችንን ከማስተካከል አንጻር ይህ ነው የማይባል ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ነው።

ሁለተኛው ተረኩ የሚያስተላልፈው ስነምግባራዊ መልዕክት የራሳችን የሆነውን ነገር (እምነት፣ ወግ ፣ባህል ፣ታሪክ) ማክበርና ማወቅ ትልቅ ጥቅም እንዳለው ነው።በተረኩ የተገለፀው ወጣት ለብዙ አመታት በውጪ ሀገር የኖረ መሆኑን ተራኪያችን "ቋንቋ እንኳ አይችልም" በማለት ነግረውናል።ይህ ሆኖ ሳለ ወጣቱ በአሁኑ ሰአት ብዙዎቻችን የተናገሩት ሁሉ የማይቀየር አድርገን የምናስባቸው የውጭ ሀገር ሀኪሞች ካሉት በላይ አያቱ ጋር መፍትሄ እንደሚኖር አስቦ ችግሩን ማዋየቱ እና ያሉትን መተግበሩ ቀድመን በሀገራችን ያለውን ነገር ማክበር እንዳለብን የሚያስተምር ነው።

በተጨማሪ ተራኪው "ሀኪሞቹም ነቀርሳውን አጡታ!" ያሉበትን የቃላት አጠቃቀም ስንመለከት ተራኪው በዚህ አባባል ነገሩ አግራሞት የሚጭር መሆኑን እና ቅዱስ ዮሀንስ ያደረገው ተአምራት እጅግ በጣም ድንቅ መሆኑን ለማመልከት የተጠቀሙት እንደሆነ እንገነዘባለን።

> አንዲት ሴት በጋብቻ ወደ አሜሪካ ትሄዳለች ።በዚያ ከባለቤቷ ጋር እየኖረች ሳለች ልጅ እምቢ ቢላት ወደ ህክምና ስትሄድ መውለድ እንደማትችል የነገራታል።በዚያ በጣም ታዝንና ወደ ሀገሯ መመለስ እንደምትፈልግ ስትነግረው "ተይ እኔ እና አንቺ ተዋደን ከኖርን ልጅ ባይመጣም ችግር የለውም ደግሞ በዚህ ምክንያት አልከዳሽም" ብሎ ቃል ይገባላታል፤ ኋላ ግን መቼስ ስጋ ደካማ ነው አስራ ሰባት አመት አብረው ከኖሩ በኋላ ሀብት ሲመጣ ወራሽ ሳይኖረኝ አስቀረሺኝ እያለ መስደብ የጀምራል።ይሄ ቃል እየተደጋገመ ሲመጣ ሁሉን ትታ ወደ ሀገሯ ትመለሳለች።ከዛ ወደዚህ ቦታ መጥታ "ምነው ዮሀንስ እንደው

ከማይረባውም ቢሆን አንድ ልጅ ለኔ እንዴት አጣህልኝ ብላ አልቅሳ ትለምነዋለች፡፡ ከዛ ችግሯን ለአባቶች ትነግርና ገድሉን አዝላ ሶስት ጊዜ መቅደሱን ዞራ ትሳላለች፡፡ በአመቱ ቅዱስ ዮሀንስ ወንድ ልጅ አሳቅፏት ስዕለቷን ይዛ መጣች፡፡ከማይረባውም አንድ ልጅ ብላ የለም? የልጁ አባት መንገድ ቁጭ ብሎ የሚቅም ፣የሚጠጣ ፣የሚያጨስ ሰው ነበር፡፡ከብዙ አመት በኋላም የበፊት ባለቤቷ ሌላ አግብቶም ልጅ መውለድ ስላልቻለ መጥቶ ይቅርታ እንደጠየቃት መጥታ ተናግራለች፡፡

( ቃለ መጠይቅ ፣ እማሆይ ፅጌ ተክሉ ፣ግንቦት 4፣2014)

ይህ ተረክ ልጅ የሚሰጠው ፈጣሪ መሆኑን የሚያመላክት እና ቅዱስ ዮሀንስ የለመኑትን ሁሉየሚያደርግ ቸር መ ሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡በውስጡም ብዙ የተለያዩ ስነምግባራዊ ጉዳዮችን ይዟል፡፡ ከተራኪዋ የቃላት አጠቃቀም ስንነሳ ሁለት ነገሮችን እናያለን "ከማይረባው" የሚለው መጀመሪያው ሲሆን እንደ ተራኪዋ አባባል መጠጥ የሚጠጣ ፣ጫት የሚቅም ፣ስራ የማይሰራ እና ሱሰኛ ሰው " የማይረባ " መሆኑን ሲሆን ሁለተኛው "ስጋ ደካማ ነው" የሚለው ነው፡፡ ተራኪዋ ይህን አባባል የተናገሩት "ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት" ለማለት ይመስላል፡፡ተራኪዋ በተረኩ ላይ የቀረበው የቀድሞ ባለቤቷ ላይ ፍርድ ለመስጠት አልፈለጉም፡፡ነገር ግን ቃሉን አለመጠበቁ ስህተት መሆኑን ያመለክታል፡፡

ተረኩ ከሚያስተምረን ስነምግባራዊ ጉዳይ ዋነኛው ቃል ጠባቂነትን ነው፡፡ በየትኛውም ሁኔታ ለገባነው ቃል ታማኝ መሆን እንዳለብን ተረኩ ያስተምረናል፡፡በተረኩ ውስጥ ቃሉን ሳያከብር የቀረው ሰው በስተመጨረሻ ችግሩ ወደእርሱ ዞሮ ተመልክተናል፡፡ስለዚህ ለገባናቸው ቃሎች ታማኝ መሆናችን እንደሚጠቅመን የሚያስተምረን ነው፡፡

በዛሬው ጊዜ እንደማይፈጽሙት እያወቁ ቃል መግባት የተለመደ ነገር የሆነ ይመስላል፡፡ እነዚህም የጋብቻ መሐላዎች፣ የንግድ ስምምነቶች ወይም ከልጆች ጋር ተጨማሪ ጊዜ ለማሳለፍ የሚገቡ ቃሎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ "ትልቅ ሰው ማለት ቃሉን የሚጠብቅ ሰው ነው" የሚለው የተለመደ አባባል በሰፊው ቸል እየተባለ መጥቷል፡፡ አንድ ክርስቲያን የተበደረውን ገንዘብ በመክፈልም ይሁን አንድ ዓይነት አገልግሎት በመስጠት ወይም የገባውን የንግድ ውል በመፈጸም ቃሉን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ይህ አምላክን የሚያስደስት ከመሆኑም በላይ "ወንድሞች ተስማምተው ሆነው በአንድነት እንዲቀመጡ" ለማድረግ የግድ አስፈላጊ የሆነውን እርስ በርስ የመተማመን መንፈስ ያጎለብታል፡፡ (መዝሙር 133:1)፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የገባነውን ቃል የምናከብር ሰዎች ከሆንን ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብተን እና ተስማምተን መኖር እንችላለን ።በተጨማሪም በማህበረሰባችን ውስጥ የሚሰጠን ማህበራዊ ደረጃ ጥሩ እና ከፍተኛ ይሆናል።ይህም ለራሳችን የምንሰጠውን ግምት በመጨመር በተሰማራንበት የሙያ መስክ ስኬታማ እንድንሆን ያደርጋል።

### 4.1 .4. ገዳሙ የማህበረሰቡን ስነ-ምግባር የሚቆጣጠርባቸው ተረኮች

ባለፉት ንዑስ አርእስታት ስር በገዳሙ የሚነገሩ ተረኮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስነ ምግባርን የሚያስተምሩ መሆናቸውን አይተናል።በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ደግሞ ገዳሙ በውስጡ ያሉት መነኮሳት እና በአካባቢው ያሉ ምዕመናን የተለያዩ የስነ ምግባር ጥሰቶችን በሚፈፅሙበት ወቅት እንደየጥፋቱ ደረጃ የተለያዩ ቅጣቶች በመጣል ወደ ሌላ ጥፋት እንዳይሄዱ የሚያደርግባቸውን ተረኮች እንመለከታለን። ወደ ተረኮቹ ከማምራታችን በፊት ምግባር ከልጅነት ይጠበቃልና በገዳሙ የሚማሩ የቆሎ ተማሪዎች እና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጥፋት በሚሰሩበት ጊዜ የሚደረገውን እንመልከት

> ስነ ምግባር እንግዲህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው።የኛ ቤተ ክርስትያን የራሷ ህግ አላት፣ ስርአት አላት።የምናስተምራቸው ልጆች ሰው አክባሪ ፣ እግር የሚያጥቡ ፣እጅ የሚያስታጥቡ ፣ አለባበሳቸው መስቀለኛ ፣ አነጋገራቸው ክርስትያናዊ፣ ሰው የማያስቀይሙ ፣ለትልቁም ለትንሹም የሚታዘዙ፣ አንገታቸውን የደፉ ፣የማይሰክሩ ፣የማይዘሙቱ እንዲሆኑ እናስተምራቸዋለን እንቆጣጠራቸዋለን።አንድ ካህን ለክህነት አገልግሎት መብቃት የሚችለው በንፅህና ነው።እንቁላል አንዴ ከእጅ ካመለጠ አይመለስም ፤ የሰው ልጅ ክብርም እንዲሁ ነው።አሁን በዘመንኛው ሳንተዋወቅ ሳንጠናና እንዴት ትዳር ይሆናል ይላሉ መገናኘት ይመጣል፣ መተቃቀፍ ፣ መላፋት ይሆናል ከዛ ሀጥያቱ ይተርፋል።ስለዚህ እኛም ወጣቶቻችንን በየትኛውም ጊዜ እግዚያብሄር እንደሚያያቸው እየነገርን እርሱን ፈርተው ከጥፋት እነዲጠበቁ ነው ምንናገረው።በውጪ የምናየው ስነምግባር ከፍቷል ወንዱ ከወገቡ በታች ሰውነቱን እያሳየ ይለብሳል ፣ በፌስታል ያስገባል በፌስታል ያወጣል ፣ ፀጉሩን ሴጣናዊ በሆነ መንገድ ያደርጋል በአጠቃላይ ጋጠወጥነት በዝቷል። በኛቤተ ክርስትያን ስር ያሉ ልጆች ወደእዚህ እንዳይገቡ እንመክራቸዋለን፣ ሴቷንም እነዲሁ ክብሯን እድትጠብቅ ፣ነገር ግን የሚያፈነግጥ ሰው ሲገኝ በመጀመሪያ ለብቻው ጠርተን አባቶች እንዲመክሩት ይደረጋል ፤ በዚያ ካልተመለሰ ከአጥቢያው ኮሚቴ ጋር በመሆን በቤተሰቦቹ ፊት እንዲመከር እናደርጋለን ።በሱ ካልተመለሰ ለአካባቢው ሰው አስታውቀን ለ1 ወር በአገልግሎት እናዳይሳተፍ ይቀጣል፤ይህ ከተወሰነበት ቅጣቱን ሲጨርስ ህዝቡንም ቤተክርስትያኑንም ይቅርታ ጠይቆ ይመለሳል።መጨረሻ ግን ተግባሩን ካላስተካከለ ሌላውንም ይንዳያበላሽ እነዲባረር ይወሰንበታል።

(ቃለ መጠይቅ ፣መጋቢ ሀዲስ መላከ መንክራት ቆሞስ አባ አብርሀም ዳኛቸው ፣ሚያዝያ 27 ፣2014)

ገዳሙ ለቆሎ ተማሪዎቹም ሆነ ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎቹ በተለያየ መንገድ ስነምግባር ትምህርት እንደሚሰጥ የነገሩን አባ አብርሀም የተለያየ ስነምግባራዊ ጥሰቶችም ሲያጋጥሙ በቶሎ ለማስተካከል የተለያዩ እርምጃዎች እንደሚወሰዱም ጠቁመዋል፡፡ከላይ ከተቀመጠው ሀሳብ ውስጥ አንድ ለየት ያለች ሀረግ ወስደን እንድንመለከት ፈለግሁ፡፡ ለዚህ ምክንያት የሆነኝም ሀረጓ ለየት ያለች እና ሳቢ በመሆኗ አባ አብርሀም ምን ለማስተላለፍ ፈልገው ተጠቀሟት በሚል ነው፡፡ "በፌስታል ያስገባል በፌስታል ያወጣል" የምትል ነች ይህችን ሀረግ ስንመረምራት ስነምግባራችንን ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ኑሯችንን የምትመረምር ትመስላለች፡፡እንዴት ብለን ብንጠይቅ እንደ ሀገራችን አኗኗር ፣ ባህል እና ወግ ምግብ ሲበላ በማዕድ ቀርቦ ፣ሰው ተሰብስቦ ፣ተባርኮ ፣እየተጎራረሰ ነበር፡፡ አሁን ግን ግለኝነቱ በዛና ማዕድ ተሰብስቦ መቁረሱ ቀርቶ በፌስታል ይዞ መሄድ ተጀመረ፡፡ማዕድ ክብር አጣ! የድሮ አባቶቻችን የማእድን ክብር ሲገልፁ ማእድ እየተቆረሰ አይወራም ፣ ቡራኬ ሳይሠጥ (አባት ባርኮ እንጀራ ቆርሶ ሳይሰጥ ) አይበላም፣ማአድ ከፍ ሳይል ሰው አይነሳም… እና የመሳሰሉትን በማለት ማእድ ክቡር መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ አሁን የ ሁሉ ቀርቶ እንደ ተራ እቃ ምግብን በፌስታል አንጠልጥሎ መሄድ የተለመደ ነገር እየሆነ መምጣቱን እያስተዋልን ነው፡፡ይህም የማህበራዊ ህይወታችን መዳከሙን የሚያሳይ ነው፡፡

"በፌስታል ያወጣል" ኮንዶምን መጠቀም ላይ ያነጣጠረ ሲሆን ኮንዶም መጠቀሙ ብቻ ሳይሆን እሱን ተገን አድርጎ ዝሙት እየተበራከተ መምጣቱን ለማሳየት የተጠቀሙት ይመስላል፡፡አንድ ወንድ በንፅህና አንዲት ሴት አግብቶ እንዲኖር በሚመከርበት ማህበረሰብ ውስጥ ራሴን እየጠበቅኩ እዘሙታለሁ የሚል ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል ብሎ ማሰብ አይቻለም፡፡ስለዚህ ከሀጥያት መቆጠብ እየተቻለ እግዚአብሄር ለቅዱስ ጋብቻ የፈቀደውን ነገር ባዕድ የሆነን ነገር አስገብቶ ማርከስ እንደማያስፈልግ ከተጠቀሙት ቃል እንረዳለን፡፡

በድሮ ጊዜ አንዲት ሴት የገዳሙን ተዓምራት እና የፀበሉን ፈዋሽነት ሰምታ ወደ ገዳሙ ይመጣሉ፡፡ከዚህ አካባቢም የአንድ መነኩሴን ቤት ተከራይተው ይቀመጣሉ፡፡ታዲያ አንድ ጊቢ ሲቀመጡ መነጋገር መግባባት ይመጣል፡፡ ሴቲቱም ቤታቸውን ማፅዳት ምግብ ማብሰል እያለች ወደ ቤታቸው መግባት ትጀምራለችለች፡፡ አንድ ቀን ታዲያ በፈተና ይወድቁ እና ከሴትየዋ ጋር ይሳሳታሉ፡፡ በዚህም በቃ አንችም ለማንም እንዳትናገሪ ብለው እንደ ሚስት ያስቀምጡና መኖር ቢጀምሩም አምላክ ዮሀንስ የተሸፈነውን የሚያይ

የተደበቀውን የሚገልጥ ነውና ስራቸው ውስጥ ውስጡን እየከነከነ ያስጨንቃቸው ጀመር፡፡ታዲያ በመጨናነቅ ብዛት አይምሯቸው ይሰወርና እብደት መጥቶ ከዚ አካባቢ እንደጠፉ፤ሴትየዋም እጅግ በጣም በበሽታ ተሰቃይተው እንደሞቱ ይነገራል፡፡

(ቃለ መጠይቅ አባ ወልደ አማኑኤል ፣ሚያዝያ 27 ፣ 2014)

ይህ ተረክ የሚነግረን የዝሙትን አስከፊነት ነው፡፡ተራኪው"አምላከ ዮሀንስ የተሸፈነውን የሚያይ የተደበቀውን የሚገልጥ ነው" ሲሉ ምንም አይነት ስሕተት ከሰው ቢደበቅ እንኳ ከእግዚአብሄር እንደማይደበቅ ለመጠቆም ነው፡፡ሌላው ተራኪው "እንደ ሚስት" የሚል ቃል የተጠቀሙት ሴትየዋ አብራ የምትኖረው ባልተገባ እና ሴጣናዊ በሆነ መንገድ በመሆኑ የሚስትነት ክብር እንደማይገባት ለማሳየት ይመስላል፡፡

በመፅሐፍ ቅዱስ አስተምሮ ዝሙት ብዙ የኀጢአት አይነቶችን ያካትታል፡፡(ሊቀ ልሣናት ቀሲስ ከፍያለው ጥላሁን ፣25 ፣ 2005)

1/ ዝሙት ማለት ከህጋዊ ጋብቻ ውጭ የሚደረግ ማንኛውም አይነት የሥጋ ግንኙነት እና ሴሰኝነት ወይም አመንዝራነት ዝሙት ይባላል፡፡

2/ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ እና ያልተፈቀደ ስልጣንን ወይም ሹመትን ሥጋዊ ክብርን አብዝቶ መፈለግና መመኘትም ዝሙት ይባላል፡፡

3/ የወንድሙን ሀብት ወይም የሌላውን ሰው ማንኛውም ነገር አጥብቆ መፈለግም ዝሙት ይባላል፡፡

4/ በአምልኮ ባእድ ወይም በአምልኮ ጣኦት ማመን ዝሙት ይባላል፡፡

5/ ከአንዱ ወደ አንዱ ሃይማኖት እያሉ ሃይማኖት መቀያየርም ዝሙት ነው፡፡

በ1ኛ ተራ ቁጥር እንደው አንድ ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ወይም አንዲት ሴት ከሌላ ሰው ባል ጋር ወይም በህጋዊ ጋብቻ ጓደኛው ወይም ጓደኛዋ ካልሆነ ወንድ እና ካልሆነች ሴት ጋር የግብረ ስጋ ተራክቦ በማድረግም ሆነ በዝሙት ሃሳብ እየተቃጠሉ መኖር ዝሙተኝነትና አመንዝራነት ይባላል፡፡ ይህንን የዝሙት ስራ የሚሰሩ ሰዎች በስጋቸው ላይ የነገሰውን የዝሙት መንፈስ ያመጣባቸው ወይም ለዝሙቱ ሃሳብ መነሻ የሆናቸው ለሰው ልጅ ውድቀት ዘወትር በጥፋት መንገድ የቆመው ሰይጣን የሚያመጣው ጠንቅና መዘዝ ነው፡፡የዝሙት ስራ በዚህ

ደካማ ስጋችን የነገሰ ቢሆንም እንኳን ለነፍስ ብቻ ሳይሆን ለሥጋ ጤንነትም እንደማይጠቅም በዘመኑ በአለም አቀፍ ከዝሙት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ደዌም ወይም ወረርሽኝ በሰው ልጅን ሁሉ በጅምላ ሲገልና ሲጨፈጭፍ ተመልክተናል። ስለዚህ ዝሙት ነፍስንም ስጋንም የሚገል መሆኑን ከኛ በላይ ሌላ ማስረጃ አያስፈልገንም። እንግዲህ ዝሙት ወይም አመንዝራነት በቃላት ስንገልፀው የሚያሳፍር በተግባር ግን ሁሉ ሰው የሚፈልገውና በተግባር የሚያውለው የሁሉ ሰው ፈተና ነው። ይህ ሲባል አንዳችን ፃድቅ ወይም ከደሙ ንፁህ ሆነን ሌላው ደግሞ በዝሙት ኀጢአት ተጠያቂ በማድረግ ሌሎቹን በመተቸት እጃችንን የምንቀስርበት መንገድ አይደለም። የዝሙት ስራ በሰው ስነልቦና ውስጥ የሚያደርሰው ፈተና እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በሥጋ ያቃታቸው እንኳን በልባቸው ይመኙታል ባፋቸው ያወሩታል። ስለዚህ የዝሙት የመነሻው ምንጩ ሃሳብ ነው። ከሃሰብ ሲወጣ በአንደበት ይነገራል፣ ከአንደበት የተነገረው ደግሞ ጊዜ ሲገጥም በተግባር ይውላል። ስለዚህ የመጀመሪያው የዝሙት ድርጊት ፅንሱ ማሰብ ነው። ብዙዎቻችን በሃሳብና በአፍ በዝሙት ጉዳይ ላይ አብዝቶ የማይነጋገርና በሃሳቡ የማይቃጠል የለም ማለት ይቻላል።(ሊቀ ልሣናት ቀሲስ ከፍያለው ጥላሁን ፣ 26-28 ፣ 2005 )

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ወይስ አመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግስት እንዳይወርሱ አታውቁምን፥ አትሳቱ ሴሰኞዎች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝራዎች ወይም ቀራጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሰሩ ወይም ሌባዎች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደዚህ ነበራችሁ ነገር ግን በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፤ ታድሳችኋል ፀድቃችኋል" በማለት የዝሙትን አይነት እና ዝሙት ከፍተኛ ኀጢአት መሆኑን ከዘረዘረ በኋላ እግዚአብሔርን በመፍራት ወደ ንስኀ ስንመለስ እንዴት ከኀጢአታችን እድፍ እንደምንታጠብና እንደምንቀደስ እንደምንፀድቅም አስተምሮናል። (ቀኛ ቆረ 6፥9፤10)

ነገር ግን ማጥፋታችን ሳያንስ ስራችንን ደብቀን እግዚያብሄርን ለማታለል መሞከር ሌላ መዘዝ እንደሚያመጣ ከተረኩ እንረዳለን ከዚህ ሀሳብ ጋር ተያይዞ የሚነሳን አንድ ተረክን እንመልከት

> አንድ በምንኩስና ህይወት የሚኖሩ ሰው በአንድ አጋጣሚ የቤተ ዘመድ ድግስ ላይ ተገኝተህ ቡራኬ መስጠት አለብህ ብለው ዘመዶቻቸው ወደከተማ ይወስዷቸዋል።መነኩሴው ድንግል እና ታቦት ተሸካሚ ንጹህ ሰው ነበሩ። ታድያ በመሀል ከተማ እንደሄዱ ከፀሎት ቢዘናጉ በፈተና ድል ይነሳሉ። ይህ ከሆነ በኋላ በስራቸው በጣም የተፀፀጹት እኚህ አባት ወደ ስፍራቸው ተመልሰው

> አልቅሰው በንስሀ ከታጠቡ በኋላ ከዚህ በኋላ በአለም ምንም የለኝም ብለው ወደ በረሀ ወርደው በብህትውና መኖር ጀመሩ፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ አባባ ደርብ ፣ ግንቦት 5 ፣2014)

በገዳሙ  አካባቢ በሚገኘው ሰፊ በረሀማ ቦታ አለምን ጥለው በብህትውና የሚኖሩ ሰዎች መኖራቸው ይነገራል፡፡"ይህን ያህል ናቸው ብለን ቁጥራቸውን አናውቀውም ፣ ከሰውም አይነጋገሩም አይታዩምም ግን አንዳንድ ችግሮች ሲኖሩ እንድንፀልይ እና የተለያዩ መልዕክቶችን ፅፈው ይልኩልናል፡፡"(አባ በለጠ ሞላ ግንቦት 1 ፣  2014)ይህን ተረክ ከመጀመሪያው ተረክ የሚለየው በሁለተኛው ተረክ ላይ የተጠቀሱት አባት ጥፋታቸውን  አምነው ያስቀየሙትን ፈጣሪያቸውን ለመካስ ያደረጉትን ጥረት ስለሚያመለክተን ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በገዳሙ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ያልተገባ ነገር በሚያደርጉበት ወቅት ገዳሙ የተላያዩ ቅጣቶችን ይጥላል፡፡ ለምሳሌ

> አንድ በዚህ የሚኖር ሰው ከትዳሩ ውጪ ባለ ግንኙነት አንድ ልጅ ይወልዳል ፡፡ ሚስቱም ሰምታ በጣም ታዝናለች ፣ ሰውየው በትዳሩ ውስጥ ሶስት ልጆችን አፍርቷል ሚስቱ በህይወት አለች፡፡ታዲያ የተወለደውን ልጅ ክርስትና ሊያስነሳ ሲጠይቅ ይሄ ዝሙትን በአካባቢያችን የሚያስፋፋ ተግባር ስለሆነ በዚህ ቤተ ክርስትያን ልጁን ክርስትና ማስነሳት አትችልም ብለው ከለከሉት ሴትየዋንም የሰው ባል እንደሆነ እያወቀች ስህተቱን በመፈፀሟ ስህተተቷን አምና ንሰሀ ከመግባት ይልቅም ሰውየውን ይዛ በመቀመጧ የንስሀ አባቷ ልጅነቷን አነስተዋል፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ፣ አባባ ደርብ ፣ ግንቦት 5 ፣2014)

ከላይ በተረኩ እንደተገለፀው ሰዎቹ በሰሩት ስህተት ምክንያት እና ስህተታቸውንም በለማመናቸው ምክንያት የተቀበሉት ቅጣት በብዙ መንገድ የሚያስተምር ነው፡፡የተወለደው ልጅ በዛ ደብር ክርስትና ያለመነሳቱ ስህተቱን የሰሩትን ሰዎች ከስህተታቸው የሚያነቃ ቅጣት ከመሆኑ ባለፈ ሌላው ሰው ይህን አይነት ስህተት ብፈፅም እንህዲህ አይነት ቅጣት ይደርስብኛል ፣ከማህበረሰቡም እገለላለሁ ብሎ እንዲፈራ ያደርገዋል፡፡ሌላው ቅጣት ደግሞ ከንስሀ ልጅነት መሰናበት ሲሆንበኦርቶዶክስ አስተምህሮ (በሲራክ 6፣6) ላይ "ብዙ ሰዎች ወዳጆች ይሁኑህ ከብዙዎች አንዱ ምክርህን የምትነግረው ከልቡናህ ጋር አንድ ይሁን፡፡" የሚለው ቃል ምእምናን ስለ ሐይማኖትና ምግባር የሚያስተምሯቸው ብዙ ካህናት ሊኖሩዋቸው ቢችሉም ከብዙዎች አንዱ ግን ንስሃቸውን የሚናዘዙለት መምህረ ንስሃ ሊሆናቸው እንደሚገባ ያሳውቃል፡፡

አዳም በገነት ለሰባት አመታት ከቆየ በሁዋላ በዲያቢሎስ ተፈትኖ እንደወደቀ ፤ለሰው በሃጢያት መፈተንና መዉደቅ የሚፀናበት ዕድሜ ከሰባት አመት ጀምሮ ስለሆነ ወደ ንስሃ አባት መቅረብ ይኖርበታል፡፡በምክረ ካህን መኖር ራሱ ትልቅ መንፈሳዊ ማእረግ ነው የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ከብሉይ ኪዳን ሰዎች የሚከብሩትን ያህል በምክረ ካህን የሚኖሩ ምእምናን ከአማኒያን በላይ የከበሩ ናቸዉ፡፡(ማቴ20 ፣2 )ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ 12 አመቱ ከመምህራን ጋር መገናኘቱ እኛም ከልጅነታችን ጀምሮ ከ መምህራን አባቶች ጋር እነድንገናኝ አብነት ይሆን ዘንድ ነዉ፡፡

ሀጢያትን ለእግዚአብሄር በካህን በኩል መናዘዝ መፅሃፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለዉ ጠቃሚ ጉዳይ ነዉ፡፡ እግዚአብሄር አዳም በበደለ ጊዜ "አዳም ሆይ ወዴት ነህ?" ብሎ የጠየቀዉ አዳም እንዲናዘዝ ስለፈለገ እንጂ አዳም ያደረገዉን ሳያዉቅ ቀርቶ አልነበረም፡፡ "እም ቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም የአምር ግብሮ" "አዳምን ከመፍጠሩ በፊት ስራዉን ያዉቃል" እንዲል፡፡ አዳምም እግዚአብሄር በጠየቀዉ ጊዜ "ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ" በማለት ተናዝዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ቦታዎች ሰዎች ሀጢያታቸዉን ይናዘዙ እንደነበር በመፅሀፍ ቅዱስ ተገልጧል፡፡ (ሐዋ 19-18 ፣ ማቴ3 5-6 ፣ ዘሌ 5-16 ፣ ኢያ 2-19)፡፡ ይሁን እንጂ "ሀጢያቴን ለመተዉ ከፈቀድኩ አይበቃም ወይ? መናዘዙ ለምን አስፈለገ?" የሚሉ ሰዎች አሉ ሀጢያትን በካህን ፊት መናዘዝ ግን የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት (ሊቀ ልሳናት ቀሲስ ሄኖክ ወልደ ማርያም 2014)፡-

- ሀጢያትን በዝርዝር በካህን ፊት መናዘዝ ዳግመኛ በዚያ ሀጢያት ላለመያዝ ሀይልን ይሰጣል፡፡ ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅ "በበደሉ ላይ ድፍረትና ሽንገላን የሚጨምር (ሀጢያት ሰርቶ እንዳልሰራ ዝም የሚል) ከዚያች ሀጢያት መጠበቅ አይችልም፡፡ እርስዋን በምትመስል ሀጢያት ከመዉደቅም አይድንም" እንዳለ፡፡
- ንጉስ የሚሽረዉና የሚሾመዉን ግራና ቀኝ አቁሞ የሚሽረዉን ወቅሶ የሚሾመዉን አሞግሶ እንደሚያከብር ያለፈ ሀጢያታችንን በካሀኑ ፊት ስንዘረዝርም ያለፈዉን ሀጢያታችንን ሽረን በሚመጣዉም ህይወት ያንን ሀጢያት ላለመድገም እየወሰንን ነው፡፡
- ኑዛዜ ያሳቅቃል፡፡ መሳቀቁ ደግሞ ለሰራነዉ ሀጢያት ዋጋ ነዉ፡፡ በፍርድ ቀን ጌታ በሰማይ መላእክት ፊት ሀጢያታችንን ገልጦ ከሚያሰቅቀን ይልቅ እኛዉ እራሳችን እዚሁ እንደኛዉ ደካማ ሰዉ በሆነው በካሀኑ ፊት በመናዘዝ ለሰራነው እጅግ ግዙፍ ሃጢያት የምንቀበለው ኢምንት ቅጣት ነው፡፡

- በሽታውን የደበቀ መድሃኒት የለውም እንደሚባለው የነፍሱን ደዌ ሀጢያቱን የሚደብቅም እንዲሁ መፍትሄ አያገኝም። የካህኑን ፀሎትና ምክርም ያጣል። “ሀጢያቱን የሚደብቅ /የሚሰውር አይለማም፡ የሚናዘዛትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛል” እንደተባለ ።ምሳ8-13

ሀጢያትን ለካህን መናዘዝ ለእግዚአብሄር አለመናዘዝ አይደለም። ሀጢያትን ለካህን መንገር ለእግዚአብሄር መናዘዝና ክብር መስጠት ነው። እያሱ እንዳለ “ልጄ ሆይ ለአምላክ ክብርን ስጥ፡ ለእርሱም ተናዘዝ፡ ያደረግከውንም ንገረኝ አትሸሽገኝ” (ኢያሱ 7-19)። ኢያሱ “ክብርን ስጥ” ያለው ለእግዚአብሄር: “ተናገር” ያለው ግን ለራሱ መሆኑ ሀጢያትን ለካህን መናዘዝ ለእግዚአብሄር ክብር መስጠት እንደሆነ ያሳየናል። አበዉ ካህናትም ኑዛዜን ከተቀበሉ በ`ላ “እግዚአብሔር ይፍታህ” እንጂ ”ፈትቼሃለሁ ” አይሉም። ይህም ምንም በነሱ ፊት ብንናገርም ሰሚዉም ሆነ በእነርሱ እጅ ስርየት የሚሰጠዉ እርሱ ባለቤቱ ስለሆነ ነው። ”ሁለት ወይም ሶስት በሚሆኑበት በዚያ በመካከላችሁ እገኛለሁ” ብሎ ቃል የገባ አምላክ በአናዛዚው ካህንና በተናዛዚው ምእምን መካከል ሆኖ ይሰማል፡ ስርየትንም ይሰጣል።

ስለዚህ ይህ ቅጣት ለአንድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ እጅግ በጣም ትልቅ ቅጣት መሆኑን ያስገነዝበናል።

## ምዕራፍ አምስት ፤ ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሣው በደብረ ምጥማቅ ሸንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ለገዳማውያኑና ለማህበረሰቡ ስነምግባርን ከማስተማር አንፃር የሚኖራቸውን ፋይዳ መፈተሸ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የፅሁፍ መረጃዎችን በመመልከት ቃለ መጠይቅን እና የቡድ ውይይትን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

መረጃዎቹን በፅሁፍ ማስታወሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፍቶ ግራፍ እና በመቅረጸ ድምፅ አማካይነት ተቀርጸዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም የተለያየ ማጣቀሻ መፅሀፍትን መሠረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡በጥናቱ በገዳሙ የሚነገሩ ተረኮች ስነምግባርን ከማስተማር አንፃር ዘርፈ ብዙ ሚና እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በጥናቱ አምስት ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው በፎክሎር ትምህርት ክፍል የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት በማሟያነት የተሰሩ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎ እና ልዩነት ተዳሷል፡፡ በዋናነትም ይህ ጥናት በሌሎች ጥናቶች ላይ ያልተመለከትነውን እና ወቅታዊ የሆነውን ሥነምግባራዊ ፋይዳ በማንሳት ሌሎች ጥናቶች ላይ እንደ ክፍተት የተመለከትነውን በዚሀ ጥናት ለመሙላት ተሞክሯል፡፡

መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ ከተሰጡት ትንታኔዎች በመነሳት የሚተረኩት ተረኮች የተወሰኑት የገዳሙን አመሰራረት እንዴት እንደተመሰረተ የሚገልፁ ናቸው፡፡ በዚህም የቅዱስ ዮሀንስ ታቦት ከመንዝ ወደ ቡልጋ ከቡልጋ ወደ ሸንኮራ አባ ሰርፀወልድ እንዳመጡት እና በዋሻ ለሰላሳ አመታት ተቀምጦ ከቆየ በኋላ በራዕይ ከዋሻው እንዲያወጡት ትዕዛዝ ታዘው እሳቸውም ትዕዛዙን አክበረው ገዳሙን መስርተዋል፡፡ከዚህ ተረክም ታዛዥነት ለክብር እና ለቅድስና እንደሚያበቃ በምድር ስንኖርም ማህበራዊ ደረጃችንን እንደሚጨምር የሚያስተምር ነው፡፡

በአጠቃላይ በገዳሙ የሚነገሩት ተረኮች ኢትዮጵያዊ የሆኑ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ያስቀመጡልንን ስነ ምግባር የሚያስተምሩ ማለትም ታላላቆችን ማክበር ፣መታዘዝ፣ የገባነውን ቃል ማክበር መጠበቅ ፣ ታማኝነት ፣ የሰው የሆነን ነገር አለመንካት ፣አንጉል የሆኑ ሱሶችን አለመጠቀም ፣ወገኖቻችንን መውደድ እና ለችግሮቻቸው መፍትሄ ማበጀት ፣ ሀይማኖታችንን ማክበር ፣ለፈጣሪ መገዛት ፣ጥፋት ስናጠፋ ጥፋቶቻችንን አምነን ይቅርታ መጠየቅ እና የመሳሰሉትን ስነምግባራዊ ትምሀርቶች በተለያየ መንገድ

የሚያስተምሩ እና እነዚህ ስነምግባራዊ  ጥሰቶች በሚፈፀሙበት ወቅት ፈጣሪ በህይወታችን መጥፎ ነገሮችን በመላክ እንደሚቀጣን እና እንደሚያስተምረን በመግለፅ የገዳሙን ማህበረሰብ ስነምግባር እንደሚ ቆጣጠሩ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

## ዋቢ መፅሀፍት

ሉሌ መልአኩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1997 ዓ . ም።

ሊቀልሳናት ቀሲስ ሄኖክ ወ/ማርያም። ክርስትያናዊ ስነ ምግባር ።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን ፣ አ.አ 2014 ዓ.ም ።

መሪማ መሀመድ።"የእንጦጦ ሀመረ ኖኀ ኪዳነ ምህረት ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት ።"አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ ዱግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት ፣ 2009 ዓ.ም።

ምህረት ተስፋዬ። "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት"። የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ ዱግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት ፣ 2003 ዓ.ም

ሰለሞን ተሾመ።ፎክሎር ምንነቱ እና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ።ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኀበር፣ አዲስ አበባ ፣2007።

ቴዎዴሮስ ገብሬ። በይነ ዱሲፕሊናዊ የስነ ፅሁፍ ንባብ። አዱስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2001ዓ.ም።

አቤል አሰፋ። "የጣራ ገዳም፣ ዋሻ እንድርያስ እና ወይን ዋሻ ተክለሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናትና በዙርያቸው የሚነገሩ ተረኮች" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ ዱግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት 2008 ዓ.ም።

አንተነህ አየነው።" በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና "።በጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ ዱግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት ፣ 2011።

ወንደሰን ሞላ "በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት " በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ ዱግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት ፣ 2007 ዓ.ም ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ።የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አርትስቲክ ማተሚያ ፤አዲስ አበባ፤ የካቲት 1993 ዓ.ም ።

ዘሪሁን አስፋው። የሥነ - ፅሁፍ መሠረታውያን። ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤አዲስ አበባ፤ 2004 ዓ .ም ።

የይሖዋን መንግሥት የሚያስታውቅ መጠበቂያ ግንብ። የይሖዋ የኢንተርኔት ቤተ መፅሀፍት ፤ 1999 ፤ያልታተመ።

የዘላለም አምላክ። የካቶሊክ ቤ/ክ መፅሄት ፤ 2014።

ያረጋል አበጋዝ። ፍኖተ ቅዱሳን። ማተሚያ ቤቱ አሌተገለፀም፤1995 ዓ.ም።

ደስታ ተክለ ወልድ ። ዐዲስ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ ፤1962 ዓ . ም ።

ፈቃደ አዘዘ።የሥነ ቃል መምሪያ። አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፤አዲስ አበባ ፤ 1992 ዓ.ም።

Bascom, William. "The Form of Folklore: Prose Narratives". The Journal of American Folklore. VOl.78.No307. (Jan-Mar 1965) P3-20 http:/www.Jstor.org.Mar 22, 2006.

Bell, Catherine M. Ritual Theory and Ritual Practice. New York. Oxford University press. 1992.

Ben-Amos. Dan. Ritual:Perspective and Dimentions. New York. Oxford University press.1997.

Bruner, Jerome. Acts of Meaning. Harvard University Press.USA. 1990.

Danielson, Larry. "Religious Folklore" In Folk Groups And Folk Genres : An Introduction . Logon; Utah State University Press, 1986.

Deign, Linda. "Oral Folklore, Oral Narretives". In Folklore And Folklife ; Richard M. Dorson(ed) Chicago And London; The University of Chicago Press, 1972.

Dorson,Richard M. (Ed.) Folklore and Folk Life: An Introduction.Chicago: University Of Chicago Press,1986.

Finnegan, Ruth. Oral Literature in Africa, Nairobi: Oxford University Press,1970. Oral Traditions and the Verbal Arts: A Guide To Research Practices. New York. Rutledge Publisher.1992.

Goldstein, Kenneth. A Guide For Field Work in Folklore . Habtboru; Published By Gale Research Company, 1964.

Oring, Elliot . Folk Groups And Folk Genres : An Introduction . Logan; Utah State University Press, 1986.

Ritamani Das. Psychoanalytical Study of Folktale. IOSR Journal Of Humanities And Social Science. 2014

Sims, Martha C. And Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction To The Study of People And Their Tradition. Logan; Utah State University Press, 2005.

www . jw .org

## አባሪ 1

# የሽንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ምስአል ወምስጋድ የእናቶች አንድነት ገዳም አመሰራረት

የሽንኮራ ቅዱስ ዮሀንስ ምስአል ወምስጋድ የእናቶች አንድነት ገዳም በ1997 ዓ.ም የሰሜነን ሸዋ ሀገረ ስብከትሊቀ ጳጳስ በነበሩት ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም ከወረዳ እስከ ክልል ድረስ በመሄድ 42 ሺ ካሬ ሜትር አስፈቅደውገዳሙን በቡራኬ ምስአል ወ ምስጋድ ብለው የእናቶች የአንድነት ገዳም የንፍሮ ገዳምነቱን እንዳይለቅ በግዝት ቃላቸውን አሳልፈው የእናቶች መነኮስያት በገዳሙ እንዲኖሩ አድርገዋል።

ይህ ገዳም በ1997 በአቡነ ኤፍሬምበግዝት ከተገደመ በኋላ እንደ አባ ጳኩሚስ ስርአት ገዳሙን በደውል ተደውሎ በአንድ አዳራሽ በገበታ ቤት እንዲመገቡ ስርአት ሰርተዋል።መነኮስያቱም ይህንን ስርአተ ገዳሙን አፅንተው በደውል በአንድ ገበታ የሚመገቡ ናቸው።የስራ ድርሻቸውንም በአንድነት ስፌት በመስፋት ፣ሽመና በመስራት እንቅብ ፣ሌማት በመስፋት ፣አትክልት በመትከል እና ለሽያጭ በማቅረብ ለገዳሙ ገቢ ያስገባሉ።በቀን ሰባት ጊዜ በጸሎት ቤት ተሰብስበው የጋራ ፀሎት እያደረሱ ይኖራሉ።

## አባሪ 2

## ከስፍራው የተሰበሰቡ ተረኮች

*ተረክ አንድ*

*ሴትዮዋ አራት ወንድ ልጆች ወልዳ በአዲስ አበባ ትኖራለች ። ብዙ ጊዜ ቤተክርስቲያን እንደማትሄድ ገልፃልኛች። ይሁንና አንድ ቀን ልጆቿን ለማዝናናት በወጣችበት ወቅት አንደኛው ወንድ ልጅ ድንገት ይታመምባታል። ህመሙም አስደንጋጭ ስለነበረ ባቅራቢያዋ ወደሚገኝ ሆስፒታል ብትወስደውም ወደ ከፍተኛ ሆስፒታል ይጻፍሊታል። እዚያ በመሄድም ለዓመታት የበሽታ መከላከያ የሆነው የደም ሴሉ አልቋል በሚል በሆስፒታለ ህክምና ሲታገዝ ቢቆይም ሊሻለው አልቻለም። አንድ ቀን ነው፤ ሴትዮዋን አልግባባትም። እንዱያው አጠገቤ መጥታ ልጅሽ እንዲድን ለምን ሽንኩራ ዮሀንስ ይዘሽው አትሄጂም ? ስትለኝ ሳላቅማማልጄን ይዠ ተነሳሁ።ሰዎችን እያጠያየኩ በነጋታው እለት መጣሁ። ስመጣ እንደዛሬው የልደታ ንግስ በዓል ነበር ብዙ ሰው አለ።እኔም ሌጄን ይዤ እያለቀስኩ ከአንድ ከሚያስተምሩ አባት ዘንድ ሄድኩ።ምን ሆነሻል ? ሲሉኝ ልጄ ያለበትን ሁኔታ ነገር ኳቸው። ሰባት ቀን አስጠምቂው ብለውኝ ቤት ተከራየሁና አስተካከልኩ ። በነጋታው ጠበል በር ሊይ ስንደርስ ለዓመታት ያልፈሰሰኝ ደም በመፍሰሱ ልጄን እንዴት እንደማስጠምቅ ጨንቆኝ ሳለ አንድ ወጣት እንዳይመለስ እሱ ብሎ ይዞልኝ ገብቶ ልጄን አስጠመቀልኝ። እቤት ስመለስ ግን ደሙ መፍሰስ አቁሞ ነበር። በኋላም ለሰባት ቀን ልጄ ሲጠመቅ በእጅጉ ተሠቃይቷል። ይህ የሆነው ለካ ! ርኩስ መንፈሱ ከውስጡ ሊወጣ ሲል ነው፡ ፡ እግዚአብሄር ይመስገን ! አሁን ድኖልኛል።ከዚያ የሥቃይ ጊዜ በኋላ ከቤተክርስትያን ተለይቼ አላውቅም፤ ከቻልኩ እዚ ካልቻልኩም በአካባቢዬ በወር በወር ሌጆቼን ይዤ ቅዳሴውን አስቀድሼ ነው የምሄደው። ( ወ/ሮ ዙርያሽ ተክሉ ግንቦት 6፣ 2014 ዓ . ም ) ።*

*ተረክ ሁለት*

*ለዓመታት በህመም ስትሠቃይ የነበረች ወጣት የተለያዩ የህክምና ተቋማት ጋራ ብትሄድም ከህመሟ መዳን ባለመቻሏ ተስፋ በቆረጠችበት ሰዓት በሰዎች ጠቋሚነት ወደዚህ መጥታ ጠበሉን በመጠመቅ በመጨረሻም ከህመሟ ተፈውሳለች።(ዲ/ን ፅጉ ተስፋ ግቦት 3፣2014)*

*ተረክ ሶስት*

*አንዲት ሀብታም ሴት ከድሬዳዋ ትመጣለች።ነቀርሳ ይዟት ነበር የመጣችው እዚህ ተጠምቃ ካዳንከኝ ዝናህን እየዞርኩ እነግራለሁ ብላ ትሄዳለችለች።ከዛ በኋላ በሽታው ጠፋ እሷም እንደቃሏ እስከ አዲስ አበባ በየቤተክርስያኑ እየዞረች ያደረገላትን መሰከረች።ከዛ በኋላ ነው እነግዲ ሰዉም እየበዛ ከሙሉ ኢትዮጵያ መጉረፍ የጀመረው።(አብዬ ተረፈ ፀጋው ግንቦት ፣1 ፣2014)*

ተረክ አራት

እግሩ አልራመድ እያለው ማስቸገር የጀመረው በልጅነቱ ነበር፤ በኋላ ላይ ግን አልራመድ ማለት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሆነን ህመም እያስከተለበት መጣ። በሰዎች ጠቋሚነት ከጎጃም ድረስ በመምጣት ጠበሉን በመጠመቅ፣ ከጠበሉ በመጠጣት፣ ለአሥራ ሦስት ዓመታት ያክል ሠርክ በመጸለይና ከጠበሉ ድህነት እንደሚያገኝ በማመን ቆየ። አንድ ቀን አንደኛው እግሩ የተለየ መልክ በማሳየት፣ የሚሟ በመምሰል፣ በመጨረሻም በመፈንዳት እሾህ የበዛበት አውሬ መሰል ነገር ወጣለት። የኋላ ኋላም ቆሞ ለመሄድ ችሎ አሁን አዚሁ አግብቶ ወልዶ ጠዋፍ በመሸጥ እየተዳደረ ነው ያለው።( ዲ/ን ሀይለ ገብርዔል ግንቦት 3፣2014)

ተረክ አምስት

ሙስሊም ሰውዬ ነው። የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ለበርካታ ጊዜያት በመቆየቱ ሰዎችን አጠያይቆ ወደ እዚህ  ይመጣል። ወደዚህ ሲያመጡት ታዲያ በነብስ ተይዞ ትንፋሹ ብቻ ትር ትር ነበር የምትለው አዚህ እንደመጣ ፀበሉን መጠጣትና መጠመቅ ጀመረ በየጊዛው የተለያዩ ስሜቶችን ያሳይ ነበር፤ በኋላም በዮሀንስ በጠበሉ ተአምር ከሆዱ ጠቀምጦ ሲያሰቃየው ቆይቶ ከሆዶ ውስጥ እባብ መሰል ወጥቶለት ሄዷል ።(አባ በለጠ ሞላ ሚያዝያ 27፣2014)

ተረክ ስድስት

ቀኑን ሙሉ ህዝቡ ሲጠመቅ አልተቋረጠም በጣም ደክሞኝ ነበር።በመሀከል ወደ አስር ሰዓት ላይ አካባቢ አንድ ሰው እየጠመቅኩ እጁ ጣቶቹ ከመዳፉ ጋር ወደ አንጓው የተጣበቀ ነበር። ታዲያ ልክ መስቀሉን እንደ ነካው እሳት እንደበላው ሰው ዋይ ብሎ በጩኸት ሲያናጋው ካለሁበት ሰመመን ብቻ ነቅቼ መስቀሉን ብድግ አደረግሁት በኋላ ባይ ጣቶቹ ተዘርግተው ይንቀሳቀሳሉ።የሚገርመው ጣቶቹ ስልል ብለው ከመቅጠናቸው ውጪ ምንም አልሆኑም ነበር።(አባ በለጠ ሞላ ሚያዝያ 27 ፣2014)

ተረክ ሰባት

ወደዚህ የመጣሁት ሰውነቴን በሙሉ እስከ ፊቴም ጭምር ለምጥ መቶኝ ነው።የጀመረኝ አምስት አመት በፊት አካባቢ ነው።አንገቴ ላይ ማሳከክ ጀመረኝ፤ከዛ ህክና ሄድኩኝ የሚቀባ መድሀኒት ሰጡኝ።እሱን እየተቀባሁ ብጠብቅ ለውጥ የለም ጭራሽ ለምጥ እየሆነ ሙሉ አንገቴን ወረሰው። ብዙ ሀኪም ቤት ዞርኩኝ ብዙ አይነት መዳኒት ዋጥኩ ተቀባሁ ለውጥሚባል የለም ።ከዛ አንድ ጓደኛዬ ወደ ሸንኮራ ዮሀንስ ሂድ እዛ ብዙ የቆዳ በሽታ ያለባቸው ድነዋል አለኝ።ስመጣ ብዙ እንደምታይው ለምጥ ያለበት ሰው አለ።ከዛ እነሱን ሳይ እየተሸላቸው

እንደሆነም ሲነግሩኝ እየበረታሁ መጣሁ አሁን ምስጋና ለሱ ፀበሉን እየተጠመቅኩ እምነቱን እየተቀባሁ እየጠፋልኝ ነው።(ያሬድ መላኩ ግንቦት 8፣2014)

ተረክ ስምንት

ሌጁ ወጣት ነበር፤የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነበር የሚሠራው። በኋላ ላይ ግን በደረሰበት የመኪና አደጋ የተነሣ መራመድ ባለለመቻሉና በህክምና ሊስተካከልለት ባለመቻሉ ወደ ገዳሙ በመምጣት በመምጣት ዘወትር ይጸልይ ነበር እምነቱን እያስመጣ ይቀባ ነበር ።ታዲያ አንድ ቀን መዳኛው ቀን ደርሶ ሁለት አመት እዚህ ተቀምጦ በሁለተኛው አመት ጠዋት የዮሀንስ ቀን እግሩ ተፈቶለታል።(እማሆይ ፅጌ ማርያም ሚያዝያ 28 ፣2014)

ተረክ ዘጠኝ

በገዳሙ ግቢ ውስጥ ውስጧ ሰይጣን ሰፍሮ ነው ተብሎ ስትጮህና ስትዘምር የነበረችውን ወጣት በመስቀሌ ግንባሯን በመምታት ልቀቅ! ብዬሃለሁ፤ ልቀቃት! ስለው ሰይጣኑ በልጅቷ ላይ አድሮ ብዙ ካሠቃያት በኋላ ሄጃለሁ፤ ለቅቄያታለሁ አለ።በኋላም ልጅቷ ጤናዋ ተመልሶላት ወደ ገዳሙ ብዙ ጊዜ ትመጣ ነበር። (አባ በለጠ ሞላ ሚያዝያ 27፣2014 ዓ.ም)።

ተረክ አስር

አንዲት ሴት ነበረች ሁለት እግሮቿ ከጊዜ በኋላ በመጣ ነገር ያብጣሉ። ብዙ ቦታዎች ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ ህክምና ትሞክራለች ነገር ግን ምንም በሽታ እንደሌለባት ነበር የሚነግሯት በመጨረሻም ወደዚህ ገዳም መጥታ ፀበል ይታዘዝላት እና ፀበሉን መጠመቅ እምነቱን መቀባት ትጀምራለች። ልክ በስድስተኛው ቀን እግሮቿ መፈነዳዳት ይጀምራሉ።( ዲን ፅጉ ተስፋ ግቦት 3፣2014)

ተረክ አስራ አንድ

ምኖረው መትሀራ ነው።ወደዚህ መጀመሪያ የመጣሁት ኪንታሮት አሞኝ ነበር። መጥቼ አንድ ወር ተጠምቄ ተስዬ ወደ ሀገሬ ተመለስኩ።ከዛ ጠፍቶልኝ በሰላም ስራዬን እየሰራሁ ቤት ሰርቼ ልጆቼን እያሳደግኩ እያለሁ ስለቴንም ረስቼ አንድ ቀን እንኳ ለንግስ ሳልመጣ ገንዘብ ብቻ እያሳሰበኝ ስኖር በአስር አመቱ ባለቤቴ ተለወጠብኝ ፣ተጣላንና ቤቴን በላዬ ላይ ሽጦ ልጄን ይዤ ወጣሁ።በዛም ተናድጅ ሳለቅስ ሳለቅስ አይኔ እየታመመ መጣ።ወወደ ሀኪም ቤት ስሄድ

በመጀመሪያ ሞራ ነው መገፈፍ አለበት ብለው አስተኙኝ ከዛ ገፈፍን ብለው ወጣሁ፡፡ጭርሱኑ ማየት አቃተኝ በሁለተኛ ፈረንጆች መጡ ተብሎ ሄድኩኝ እነሱም የአይንግፊት ብለው ቀዶ ጥገና አደረጉ ግን ለውጥ የለም ፡፡በኋላ አንድ ቀን ነብስ አባቴ ተይ እስቲ የባሰ አለ አታማሪ ብለው ሲመክሩኝ ሁሉንም አስታወስኩኝ፡፡ ይኸው እዚ መጥቼ ንስሀ ገብቼ በእምነቱ በጠበሉ ድኜ አሁን እዚሁ ከደጁ አልርቅም ብዬ አለሁ፤ እዚሁ ነው ምኖረው፡፡(እማማ አስካለ ማርያም ግቦት 4፣ 2014)

ተረክ አስራ ሁለት

በድንገት ነው የታመምኩት አራስ ልጅ ይዤ ልሞት ስል ባለቤቴ እኔ ስትሞቺ አላለቅስም ሸንኮራ ይዤሽ እሄዳለሁ፡፡ከሞትሽም እዛው ሙቺ ብሎ ይዞኝ መጣ ለሃያ ቀን ተጠመኩኝ በሀያ አንደኛው ቀን ጠዋት ተጠምቄ መጣሁ ቁጭ ብዬ ፀበሉን እየጠጣሁ እያለ ተናነቀኝ ጉሮሮዬን ያዘኝ መናገር ተሳነኝ ዘግቶኝ ዋለ እኔም ፀበሉን አላቆምኩም ስጠጣ ውዬ ልክ አስራ አንድ ሰዓት ላይ አስመለሰኝና እንቁራሪት ነው የወጣልኝ፡፡(ወለተ ማርያም ግንቦት 1፣ 2014)

ተረክ አስራ ሶስት


ታማ መጥታ አልቆየችም ሰባት ቀን ተጠምቃ እንደተመለሰች ስትመረመር የነበረባትን ካንሰር ዮሀንስ ቆርጦላት ምንም የለብሽም ተብላ መጥታ መስክራለች፡፡(ዲ/ን ሀይለ ገብርዔል ግንቦት 3፣2014)

# አባሪ 3

## ከቦታው የተገኙ ምስሎች




የሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም አዲሱ ህንፃ ቤ/ክ




የሸንኮራ ዮሀንስ ገዳም ምስአል ወ ምስጋድ የሴቶች ገዳም የተመሰረተበት መሰረተ ድንጋይ









በሴቶች ገዳም የተግባር ቤቶች የሚከወኑ ስራዎች

# አባሪ 4

## መረጃ ለመሰብሰብ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. አመሰግናለሁ!

2. ስምዎትን ማን ልበል?

3. የስራ ድርሻዎ /ሃላፊነትዎ/ ምንድን ነው? ቢነግሩኝ?

4. የገዳሙን ታሪካዊ አመሰራረት በተመለከተ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ? በነማንስ ነው የተመሰረተው?

5. ስነ ምግባር እንደ ኦርቶዶክስ አስተምህሮ እንዴት ይገለፃል?

6.ለገዳሙ ማህበረሰብ በተለይ ደግሞ ለቆሎ ተማሪዎች እና ለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች የስነምግባር ትምህርቶችን በምን መልኩ ይሰጣል ?

7 የገዳሙ እና የአካባቢው ማህበረሰብ ቁርኝት ምን ይመስላል?

9.የአካባቢውን ማህበረሰብ ስነምግባር እንዴት ይመለከቱታል ለዚህስ የገዳሙ አስተዋፅኦ ምንድነው?

10 በዚህ አካባቢ የተለያዩ ስነምግባር ጥሰቶች ሲያጋጥሙ ለማስተካከል እና ለመቆጣጠር የሚሞከረው በምን መንገድ ነው?

11 ስለሰጡኝ መረጃ እና ጊዜ በእግዚያብሄር ስም አመሰግናለሁ።

## አባሪ 5

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | መረጃ የሰጡበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መጋቢ ሀዲስ መልአከ መንክራት ቆሞስ አባ አብርሀም ዳኛቸው | ወ | 35 | ሚያዝያ 27፣2014 |
| 2 | መጋቢ ሀዲስ ቆሞስ አባአባ ወልደ አማኑኤል | ወ | 63 | ሚያዝያ 27፣2014 |
| 3 | አባ በለጠ ሞላ | ወ | 76 | ሚያዝያ 27፣2014 |
| 4 | አባ መላኩ በላይ | ወ | 52 | ሚያዝያ 28፣2014 |
| 5 | አብዬ ተረፈ ፀጋ | ወ | 83 | ግንቦት 1፣2014 |
| 6 | አባባ ደርብ ዋጋዬ | ወ | 80 | ግንቦት 5 ፣2014 |
| 7 | እማሆይ ፅጌ ተክሉ | ሴ | 55 | ግንቦት 4፣2014) |
| 8 | እማሆይ ትርሲተ ማርያም | ሴ | 40 | ግንቦት 4፣2014 |
| 9 | ዲ/ን ፅጉ ተስፋ | ወ | 41 | ግንቦት 3፣2014 |
| 10 | ዲ/ን ሀይለገብርኤል | ወ | 35 | ግንቦት 3 ፣2014 |
| 11 | አማማ ሰርካለም ጥሩ | ሴ | 58 | ግንቦት 5 |